አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3578 | ቅዳሜ ሰኔ 13 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# የምቹ ከተማ አረንጓዴ ጋሻ

- የአዲስ አበባን የደን ሽፋን 30 በመቶ በማድረስ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት ዘንድሮም የተጠናከረ ስራ እንደሚከናወን ተጠቁሟል



➔ 6

ፎቶ- ከገፀ ድር
የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዘንድሮው ሀገር አቀፍ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ማስጀመሪያ ላይ ችግኝ ሲተክሉ

## የ"ሲስተም የለም" ሰበብን ታሪክ ያደረገው ተቋም

➔ 14



ፎቶ- ከገፀ ድር
የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ደሳለኝ ተረፈ (ኢንጅነየር)

## ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ቱሪዝም መንገድ



➔ 11

ፎቶ- ከገፀ ድር
ሰዎች በፊልም ቤት ተሰባስበው የትርጉም ፊልም ሲመለከቱ

## የአለም ዋንጫ፡- አይረሴ ትዝታዎቻችን

➔ 20




ፎቶ- ከገፀ ድር
የ96 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋው የዓለም ዋንጫ ውድድር በልዩ ልዩ ትዝታዎች ታጅቦ ጉዞውን ቀጥሏል

# የጠላቶቿን ሴራ እንደ በረዶ እያቀለጠ ያለው የኢትዮጵያ እውነት

በመለሰ ተሰጋ

"ዓባይ ወንዛ ወንዙ፤ ብዙ ነው መዘዙ" እንዲሉ፣ የኢትዮጵያ ጠላቶች ለበርካታ ዘመናት ዓባይን ምክንያት እያደረጉ ጦር አዝምተውባታል፡ ፡ በደቦ ዝተውባታል። እንደ ጦስ ዶሮ ዙሪያዋን እየተሽከረከሩ ሕልሟን ቅዠት፤ እውነቷንም ሀሰት ሊያደርጉ ያልቧጠጡት ዳገት፣ ያልጫሩት የነገር ክብሪት ያላቀጣጠሉት የእልቂት እሳት የለም፡፡ ግን በኢትዮጵያውያን ብርቱ ክንድ እየተደቆሱ ወደ መጡበት መመለስ ታሪካቸው ሆኖ ቀረ እንጂ፡፡

በተለይ ግብፅ የዓባይን በረከት ብቻዋን ጠቅልላ

ወደ ገጽ 3 ዞሯል




ፎቶ- ከገፀ ድር
አምባሳደር ዲና ሙፍቲ



Addis Media Network-AMN
Addis Media Network-AMN
Addis Media Network-AMN
www.amn.gov.et
Addis Media Network

# ለላቀ ስኬት የታጩ ቀናት

- በ90 ቀናት የህዝብን የኑሮ ጫና ማቃለል፣ የአገልግሎት አሰጣጥን ማዘመን፣ የተጀመሩ የኮሪደር ልማት እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራዎችን በጥራት፣ በተያዘላቸው የጊዜና የበጀት ገደብ ማጠናቀቅ ላይ ትኩረት ይሰጣል

በሳህሉ ብርሃኑ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የነዋሪዎችን እንግልትና ምሬት የሚቀንሱ፣ ፈጣንና ውጤታማ ለውጥ የሚያመጡ ስራዎችን በአጭር ጊዜ ዕቅዶች ውስጥ አካትቶ በተለየ ትኩረት መተግበር ከጀመረ ውሎ አድሯል። ለዚህ ደግሞ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የ90 ቀናት እቅዶችን በልዩ ሁኔታ አዘጋጅቶ ከቢሮ እስከ ወረዳ ድረስ በማውረድ እንዲተገበር እያደረገበት ያለው ልምድ ተጠቃሽ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ርዕሰ አንቀፅ



## የአረንጓዴ አሻራን የማኖሩ ተግባር የሁሉንም ንቁ ተሳትፎ ይሻል!

ኢትዮጵያ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን መተግበር ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ፣ ሰባት ክረምቶችን በስኬት መጓዝ ችላለች። ይህ መርሃ ግብር ከአንድ ተራ የተከላ እንቅስቃሴ አልፎ፣ ሀገራችን ለዓለም የተሻለ የአየር ንብረት ጥበቃ እያበረከተች ያለችው ታላቅ የጋራ ጥረት መገለጫ ሆኗል። በሀገር ደረጃ የአረንጓዴ ሽፋን ትርጉም ባለው መጠን መጨመሩ፣ የአካባቢ አየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመቀነስ እና የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ሂደትን ለማሳለጥ ጉልህ ሚና እየተጫወተ ነው። ይህ ድንቅ ተግባር ዛሬም በአዲስ አበባችን እና በየክልሉ በከፍተኛ ወኔ እየቀጠለ ይገኛል።

በአዲስ አበባ የአረንጓዴ አሻራ በተግባር እየታየ ነው። የከተማዋ ነዋሪዎች፣ የመንግስት ተቋማት እና የከተማ አስተዳደሩ በጋራ ችግኞችን በመትከል አሻራቸውን አሳርፈዋል፡፡ ባለፉት ሰባት ዓመታት 90 ሚሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል፡፡ በመንከባከቡ በኩል በተሰራው ስራም የ86 ነጥብ 82 በመቶ የጽድቀት ምጣኔ መመዝገቡን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህ ዛሬ ላይ የከተማዋን ገጽታ በመቀየር ላይ ነው። የአረንጓዴ ሽፋን እድገቷ፣ ከተማዋ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ንጹህ አየር የተላበሰች እና ውብ እንድትሆን ትርጉም ያለው ለውጥ እያመጣ ነው። እነዚህ የተተከሉ ችግኞች የከተማዋ ሳንባ ሆነው፣ የአካባቢ ሙቀትን በመቀነስ እና ውበቷን በማጎልበት ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው።

ዘንድሮም አዲስ አበባ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር 6 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ተዘጋጅታለች፡፡ ይህም እቅድ ስኬታማ እንዲሆን የሁላችንም ተሳትፎ ወሳኝ ነው። የከተማ አስተዳደሩ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት አስፈላጊውን ሁሉ ዝግጅት እያደረገ ቢሆንም፣ የዚህ እቅድ ባለቤት የከተማዋ ነዋሪዎች ናቸው። እያንዳንዱ የከተማዋ ነዋሪ በግል ወይም በቡድን በመደራጀት ለዚህ ታላቅ አገር አቀፍ እንቅስቃሴ የራሱን ድርሻ መወጣት ይኖርበታል። የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ብሔራዊ ኩራታችን መሆኑን ተገንዝበን፣ ዘንድሮም በተቀናጀ መንገድ መረባረብ ይጠበቅብናል።

ይህ ጥረት የግለሰቦችን ብቻ ሳይሆን፣ የመንግስት እና የግል ተቋማትንም ንቁ ተሳትፎ ይሻል። ተቋማት በአካባቢያቸው የሚገኙ ቦታዎችን በልማት ስራዎች በማካተት፣ ሰራተኞች በየስራ ቦታቸው የሚያኖሩት አረንጓዴ አሻራ ለከተማዋ አጠቃላይ የአየር ንብረት ሚዛን መጠበቅ ወሳኝ ነው። በተለይም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ከተማዋ የጀመረችውን የኮሪደር ልማት እና አረንጓዴ አካባቢዎች የማስፋፋት ስራ ላይ በንቃት መሳተፍና መደገፍ እንዲሁም በአካባቢያችን ያሉትን ችግኞች በጋራ እንክብካቤ ማሳደግ ግዴታችን ነው።

ችግኝ መትከል የመጀመሪያው እርምጃ ሲሆን፣ ዋነኛው የጥንካሬ መለኪያችን ደግሞ የተተከሉ ችግኞችን ማጽደቅ ነው። ላለፉት ሰባት ዓመታት የተተከሉ ችግኞች የጸደቁበት መጠን፣ ለወደፊት የምንተክላቸውም ስኬት ማሳያ ይሆናል። የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ለተተከሉ ችግኞች የውሃ አቅርቦት፣ ጥበቃ እና እንክብካቤ በማድረግ ረገድ የምታሳዩት ቀናኢነት፣ የከተማዋን የአረንጓዴ እድገት ዘላቂነት ያረጋግጣል። በአንድነት የምንተክላቸው ችግኞች፣ የነገዋን አዲስ አበባ የበለጸገች ያደርጓታል።

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ትኩረት የሚፈልጉ የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች ትዝብት

ቀላል የማይባል ቁጥር ያለው የከተማዋ ሰው ሸማች ነው፡፡ በተለይ መሰረታዊ የሚባሉ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለዕለት ተዕለት ፍጆታው ሸምቶ ወይም ገዝቶ ይጠቀማል፡፡ እኔም የዚህ የህብረተሰብ ክፍል አካል እንደመሆኔ ወደ ገበያ ሥፍራዎች እወጣለሁ፡፡ የዋጋ፣ የምርት አቅርቦት፣ የጥራት እና የጤናማ ግብይት ስርዓት መዛባት ከገበያ ሥፍራዎች ደርሶ ለመመለስ ሲታሰብ እንደሚያስጨንቅ እኔና መሰሎቼ እናውቀዋለን፡፡

የመሰረታዊ ፍጆታ ምርቶች አቅርቦት ላይ የሚታየውን ችግር መፍታት በገበያው ላይ ለሚታየው ውስብስብ ችግር አንዱ መፍትሄ እንደሆነ ሸማቹ ብቻ ሳይሆን መንግስትም ተረድቶታል ማለት ይቻላል፡፡ ይህንን እንድል ያደረገኝ፣ የተለያዩ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ለሸማቹ እንዲደርሱ እየሠራ ያለው ሥራ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ የሚገኙ የሸማች ሱቆች፣ የቅዳሜ እና እሁድ ገበያዎች፣ ግዙፍ የግብርና ምርት ማከማቻ እና መሸጫ ማዕከላት አገልግሎት ላይ መዋላቸው ለዚህ ምስክር ነው፡፡ እነዚህ የምርት ማቅረቢያና መሸጫዎች ባይኖሩ የከተማዋ ነዋሪ ኢኮኖሚያዊ ጫና ምን እንደሚሆን መገመት አያዳግትም፡፡

እኔ ይህንን ሃሳብ ላነሳ ምክንያት የሆነኝ በተደጋጋሚ በአካባቢዬ ወዳለው የቅዳሜ እና እሁድ ገበያ በመሄድ ያስተዋልኩት ነገር ነው፡፡ ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት የቅዳሜ እና እሁድ አይነት የግብይት አማራጮች መስፋፋታቸው የሚመሰገን ነው፡፡ እነዚህ የግብይት ሥፍራዎች በከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ ድጋፍ፣ አምራቹና ሸማቹ በቀጥታ እንዲገናኙባቸው ታልሞ ወደ ሥራ የገቡ ናቸው፡፡

ይህም ሆኖ የግብይት ሥፍራዎቹ ለህብረተሰቡ ተገቢ አገልግሎት መስጠት ላይ የተወሰነ ጉድለትና ክፍተት ይስተዋልባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ያክል እኔ አካባቢ ባሉ የቅዳሜ እና እሁድ ገበያዎች ላይ ከታዘብኳቸው ጉድለቶች መካከል፡- የግብርና ምርት አቅራቢዎች ሁሉንም ዓይነት መሰረታዊ የግብርና ምርቶች ይዞ አለመቅረብ፣ የምርት ጥራት ጉድለት፣ አልፎ አልፎ በመሸጫ ቦታቸው ላይ ከተለጠፈው የዋጋ ተመን አስበልጦ መሸጥ ይጠቀሳሉ። በተለይ የሽንኩርት፣ የድንች እና የቲማቲም ምርት ዋጋ እና አቅርቦት ላይ በተደጋጋሚ የሚታይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ከላይ ያነሳኋቸውን በቅዳሜ እና እሁድ ገበያዎች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት፣ ከጅምሩ የገበያ ሥፍራዎቹን በማመቻቸት አምራቹና ሸማቹ በቀጥታ እንዲገናኝ ያደረገው ተቋም ኃላፊነቱን ሊወስድ ይገባል፡፡

በእነዚህ የግብይት ሥፍራዎች የሚቀርቡ ምርቶች ጥራት፣ ዓይነትና ዋጋ ሸማቹን የሚያስደስት፣ አቅራቢውንም የሚጠቅም እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡ የዕለት ተዕለት ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በምርት አቅርቦት ሰንሰለቱ ላይ የሚታዩ ችግሮችን በጥናት በመለየት መፍትሄ መስጠትም ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ሲሆን፤ ለትልቅ ዓላማ የተቋቋሙት የቅዳሜ እና እሁድ ግብይት ሥፍራዎች ስኬታማነት ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

ሸማቹም አቅራቢውም ፍትሐዊ ተጠቃሚነታቸው ይረጋገጣል፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

**እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
(Creative Art Director)
እዮብ ተፈራ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ለይላ መሀመድ
ሄለን ጥላሁን
ፋንታነሽ ተፈራ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# የጠላቶቿን ... ከገጽ 1 የዞረ

መብላቷ ሳያንስ ወንዙንም በስሟ ልታስጠራ የተጓዘችው ርቀት እንኳን ለሷ በእውነት መነፅር ለተመለከተው ሁሉ እጅግ አድካሚ ነው:: "እውነትና ንጋት እያደር ይገለጣል" እንዲሉ፣ ዓባይ ዛሬ ምንጩን እያስታወሰ፤ ኢትዮጵያ እናቱን በልማት እየካሰ ጉባ ላይ ከትሟል::

ታዲያ ይህ እውነት መገለጡ፣ እኩልነት መንገሱ ያንገበገባት ግብፅ ዛሬም እንደ ትናንቱ ከኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ጠላቶች ጋር እየተመሳጠረች የሴራ ጥንስሷን፣ የተንኮል ድግሷን እያሰናዳች ነው:: የሀገሬ ሰው "እኛ መች አልንና የጎረቤት ጠጅ፤ እየበጠበጡ ይጠሩናል እንጅ" እንዲል ከሻቢያ እና መሰል የኢትዮጵያ ሰላም ውሎ ማደር ህመም ከሚሆንባቸው ጋር ያሰናዱት ድግስ በኢትዮጵያውያኑ ብርቱ ክንድ የጨረባ ተስካር ሆኖ እንደሚቀር ታሪክ ምስክር ነው::

ለአብነትም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ3000 ዓመት ዓለም የግብፅ ንጉስ ዳግማዊ ነቶሎሚ የዓባይን ምንጭ እርግጠኛ ቦታ ለማወቅ ወደ ኢትዮጵያ ሰላዮችን ብቻ ሳይሆን ጦርም አዝምቶ እንደነበር አስትሪያዊ የግብፅ ታሪክ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ጉንተር ሆልብል እ.ኤ.አ 2001 "A History of the Ptolemaic Empire" በሚል ርዕስ ባሳተሙት ጥናታዊ መፅሐፍ ላይ ሰፍሯል። ይህ ሀቅ የግብፅ ሴራ ዘመናትን የተሻገረ ስለመሆኑ አንዱ ምስክር ነው::

ይህም ግብፅ፣ በሮማውያን አውግስጦስ ቄሳር ዘመነ መንግስት በተገዛችበት ወቅትም (ማለትም እስከ 30 ዓ.ዓ ድረስ) የቀጠለ ነው:: በዘመኑ የቄሳር እንደራሴ የነበሩ የግብፅ ሹማምንት በዘመኑ የተሻለ የጂኦግራፊ ዕውቀት የነበረውን ፊሊጶስ የተባለ ጣሊያናዊ በመመልመል እና ጦራቸውን በማስከተል ወደ ኢትዮጵያ ልከው እንደነበር እና አሁንም የቄሳርና የፈርኦን ፈረሶች ስለመሸነፋቸው ታሪክ ይነግረናል::

አዎ! ዛሬ ታሪክ ቢቀየርም ጉንደትና ጉራን በመሳሰሉ ግብፅ አውደ ውጊያዎች ጦር ከማዝመት፣ የኢትዮጵያን ሰላም በእጅ አዙር ከማናጋት ባሻገር የዓባይን ልጅ ውሃ ሲያስጠሙ የነበሩ ስምምነቶችንም በማድረግ ትታወቃለች::

የመጀመሪያው ስምምነት እ.ኤ.አ በ1891 ሚያዝያ ወር ላይ የተደረገው የአንግሎ ጣሊያን ፕሮቶኮል ሲሆን፣ ይሄውም ጣሊያን በማን አለብኝነት ኢትዮጵያን ወክላ ከጥቁር ዓባይ ገባር ወንዞች አንዱ በሆነው በተከዜ ወንዝ ላይ ምንም አይነት ልማት እንዳይከናወን የተደረገ ስለመሆኑ በስምምነቱ አንቀፅ 3 ላይ ሰፍሯል::

ሁለተኛው ስምምነት በእንግሊዝ፣ በጣሊያን እና በኢትዮጵያ መካከል እ.ኤ.አ በ1902 ግንቦት ወር ላይ የተደረገ ነው:: በዚህ ስምምነት አንቀፅ 3 ላይ እንደሰፈረው አሁንም በዓባይ ተፋሰስ ምንም አይነት ልማት እንዳይከናወን የሚል ሲሆን፣ ባይሳካም ቅሉ ኢትዮጵያን በእንግሊዘኛ እና በአማረኛ ትርጉም ለማሳሳት የተደረገ ጥረት ነበር::

ሦስተኛው እ.ኤ.አ በ1909



ፎቶ- ከገፀ ድር
የግብፅ የአባይን ውሃ በብቸኝነት የመጠቀም ፍላጎት ኢትዮጵያን ሰላም በመንሳት ጭምር የቀጠለ ነው

በዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ መንግስትና በእንግሊዝ መካከል የተደረገ ስምምነት ሲሆን፣ ይህም ኢትዮጵያን ያገለለ ነበር። አራተኛው እ.ኤ.አ 1909 መስከረም ወር ላይ በእንግሊዝ፣ በፈረንሳይ እና በጣሊያን መካከል የተደረገ ስምምነት ነው:: በዚህ ስምምነት አንቀፅ 4 (ሀ) በግልፅ እንደሰፈረው የዓባይ ተፋሰስን እና ገባር ወንዞችን መቆጣጠር እና መጠቀም የሚቻለው ቅድሚያ የግብፅና እንግሊዝ ፍላጎትንና ጥቅምን ባስቀደመ መልኩ እንደሆነ የሚደነግግ ስምምነት ነበር::

አምስተኛው እ.ኤ.አ በ1925 እንግሊዝ እና ጣሊያን በጣና ሐይቅ ላይ ያደረጉት የማስታወሻ ልውውጥ ነው:: ይህም ጣሊያን በኢትዮጵያ ውሃ የመጠቀም ቀዳሚውን ዕድል ለግብፅና ለሱዳን አሳልፋ የሰጠችበት ነበር::

ስድስተኛው እ.ኤ.አ በ1929 ግንቦት ወር ላይ በግብፅ እና በአንግሎ ግብፅ - በሱዳን መካከል የተደረገ ስምምነት ነው። በዚህ ስምምነትም ሱዳንና ግብፅ የዓባይ እናት የሆነችውን ኢትዮጵያን አግልለው ውሃውን እንደ አቅማቸው የተከፋፈሉበት መርህ አልባ ውል፣ እውነት የራቀው ስምምነት እና ጊዜ የገለጠው ሴራ ነበር::

ሰባተኛው እ.ኤ.አ በ1959 ግብፅ የዓባን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ዳግም ከሱዳን ጋር የተፈራረመችው ስምምነት ነው:: ስምንተኛው ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ ከ1891 ጀምሮ በራሷ ውሃ የማዘዝ መብቷ በታሪካዊ ጠላቶቿ ሴራ ተነፍጎ ከቆየ በኋላ በኢትዮጵያ አስተባባሪነት እ.ኤ.አ በ1999 የተቋቋመው የዓባይ ተፋሰስ የጋራ ስምምነት (The Nile Basin Initiative) ነው::

ይህ ስምምነት ከጥንት እስከ ትናንት በግብፅና መሰል የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች የተሸረበውን ሴራ ያመከነ፣ እኩልነትን ያነገሰ የኢትዮጵያን የዘመናት እምባ ያበሰ ብስራት ነው:: ምንም እንኳ

> **"ግብፆች ሁልጊዜ ኢትዮጵያን በጥርጣሬና በጥላቻ ይመለከቷታል። ይህም ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተባባሪዎቿን የማደራጀት፣ የመደገፍና በኢትዮጵያ ላይ በጠላትነት የማነሳሳት ተግባሯ ያልተቋረጠና ዘመናትን ያስቆጠረ ነው"**

ከትናንት የሽንፈት ታሪካቸው ያልተማሩ ግብፅና ሻቢያን የመሳሰሉ ተላላኪዎቿ ዛሬም ከጥፋታቸው ባይመለሱም ዓባይ ግን ዐይናቸው እያየ በኢትዮጵያ ሰማይ ስር በንጋት ሐይቅ ላይ አረፍ ብሎ ለኢትዮጵያውያን ራትና መብራት መሆኑን ቀጥሏል::

ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ በግብፅ፣ የኢትዮጵያ ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሆነው ለረዥም ዓመታት ያገለገሉት አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገዋል::

አምባሳደሩ እንደሚሉት ግብፆች ሁልጊዜ ኢትዮጵያን በጥርጣሬና በጥላቻ ይመለከቷታል:: ይህም ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተባባሪዎቿን የማደራጀት፣ የመደገፍና በኢትዮጵያ ላይ በጠላትነት የማነሳሳት ተግባሯ ያልተቋረጠና ዘመናትን ያስቆጠረ ነው::

ግብፅ፣ ኢትዮጵያን በጠላትነት የመፈረጇ ምስጢር እንደ ምክንያትነት የሚነሳው የዓባይ ወንዝ ጉዳይ ነው:: ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነውን የናይልን ውሃ የምታመነጨው ኢትዮጵያን ትተው 'ውሃው የእኛ ነው' የሚል የተሳሳተ ትርክት ገንብተዋል::

እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስም "ውሃው የኢትዮጵያ ነው" የሚለውን ሀቅ የማይቀበሉበት ሁኔታም ነበር:: ለዚህም የ1929 እና 1959ኙ አግላይና ከእውነት የራቀውን የተሳሳተ ስምምነት በዋቢነት ጠቅሰዋል::

ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ግብፃውያኑና ፈረሶቻቸው በኢትዮጵያውያኑ ብርቱ ክንድ የተሸነፉበት ዋናው ምስጢር ኢትዮጵያ ከመጀመሪያው ጀምሮ የያዘችው አቋም በሀቅ ላይ የተመሰረተ እና በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የጸና በመሆኑ ነው::

ኢትዮጵያ የሕዳሴውን ግድብ በምትጀምርበት ጊዜም ከግብፅ፣ ከሱዳን እና ከኢትዮጵያ የተውጣጡ ባለሙያዎች ግድቡ በፍትሐዊነት፣ በእኩልነት እና በእውነት ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ እንዲያጠኑ በሯን ከፍታ ሰርታለች። በሦስትዮሽ ድርድሮችም በሀቅ ላይ የተመሰረተውን አቋሟን በተደጋጋሚ አሳውቃለች:: ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ መልካም ነገር ውስጥ ግብፅ ታሪካዊ ጠላትነቷን በተለያየ መልኩ እያንፀባረቀች ቀጥላለች ይላሉ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ።

"ሀቅ ላይ መቆም ሁሌም አሸናፊ ያደርጋል" የሚሉት አምባሳደሩ፣ ግብፅ ምንም እንኳ ከትናንት እስከ ዛሬ የኢትዮጵያን ጠላቶች በማደራጀት ብዙ ብትጥርም በሀሰት ላይ የተመሰረተ ነውና እውነት የያዘችውን ኢትዮጵን ማሸነፍ እንደማትችል ታሪክ ምስክር ነው::

የህዳሴው ግድብን ማስቆም ያልቻለችው ግብፅ፣ አሁንም የኢትዮጵያን ትክክለኛ የባህር በር ጥያቄ ምክንያት በማድረግ ዳግም በጠላትነት ተነስታለች::

ከቀይ ባህር በቅርብ ርቀት ያለችና በቀጣናው የቀደመ ጥብቅ እና ገናና የታሪካዊ ትስስር ያላትን ሀገር ከዚህ ስትራቴጂካዊ ክልል ለማራቅ ብዙ ሴራዎችን እየጎነጎነች ነው::

ይሁን እንጂ ሁሌም በእውነት፣ በእኩል መልማት እና በሰጥቶ መቀበል መርህ ላይ የተመሰረተችው ኢትዮጵያ መቼም አሸናፊ ናት::

በመሆኑም የግብፅ፣ የሻቢያና የተላላኪዎቻቸው ሴራ እንደ በረዶ ክምር በእውነት ፀሐይ ሳይውል ሳያድር ይቀልጣል:: ለዚህ ደግሞ ዛሬም እንደ ትናንቱ ኢትዮጵያውያን ያለምንም ልዩነት ብሔራዊ ጥቅሞቻችን እንዲከበሩ እንድ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነን ልንቆም እንደሚገባም መክረዋል::

ዜና ትንታኔ

## ለላቀ ... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በከተማ አስተዳደሩ የ90 ቀናት ዕቅድ ላይ ከመላውየከተማዋ አመራሮች ጋር ተወያይተው ወደ ተግባር አስገብተዋል

ነው። ይህ ተግባራዊ በመሆኑም በርካታ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዎችን አስገኝቷል። ለማህበረሰቡ የሚቀርበው አገልግሎት እንዲሻሻል የማይናቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

ከሰሞኑም በ90 ቀናት ዕቅድ ላይ መላውን የከተማዋን አመራሮች ያካተተ ውይይት ተደርጎ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ በዚህም የህዝብን የኑሮ ጫና ለማቃለልና የአገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን ትኩረት የሰጠበትን የ90 ቀናት እቅድ ይፋ አድርጓል። በዚህ ወቅት ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ "በፍጥነት ፊታችንን ወደ ሥራ በመመለስ ፈጣን ውጤቶችን ማስመዝገብ፣ ተከታታይና አዳዲስ ነገሮችን መተግበር፣ ህብረተሰባችን ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በላቀ ትጋትና ያለ እረፍት መፈጸም የሚያስችል እቅድ ይዘን በልዩ ትኩረት የምንፈጽም ይሆናል" ብለዋል፡፡

በዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዘውን የ አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል አገልግሎት በማስፋት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የታለመ ሲሆን፣ የኑሮ ውድነትን ከማረጋጋትና የንግድ ስርዓቱን ከመግራት ጀምሮ እስከ ከተማ ግብርና፣ አረንጓዴ አሻራ እና የተጀመሩ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማቶችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ በጥራት ማጠናቀቅ ላይ በስፋት እንደሚሰራም ተገልጿል። ይህ የተቀናጀ ዕቅድ የከተማዋን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ፣ የበጎ ፈቃድና የሰላም ግንባታ ስራዎችን ከህብረተሰቡ ተሳትፎ ጋር በማጣመር የነዋሪዎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት በተጨባጭ ለማረጋገጥ ያለመ ነው ተብሏል።

የ90 ቀናት ርብርብ የቤት ግንባታን እንደ ዋና አጀንዳ ይዞ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ከንቲባ አዳነች አቤቤ አስታውቀው፣ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የቤት ግንባታው በልዩ ትኩረት ሊሰራ እንደሚገባም አንስተዋል፡፡ በዚህም ዙሪያ ቁልፍ የስራ አቅጣጫዎችን ያስቀመጡ ሲሆን፣ በመካሄድ ላይ ያሉ የቤት ግንባታ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ማድረግ፣ የ2019 ዓ.ም የቤት ልማት ፕሮጀክቶች የሚሆኑ ቦታዎችን መለየት እና ዲዛይን ማዘጋጀት፣ ኮንትራክተሮችን፣ አማካሪዎችን እና የሰው ኃይል ዝግጅትን በአጭር ጊዜ ማጠናቀቅ ዋና ዋና ትኩረቶች መሆናቸውን አመላክተዋል።

በመንግስት ይዞታ ስር ያሉ ሰፋፊ ቦታዎችን ለዘላቂ እና ብዙ ህዝብን ሊያስተናግዱ ለሚችሉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ባለ አራት ወለል እና ከዚያ በላይ ለመገንባት እንደሚውሉም ገልጸዋል።

በእነዚህ 90 ቀናት ውስጥ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የተለዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት እና አገልግሎትን የማሻሻል ስራን በማጠናከር የአዲስ መሶብ አንድ ማዕከል ዲጂታል አገልግሎትን ማስፋት ዋነኛ ግቦቹ መሆናቸውን ከንቲባዋ ጠቁመዋል። ከዚህም በተጨማሪ የኑሮ ውድነትን ማረጋጋት፣ የንግድ ሥርዓቱን መግራት፣ የስራ እድል ፈጠራ እንዲሁም የወጣቶችና ሴቶች ተጠቃሚነት ላይ በትኩረት እንደሚሰራም አብራርተዋል። በአረንጓዴ ዐሻራ ልማት፣ በከተማ ግብርና፣ በሌማት ትሩፋት፣ በሰላም ግንባታ እና በገቢ አሰባሰብ ላይ ሰፋፊ ስራዎች እንደሚሰሩ የገለጹት ከንቲባ አዳነች፤ ልመናንና ተረጂነትን በመቀነስ የበጎ ፍቃድ መርሃ ግብርን በተቀናጀ የህብረተሰብ ተሳትፎ ለመተግበር መታቀዱን አመላክተዋል።

ከንቲባዋ ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን፣ የተጀመሩ የኮሪደር ልማት እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራዎችን በጥራት፣ በተያዘላቸው የጊዜና የበጀት ገደብ ለማጠናቀቅ እንዲሁም የሚዲያና የሕዝብ ግንኙነት ስራዎችን ይበልጥ ለማጠናከር አስተዳደሩ ሙሉ በሙሉ መዘጋጀቱን አስታውቀዋል። አያይዘውም የ2018 በጀት ዓመት ማጠቃለያ እና የ2019 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት ላይ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ገልጸው፣ "አዲሱ በጀት ዓመት ህዝባችንን ይበልጥ የምናገለግልበት፣ አዲስ አበባን የብልፅግና ተምሳሌት የማድረግ ጉዟችንን የምናረጋግጥበት እንዲሆን ከእቅድ ዝግጅት እስከ ተግባር አፈፃፀም በጠንካራ ክትትልና ድጋፍ የምንፈፅም ይሆናል" ሲሉ አረጋግጠዋል።

ይህንን ግብ በተሟላ ሁኔታ ስኬታማ ለማድረግም፣ ከከተማ አስተዳደሩ ዋና ዋና ተቋማት ጀምሮ እስከ ታችኛው የወረዳ መዋቅር ድረስ የሚገኙ ሁሉም ክፍለ ከተሞች በተቀናጀ ሁኔታ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ገብተዋል። እያንዳንዱ የአስተዳደር እርከንና ተቋም የተጣለበትን ኃላፊነት በመገንዘብ፣ የነዋሪዎችን እንግልት የሚያቃልሉና ፈጣን ለውጥ የሚያመጡ አሰራሮችን መሬት ለማውረድ በቁርጠኝነት ስራቸውን የጀመሩ ሲሆን፣ ይህም የተቀናጀ ርብርብ ዕቅዱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጨባጭ ፍሬ እንዲያፈራ ትልቅ መነቃቃትን ፈጥሯል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮም በ90 ቀናት ሊተገበሩ የሚገባቸውን ዋና ዋና ተግባራት ለቢሮው ተጠሪ ከሆኑ የክፍለ ከተማ ጤና ጽህፈት ቤቶች እና የሆስፒታል ኃላፊዎች በተገኙበት ዕቅዱን አቅርቦ ውይይት አካሂዷል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ ዮሐንስ ጫላ (ዶ/ር) እቅዱ ለአገልግሎት አሰጣጥ ተግዳሮት ናቸው ተብለው የተለዩትን ተግባራት በአግባቡ በመምራት እና በተቀመጠው የጊዜ ገደብ በመፍታት ህብረተሰቡን የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል።

የቢሮው ምክትል ኃላፊ ሙሉጌታ እንዳለ (ዶ/ር) በበኩላቸው በዘጠና ቀን በእቅድ የተያዙ ተግባራት በየደረጃው ያሉ ከቢሮ እስከ ጤና ተቋማት ተናብበውና ተቀናጅተው በመስራት የሚጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ እንደሚገባቸው ገልፀዋል፡፡ በተለይም በክረምት የነፃ ህክምና አገልግሎት በምርመራ የመለየት እና የህክምና አገልግሎት በሪፈር ጭምር ለታካሚዎች የሚሰጥ፣ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለውን የጤና ችግር የሚፈታ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተናግረዋል።

ቢሮው በዘጠና ቀናት እቅዱ የጀመራቸውን የጤና ፕሮጀክቶች ማጠናቀቅ፣ ለ771 ሺህ 3 መቶ በላይ የህብረተሰብ ክፍሎች ነፃ የተለያዩ ህክምና አገልግሎቶችን መስጠት፣ 25 ሺህ ዩኒት ደም መሰብሰብ፣ ለ50 ሺህ የህብረተሰብ ክፍሎች ማዕድ ማጋራት፣ የአቅመ ደካሞችን ቤት መስራት፣ በአረንጓዴ አሻራ ችግኞችን መትከል እና ሌሎችም አንኳር ተግባራት በዕቅድ ስለመያዛቸው ከቢሮው ማህበራዊ ትስስር ገጽ ላይ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ስራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አዕምሮ አዱኛ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት እንደገለፁት፣ ክፍለ ከተማው በ90 ቀናት ውስጥ የተለያዩ ስራዎችን ለማከናወን ማቀዱን አስረድተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ 12 ቦታዎችን ከስጋት ነጻ ለማድረግ ስራዎች ስለመጀመራቸው ገልፀዋል፡፡

ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎችን በመለየት የአጭርና የረጅም ጊዜ መፍትሔ ለመስጠት በትኩረት እየተሰራ እንደሚገኝ የገለፁት ደግሞ ዋና ስራ አስፈፃሚው አቶ አለማየሁ ሚጀና ናቸው፡፡ አያይዘውም ከሰሞኑ የተጀመረው የጎርፍ አደጋ ስጋት የመከላከል ስራ አደጋው ከመከሰቱ አስቀድሞ የመከላከል እርምጃዎች አንዱ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ችግሩም በመንግስት ብቻ የሚፈታ ሳይሆን በሁሉም ዜጎች ርብርብ የሚቀረፍ በመሆኑ፣ ሁሉም ዜጋ አካባቢውን በማፅዳትና የውሃ ማስተላለፊያዎችን በመክፈት ራሱን ከጎርፍና ከሌሎች አደጋዎች ሊጠብቅ እንደሚገባም አሳስበዋል።

ክፍለ ከተማው ካለው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ የተነሳ ለበርካታ ዓመታት የጎርፍ አደጋ በነዋሪዎች ህይወትና ንብረት ላይ ጉዳት ሲያስከትል መቆየቱን አስታውሰው፣ ይሁን እንጂ አስተዳደሩ በሰራቸው ሰፋፊ ስራዎች የጎርፍ አደጋን ከዓመት ዓመት በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ መቻሉን አቶ አለማየሁ ገልፀዋል።

እንደዚሁም በበጎ ፍቃድ ስራ ሰፋፊ የልማት ስራዎችን መስራት፣ የስራ ዕድል ፈጠራ ንቅናቄ ማከናወን፣ የ2 ጤና ጣቢያዎችን ግንባታ ማጠናቀቅ የሚሉ ዕቅዶች በ90 ቀናት ዕቅድ ውስጥ ስለመካተታቸው ያስረዳሉ፡፡ አክለውም የአደጋ ጊዜ ሀብት ማከማቻ መጋዘንን ሙሉ በሙሉ ወደ ስራ ማዋል፣ በግንባታ ላይ ካሉ 41 ልዩ ልዩ የልማት ፕሮጀክቶች መካከል የተጠናቀቁትን ወደ ስራ ማስገባትና በግንባታ ላይ ያሉትን ደግሞ ለማጠናቀቅ ዕቅድ ስለመያዙ የጽህፈት ቤት ኃላፊው አቶ አዕምሮ አዱኛም አብራርተዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤም በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት፣ በድህረ-ምርጫ በፍጥነት ፊትን ወደ ስራ በመመለስ ፈጣን ውጤቶችን ማስመዝገብ፣ እንዲሁም ህብረተሰቡ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በላቀ ትጋትና ያለ እረፍት መፈጸም የሚያስችል ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር መገባቱን ገልጸዋል።

# አዲስ አበባ የጎርፍ ስጋትን ለመከላከል ምን ያህል ተዘጋጅታለች?

- **በወንዝ ዳርቻ ልማቱ ቀበና፣ ባንተይቀጡ እና ሌሎች ወንዞች ከጎርፍ ስጋትነት ተላቅቀው ውበትና ምግብ የሚፈልቅባቸው ሆነዋል**

**በመለሰ ተሰጋ**

ዓለማችን ባለፉት 48 ዓመታት ውስጥ ብቻ 1 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሰዎችን በጎርፍ አደጋ አጥታለች፡፡ ይህን ያሳወቀው ቤልጂየም የሚገኘው የምድራችን አደጋዎች የመረጃ ቋት ወይም የአደጋዎች ኤፒዲሚዮሎጂ ምርምር ማዕከል (CRED) እ.ኤ.አ የካቲት 28 ቀን 2024 ዓ.ም ይፋ ባደረገው ጥናታዊ መረጃ ነው፡፡ በዚህ መረጃ መሰረት እ.ኤ.አ ከ1975 እስከ 2022 ባሉት ዓመታት ከላይ የተጠቀሱትን ያህል ሰዎች በጎርፍ አደጋ ይችን ምድር ተሰናብተዋል፡፡

አዎ! አንዳንዴ የሚንከባከባት አጥታ ተፈጥሮ ስትቀየም ወንዞች ያኮርፋሉ። ከአፍ ከገደፋቸውም አልፈው ይጎርፋሉ፡፡ እንዲህ ሲሆን፣ ደግሞ የበርካቶች ውድ ሕይወትና ንብረት እንደዋዛ ይጠፋል፤ ይረግፋል። ከዓመታት በፊት የአዲስ አበባ ወንዞች እውነታም ከዚህ የራቀ አልነበረም፡፡ አዲስ አበባ ተዳፋታማ የመሬት አቀማመጥ ያላት ከተማ ናት፡፡ ከፍታማ ከሆነው የእንጦጦ ተራራማ ሰንሰለት በመነሳት ከተማዋን ወዲያና ወዲህ እየከፈሉ የሚነጉዱ ቀበና እና ባንተይቀጡን የመሳሰሉ ወንዞችና ጅረቶች አሏት፡፡ ታዲያ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ከተማዋ በኮሪደር እና በወንዝ ዳርቻ ልማት ከመዋቧ በፊት፣ ወንዞቿና ዳርቻዎቻቸው እንዲህ እንደ ዛሬው እንጀሪ ሳይቆረጥባቸው ብዙ ዋጋ አስከፍለዋል፡፡ ለአብነት የአቶ አዳም ባንተይርጋ እና የቀበናን ወንዝ የሕይወት ሰበዝ መዝዘን ጥቂት እንጨዋወት፡፡ በቀበና ወንዝ ዳርቻ ለአስር ዓመታት ያህል ኖረዋል፡፡ እናም ቀበናን ከእግር እስከራሱ፤ ከፈገግታ እስከ ቁጣው ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ በክረምት ከእንጦጦ ጋራ ስር ጀምሮ አሰሱን ገሰሱን እየጠራረገ፣ ደሳሳ ጎጇቸውን እየታከከ ይወርዳል፤ ይነጉዳል፡፡ እርሳቸውም 'ከዛሬ ነገ ከነቤተሰቤ ጠራርጎ ወሰደኝ' እያሉ ሁሌም ክረምቱን በስጋት የበጋው ወቅት ሲመጣ ደግሞ በየጥጋጥጉ አሸዋ እያለበሰ ያስቀመጣቸው የእንስሳት በድኖች እና መሰል ቆሻሻዎች ዘግናኝ ጠረን በአካባቢው ለመኖር ቀርቶ ለማለፍ ይከብድ እንደነበር አጫውተውናል፡፡

በቀበና አካባቢ በተለምዶ 06 ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ተከራይተው ይኖሩ የነበሩት አቶ አዳም ባንተይርጋ እንዳጫወቱን ያኔ የቀበና ወንዝ ክረምት ሲያስገመግም በወንዙ ዳርና ዳር ይኖሩ ለነበሩ በርካታ ሰዎች የፍርሃትን ደመና አዝሎ ይመጣ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ውበትን ተጎናፅፎ ሲመለከቱት አብዝተው መደሰታቸውን ከአንደበታቸው በላይ የፊታቸው ፈገግታ ይናገራል፡፡ በርግጥም የዝግጅት ክፍላችን በስራ ምክንያት በየጊዜው ተዘዋውሮ ሲመለከታቸው እንደነበረው የመዲናዋ ወንዞች የትናንት መልካቸው አቶ አዳም ባንተይርጋ እንደገለፁት እጅግ አስፈሪ ነበር፡፡ ለአብነትም በክረምት ወቅት በጎርፍ አደጋና ተያያዥ ችግሮች የሚደርሱ አደጋዎች ከመገናኛ ብዙሃን የዜና ዝርዝሮች መካከል እንደማይጠፉ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች የከተማዋን የጎርፍ ስጋት ተጋላጭነት ቀንሰዋል

አሁን ቀበና በኮሪደር ልማት እንደ አዲስ ተወልዷል፡፡ ለስጋት ሳይሆን ለውበት የሚወርድ ለዛና ወዝ ያለው ውብ ወንዝ ሆኗል፡፡ በዳርና በዳር ያሉ መናፈሻዎች ለአካባቢው ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን ለአላፊ አግዳሚውም የውበት ሰገነት ሆነዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መረጃ እንደሚያመለክተው ከተማዋ ከ76 በላይ ወንዞች አሏት። እነዚህ ወንዞች በድሮው ጊዜ ተፈጥሯዊ መልክና ይዘታቸው ሳይቀየር ለህብረተሰቡ የተለያየ አገልግሎት ይሰጡ ነበር፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ የከተማዋ የህዝብ ቁጥር እየጨመረ መምጣት ጋር ተያይዞ በርካታ ነዋሪዎች በወንዝ ዳርቻዎች ሰፍረዋል፡፡

ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎም ለዘመናት ተረስተው የቆዩት ወንዞችን ለማልማት፣ የተጎሳቆለውን ገፅታቸውን ለመቀየር፣ ከብክለት ለመታደግ የከተማ አስተዳደሩ በቁርጠኝነት ሰርቷል። ለአብነትም 20 ኪሎ ሜትር ርዝመት በሚሸፍነው የወንዝ ዳርቻ ልማት ቀበና ዳግም ነፍስ ዘርቷል፡፡ ቀበና እና ባንተይቀጡን የመሳሰሉ የአዲስ አበባ ወንዞች ከስጋትነት እየተላቀቁ፣ ውበትና ምግብ የሚፈልቅባቸው ሆነዋል።

የወንዝ ዳርቻ ልማቱ ጎርፍን ለመከላከል ከፍተኛ ፋይዳ አለው፡፡ በተለይ ክረምት በመጣ ቁጥር የከተማ አስተዳደሩንና ነዋሪዎችን ከሚያስጨንቁ አደጋዎች መካከል ጎርፍ አንዱ ነው፡፡ በርካታ ዜጎችም በወንዝ ዳርቻ፣ የቤታቸውን ግርግዳ ወንዙ ስር በማድረግ ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው ይኖሩ ነበር፡፡

በዚህም በተለያዩ ጊዜያት በሰው ህይወትና ንብረት ላይ አደጋዎች ሲያጋጥም ቆይቷል፡፡ በወንዝ ዳርቻ ልማቱ ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ ነዋሪዎችን በማንሳትና ንፁህና ደህንነቱ በተጠበቀ አካባቢ እንዲኖሩ በማድረግ፣ የጎርፍ መከላከያ የድጋፍ ግንቦችን በመገንባት፣ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን በመስራት የጎርፍ አደጋ ስጋትን መከላከል የሚያስችል አቅም መፍጠር ተችሏል፡፡

ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር ኮማንደር አሕመድ መሐመድ እንደገለፁት፣ በተለይ ከክረምት ጋር ተያይዞ በልዩ ሁኔታ የሚፈጠሩ አደጋዎች አሉ፡፡ ከነዚህም አንገብጋቢ የአደጋ ስጋት ሥራዎች ከሚባሉት መካከል ጎርፍና የመሬት መንሸራተት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ የኮሪደር ልማቱ በደረሰባቸው አካባቢዎች ላይ የጎርፍና የመሬት መንሸራተት ጉዳዮች ሥጋት አይደሉም፡፡ ምክንያቱም የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማቱ ጥራቱን እና ደረጃውን ጠብቆ የሚሰራ ነው፡፡ ለአብነትም መሬቱ እንዳይንሸራተት የድጋፍ ግንብ ተደርጎ፣ ድልድይ ለሚያስፈልገው ድልድይ ተሰርቶ፣ አረንጓዴ መሆን የሚገባውም አረንጓዴ ሆኖ እና በጥናት ላይ በመመስረት ሙሉ በሙሉ ደረጃውን ጠብቆ ስለሚሰራ የጎርፍና የመሬት መንሸራተት ያጋጥማል ተብሎ አይታሰብም፡፡

በለሙ አካባቢዎች ላይ ውሃው ቁጥጥር ስለሚደረግበትና አካባቢውም በአረንጓዴ ልማት ስለሚሸፈን እንዲሁም ሁሉም በመስመሩ ስለሚንቀሳቀስ የኮሪደር እና ወንዝ ዳርጃ ልማቱ ቀደም ባሉት ዓመታት ይታይ የነበረውን በተለይም በጎርፍና በመሬት መንሸራተት ይደርስ የነበረውን ስጋት እና አደጋ ቀንሷል፡፡ ከዚህ ባሻገርም የኮሪደር ልማቱ የእሳት አደጋንም ከመቀነስ አንፃር ከፍ ያለ አበርክቶ እንዳለውም ጠቁመዋል፡፡

ይሁን እንጂ በሁሉም የከተማዋ አካባቢዎች የኮሪደር ልማቱ ተደራሽ ባለመሆኑ ልማቱ ባልደረሰባቸው ቦታዎች እና ተጀምሮ ባላለቀባቸው ስፍራዎች ከጫፍ እስከጫፍ ሙሉ አይደለም፡፡ ስለሆነም የኮሪደር እና ወንዝ ዳርቻ ልማቱ ሙሉ ባልሆነባቸው ቦታዎች ላይ የጎርፍ እና የመሬት መንሸራተት ሊኖር ይችላል፡፡

ይህንንም መሰረት በማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን በሁሉም ክፍለ ከተሞች በተለይም የኮሪደር ልማቱ ባልደረሰባቸው አካባቢዎች ለጎርፍ፣ ለመሬት መንሸራተት እና ለእሳት አደጋ ስጋት በከፍተኛ፣ በመካከለኛ እና በዝቅተኛ ደረጃ ተጋላጭ የሆኑትን ለይቶ የተጠናከረ ርብርብ እያደረገ ነው፡፡

በከተማዋ በተለይ በወንዞች ዳርቻዎች ላይ የተሰራው ልማት የጎርፍ አደጋን ለመከላከል ያለው አበርክቶ ትልቅ ነው። እስካሁን በነበረው ሁኔታ የወንዞችን መስመር የሚያስተጓጉል ነገር ሲኖር ውሃው ወደ ዳር ፈስሶ ጉዳት ያደርሳል። ለምሳሌ ጎርፍ ከላይ በሚመጣበት ጊዜ ትልልቅ ዛፎችን የመሳሰሉ ግኡዝ ነገሮችን ይዞ ይመጣል፡፡

እነዚህም ነገሮች የሆነ ቦታ ላይ የውሃውን መንገድ ሲዘጉ ውሃው ወደ ግራና ቀኝ እየፈሰሰ አደጋ ያደርሳል። ይህን መሰል አደጋ ባለፈው ዓመትም ኮተቤ አካባቢ አጋጥሟል፡፡ አሁንም እንዳይከሰት የስጋት አካባቢዎች ተለይተው እየተሰራ ነው፤ ብለዋል ኮማንደር አሕመድ መሐመድ፡፡

እንደ ኮሚሽነሩ ማብራሪያ በኮሪደር እና በወንዝ ዳርቻ ልማቶች የወንዞችን መውረጃ የማስፋት ስራዎች እና ዳር እና ዳር የመከላከያ ግንባታዎች ተከናውነዋል። ይህም ውሃው ተፈጥሯዊ ፍሰቱን ጠብቆ እንዲሄድ ያደርገዋል፡፡

በመንግስት በኩል ሰፊ የንቅናቄ ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን የገለፁት ኮሚሽነር ኮማንደር አሕመድ መሐመድ እንደ ከተማም ችግሮችን ለመለየት ተሞክሯል፡፡ የማቅለያ ስራም ለመስራት ሰፊ ርብርብ እየተደረገ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሉም ቦታ ላይ ተደራሽ ሆኖ በደንብ ተለይቷል ማለት ላይሆን ችላል፡፡ ስለዚህ ህብረተሰቡ አሁንም ቢሆን የሚያውቃቸውን ችግሮች ለይቶ በማቅረብ፣ ስራዎች በሚሰሩበትም ጊዜ በዕውቀቱም፣ በጉልበቱም፣ በገንዘቡም የበኩሉን በማድረግ ክረምቱን እጅ ለእጅ ተያይዘን እንሻገር በማለት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በቅርቡ ከከፍተኛ አመራሮች ጋር የ90 ቀናት ዕቅድ ዙሪያ ባደረጉት ውይይት በመጪው ክረምት በየትኛውም የመዲናዋ ክፍል የጎርፍ አደጋ እንዳይከሰት ጥብቅ መመሪያ ማስተላለፋቸው አይዘነጋም፡፡

# የምቹ ከተማ አረንጓዴ ጋሻ

- **የአዲስ አበባን የደን ሽፋን 30 በመቶ በማድረስ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት ዘንድሮም የተጠናከረ ስራ እንደሚከናወን ተጠቁሟል**

**በጊዜው አማረ**

የኢትዮጵያ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የአየር ንብረት ለውጥ፣ የደን መመናመን እና የውሃ እጥረትን የመሰሉ ስነ-ምህዳራዊ አደጋዎችን ለመከላከል እንዲሁም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተጀመረ ታሪካዊና ስትራቴጂካዊ ንቅናቄ ነው። ይህ መርሃ ግብር ከአካባቢ ጥበቃ ባለፈ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የኢኮኖሚና የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አንጻር ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶበት እየተሰራ ይገኛል። ከተለመዱት ጥላና የደን ዛፎች በተጨማሪ እንደ አቮካዶ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ፣ ቡናና ሻይ ያሉ የፍራፍሬና የሰብል ችግኞች በስፋት እየተተከሉ ይገኛሉ።

በሰባት ዓመታት ጉዞ ውስጥ በተከናወኑ ተከታታይ የችግኝ ተከላ ዘመቻዎች፣ በመላው አገሪቱ በአጠቃላይ ከ48 ቢሊዮን በላይ ችግኞች ተተክለዋል። የመርሃ ግብሩ ስኬት ችግኝ በመትከል ብቻ የተገደበ ሳይሆን፣ በተደረገው ቀጣይነት ያለው እንክብካቤና ክትትል የችግኞቹ የመጽደቅ ምጣኔ 84 በመቶ መድረስ ችሏል። ይህም ማለት ከተተከሉት መካከል ከ40 ቢሊዮን በላይ የሚሆኑት ችግኞች ጸድቀውና አድገው ኢትዮጵያን አረንጓዴ አልብሰዋታል። ይህ ከፍተኛ የመጽደቅ ስኬት የሚያሳየው፣ ንቅናቄው ከመትከል ባለፈ የተተከሉትን ጠብቆና ተንከብክቦ ለማሳደግ የተደረገውን የተቀናጀና ሳይንሳዊ የክትትል ስራ ውጤታማነቱን ነው።

ይህንን ተከትሎ በአገሪቱ የአካባቢ ጥበቃ ላይ አስደናቂና ታሪካዊ ለውጥ የተመዘገበ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ የደን ሽፋን ቀደም ሲል ከነበረበት የ3 በመቶ ደረጃ ተነስቶ አሁን ላይ 23 ነጥብ 6 በመቶ እንዲደርስ ማድረግ ተችሏል። ከዚህ ጎን ለጎን፣ በከፍተኛ ደረጃ ተራቁቶና ለምነቱን አጥቶ የነበረ ከ10 ሚሊዮን ሔክታር በላይ መሬት መልሶ እንዲያገግምና ወደ ቀድሞ ተፈጥሯዊ ይዘቱ እንዲመለስ ተደርጓል። ይህ የተፈጥሮ ሀብት መታደስ ለአፈርና ውሃ ጥበቃ፣ ለብዝሃ ሕይወት መበልጸግ እንዲሁም ለግብርናው ዘርፍ መጎልበት ያበረከተው አስተዋጽኦ እጅግ የላቀ ነው።

የኢትዮጵያ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ባለፉት ሰባት ዓመታት ያስመዘገባቸውን ውጤቶች መሰረት በማድረግ፣ ዘንድሮም በአዲስ መንፈስና በላቀ ቁርጠኝነት በይፋ ተጀምሯል። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቢሾፍቱ ከተማ ተገኝተው የዘንድሮውን ሀገራዊ የችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር በይፋ ያስጀመሩ ሲሆን፣ ይህም ንቅናቄው ወደ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገሩን ያበሰረ ሆኗል። ይህ በየዓመቱ የሚካሄደው አረንጓዴ አሻራ




ፎቶ፦ ከገፀ ድር

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዘንድሮው ሀገር አቀፍ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ማስጀመሪያ ላይ ችግኝ ሲተክሉ

በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመመከት እና ለአየር ንብረት የማይበገርን ምጣኔ ሀብት ለመገንባት ዋነኛ መሰረት ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

በዘንድሮው መርሃ ግብር በአገር አቀፍ ደረጃ 8 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ትልቅ ግብ የተቀመጠ ሲሆን፣ ይህ ዕቅድ አገሪቱ ቀደም ሲል ካስቀመጠችው አጠቃላይ የ65 ቢሊዮን ችግኞች ግብ ላይ ለመድረስ የምታደርገውን ጉዞ የሚያፋጥን ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚሁ ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት፣ ሀገሪቱ ያስቀመጠችውን የረጅም ጊዜ አረንጓዴ ትልም ለማሳካት በጽናት እየገሰገሰች መሆኗን ገልጸው፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ንቅናቄውን በንቃት እንዲቀላቀል ጥሪ አቅርበዋል። ይህ ግብ እንዲሳካ ችግኞችን ከመትከል ባለፈ፣ የተደራጀ የእንክብካቤና የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት የመጽደቅ ምጣኔውን ይበልጥ ለማሳደግ ከፍተኛ ዝግጅት ተደርጓል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ የዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር "ተስፋን መትከል" በሚል ጥልቅ ትርጉም ባለው መሪ ሀሳብ መጀመሩን ጠቁመው፣ ሀሳቡ የነገሩን ብሩህ ታሪክ ዛሬ በጋራ መጻፍን የሚያመላክት መሆኑን አስታውቀዋል።

ተስፋን መትከል ማለት የተስፋ ሥሮች ወደ ጥልቅ መሬት ገብተው ጠንካራ መሠረት እንዲይዙ፣ የብልጽግና ግንዶች ወደ ላይ ከፍ ብለው እንዲያድጉ እንዲሁም የብልጽግና ቅርንጫፎች ወደ ጎን እንዲንሰራፉ በማድረግ ከተከልነው ዛፍ የምንበላው እና የምንሸጠው ግዙፍ ሀብት እንዲኖር ማስቻል መሆኑን አብራርተዋል።

ተስፋ እጅግ በርካታ ትርጓሜዎች እንዳሉት የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተስፋ አረንጓዴ መቀነት በመሆን የገረጣን እና የነጣን ስፍራ በለምለም አረንጓዴ ልብስ የሚያለብስ መሆኑን ገልጸዋል። እንዲሁም ተስፋ አረንጓዴ ጸዳል በመሆን የተረበሸ ማንነትን በማከም መንፈስን የሚያድስ፣ ተፈጥሮ በውስጡ ደስታን እና የመረጋጋት ስሜትን የሚፈጥርበት ታላቅ ጉልበት እንደሆነም አስረድተዋል።

በዚህ ሀገራዊ የአረንጓዴ አሻራ ስኬትና ጉዞ ውስጥ የአዲስ አበባ ከተማ ድርሻም ከፍተኛ ነው፡፡ በእርግጥም በየዓመቱ የሚከናወነው የችግኝ ተከላ ንቅናቄ የከተማዋን ስነ-ምህዳር ከማስተካከል ባለፈ፣ የነዋሪዎቿን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትልቅ አቅም እየሆነ መጥቷል። በአዲስ አበባ ከተማ ባለፉት ዓመታት የተከናወነው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር፣ መዲናዋን ይበልጥ ውብ የማድረግ ጉዞ ምን ያህል ስኬታማና እያደገ የመጣ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል። በንቅናቄው በየዓመቱ እያደገ የመጣው የሚተከል ችግኝ ቁጥር፣ የነዋሪዎቿንና የአመራሩን ቁርጠኝነት የሚያንጸባርቅ ታሪካዊ ክንውን ሆኗል።

የዚህ ታላቅ ጉዞ መጀመሪያ በሆነው በ2011 ዓ.ም በመዲናዋ ከ6 ሚሊዮን በላይ ችግኞች በተሳካ ሁኔታ ተተክለው ነበር። ይህ መነሻ በቀጣዩ ዓመት ይበልጥ ተጠናክሮ በመቀጠሉ፣ በ2012 ዓ.ም የተተከሉት ችግኞች ቁጥር ከ8 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ከፍ ሊል ችሏል።

በ2013 ዓ.ም በተደረገው መጠነ-ሰፊ ርብርብ ከ11 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ወደ መትከል ተሻግሯል። በ2014 ዓ.ም ከ14 ነጥብ 7 ሚሊዮን በላይ እንዲሁም በ2015 ዓ.ም ከ17 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ መተከሉ ከተማዋን በአረንጓዴ የመሸፈን አቅም በየጊዜው እያደገ መምጣቱን አረጋግጧል።

በተለይም በ2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ታሪክ ታላቅ ስፍራ የሚሰጠው አፈጻጸም ተመዝግቧል። በወቅቱ በአንድ ጀምበርና በተለያዩ መርሃ-ግብሮች ከ27 ነጥብ 7 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል በመዲናዋ ትልቅና አዲስ ታሪክ ተሰርቷል። ይህ ክንውን የሕዝቡን ከፍተኛ ተሳትፎና የአረንጓዴ አሻራውን አስፈላጊነት በሚገባ የተረዳ ማኅበረሰብ መፈጠሩን ያሳየ ነው።

ይህንን ታላቅ ስኬት ተከትሎ፣ ባሳለፍነው ዓመት የአረንጓዴ አሻራው ንቅናቄ ሳይቋረጥ ቀጥሏል። በዚህም መሠረት ባለፈው ዓመት ከ4 ሚሊዮን በላይ ችግኞች በመዲናዋ የተለያዩ አካባቢዎች የተተከሉ ሲሆን፣ ይህም ቀደም ሲል የተተከሉትን የመንከባከብና አዳዲስ አረንጓዴ ቦታዎችን የመፍጠር ዘላቂ ግብ አካል ሆኖ ተከናውኗል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤም የአዲስ አበባን የደን ሽፋን 30 በመቶ የማድረስና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለማድረግ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት ዘንድሮም የተጠናከረ ስራ እንደሚከናወን አብራርተዋል፡፡ የዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ ስራ በተለይ ከኮፕ 32 ዓለም አቀፍ ጉባኤ ጋር ተያይዞ በስፋት እየተሰራበት መሆኑን የገለጹት ከንቲባ አዳነች፣ ለዚህም ዓላማ ብቻ ወደ 300 ሄክታር የሚጠጋ መሬት የተዘጋጀ መሆኑን አስረድተዋል።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ "ተስፋን እንትከል" በሚል እንደ ሀገር 8 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል የጀመርነው የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም ታሪካዊ ነው ሲሉ በማህበራዊ ሚዲያ ገጻቸው ላይ አስፍረዋል፡፡

በተጨማሪም በቀጣይ 90 ቀናት ዕቅድ ላይ ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት ዘንድሮም አረንጓዴ አሻራ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑን አንስተዋል። በየክፍለ ከተማው የችግኝ መትከያ ቦታዎች እንዲለዩ ከንቲባዋ ማሳሰቢያ ሰጥተዋል። ከተማዋ የአረንጓዴ ሽፋኗን 30 በመቶ በማድረስ ተወዳዳሪ ከተማ መሆን አለባት የሚለው ቁጭት በሁሉም ዘንድ መፈጠረ እንዳለበት የጠቀሱት ከንቲባ አዳነች፣ እስከዛሬ አቅደን ያላሳካነው የለም፡፡ የዘንድሮውን እቅድም ማሳካት እንችላለን ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ግርማ ሰይፉ በበኩላቸው ባለፉት ሰባት ዓመታት በመዲናዋ የተካሄደው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ትልቅ ለውጥ ማምጣቱን ጠቅሰዋል። ከሰባት ዓመታት በፊት አዲስ አበባ አረንጓዴ እንዳልነበረች እና ዝቅተኛ የደን ሽፋን እንደነበራት በማስታወስ ባለፉት ሰባት ዓመታት አስደናቂ ስራዎች መሰራታቸውን ገልጸዋል፡፡ በዚህም የከተማው የአረንጓዴ ሽፋን ከ3 በመቶ በታች የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን ከ22 በመቶ በላይ ነው፡፡ አጠቃላይ ግቡም

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# የትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ ምን ውጤት አመጣ?

- ‘ንቅናቄው’ በትብብርና በቅንጅት ከተሰራበት የትምህርት ጥራትን ዘላቂ በሆነ መልኩ ማሻሻል እንደሚቻል አመላክቷል

**በቶለሳ መብራቴ**

ዕድሜዋ ገና 15 ቢሆንም በዐይኖቿ ውስጥ ትልቅ ራዕይና ተስፋ ይንጸባረቃል፤ ስሟ ሳሮን ተሾመ ይባላል፤ መገኛው የካ ክፍለ ከተማ በሆነው የህብረት ፍሬ አንደኛ ደረጃና ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ8ኛ ክፍል ተማሪ ናት። ሳሮን ዛሬ ላይ ቆማ የትናንቱን የትምህርት ቤቷን ገጽታ ስታስታውስ፣ በትምህርት ጉዞዋ ላይ ጥሎት የነበረው ጥላ በቀላሉ የሚረሳ አይደለም። በቂ የመማሪያ ክፍሎች የሌሉበት፣ በቂ ቤተ መጻሕፍትና የንድፈ ሀሳብ ትምህርቷን በተግባር የምታይበት ቤተ ሙከራ ያልተሟላለት ያ ትምህርት ቤት፣ በእሷና በጓደኞቿ የትምህርት አቀባበል ላይ ትልቅ ውስንነት ፈጥሮባቸው እንደነበር ታስታውሳለች።



ፎቶ- ከፋይል
‘ትምህርት ለትውልድ’ ንቅናቄ የትምህርት ቤቶችን ቅጥር ግቢ ምቹና ሳቢ በማድረግ በተማሪዎች የእውቀት አቀባበል ላይ መሻሻል አምጥቷል

ያ የዕውቀት ረሀብ ዘመን ግን እንደቀጠለ አልቀረም፤ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በመላው የአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ የተዘረጋውና በሳሮን ትምህርት ቤትም የተተገበረው የ‘ትምህርት ለትውልድ’ መርሃ ግብር፣ በታሪካቸው አዲስ ደማቅ ብርሃን ይዞ ብቅ አለ። ይህ ታላቅ ንቅናቄ የትምህርት ቤቱን ነባር ውስንነቶች አንድ በአንድ እየፈታ፣ የቆዩ ክፍተቶችን በማቃለልና መሰረተ ልማቶችን በማሟላት የትምህርት ቤቱን ገጽታ ቀየረው። ትምህርት ቤቱ ከአሮጌ ገጽታው ተላቅቆ፣ ለልጆች አእምሮ መጎልበትና ለትውልድ መቅረጫነት የሚመጥን ዘመናዊና ምቹ ቁመናና ገፅታን ለመጎናጸፍ በቃ።

አሁን ብዙዎቹ የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቤቶች ቅጥር ግቢ ለመማር ማስተማር ሂደቱ ምቹና ሳቢ ሆነዋል። ተማሪዎች አካላቸውን የሚያጠናክሩበት ሰፊ የስፖርት ሜዳዎች፣ አእምሮን የሚያድሱ አረንጓዴ ስፍራዎች እንዲሁም የጤና አጠባበቅን ባህል የሚያሳድጉ ንጹሕ የእጅ መታጠቢያ ቦታዎች ተዘጋጅተዋል። ተማሪዎች በደስታና ምቾት ተቀምጠው የሚመገቡበት ምቹና ሰፊ የምሳ መመገቢያ አዳራሾችም ተገንብተዋል፡፡

ይህ ሁሉ ለውጥ በሳሮን የትምህርት አቀባበል ላይ የፈጠረው ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። “ሁሌ ማለዳ ከእንቅልፌ ስነቃ ትምህርት ቤቴን በመናፈቅና ለመድረስ በመጓጓት ነው የምነሳው” ስትል ትናገራለች።

የሳሮን ታሪክ የአንድ ተማሪ የግል ስኬት ብቻ ሳይሆን፣ በትምህርት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት በትውልድ ላይ እንዴት ትልቅ ለውጥ ማምጣት እንደሚችል የሚያሳይ ህያው ማረጋገጫ ነው። የህብረት ፍሬ አንደኛ ደረጃና ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አዲስ ገጽታና የሳሮን ውጤታማነት፣ የ‘ትምህርት ለትውልድ’ መርሃ ግብር የከተማዋን አዳጊዎች ተስፋ እንዴት እያለመለመ መሆኑን የሚያሳይ ትልቅ ማሳያ ነው።

በተመሳሳይ የዚሁ የህብረት ፍሬ ትምህርት ቤት የ8ኛ ክፍል ተማሪ ኃይለመለኮት ፀጋዬ በትምህርት ቤቱ የተደረጉት ሁለንተናዊ ማሻሻያዎች ተማሪዎችን ከንድፈ ሀሳብ ባለፈ በተግባር እንዲማሩ ሰፊ ዕድል እንደፈጠሩላቸው በኩራት ይናገራል። የትምህርት ቤቱን ነባር ሁናቴ ከአምናና ከካቻምናው ጋር እያነጻጸረ የዘንድሮውን እምርታ ሲመሰክር “በአሁኑ ወቅት በትምህርት ቤታችን የተሟሉት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) ክፍሎች እኛ ተማሪዎች እውቀትን በእጃችን እየነካንና ራሳችን እየሞከርን እንድንማር አድርገውናል” ይላል።

ቀደም ሲል በነበረው እጥረት ምክንያት እስከ 10 የሚደርሱ ተማሪዎች በአንድ ኮምፒውተር ላይ ተጨናንቀው በቡድን ለመስራት ይገደዱ እንደነበር የሚያስታውሰው አዳጊው፣ ይህም ሁኔታ እያንዳንዱ ተማሪ በትክክል ተሳትፎ እንዳያደርግና አቅሙን እንዳያሳድግ ትልቅ ጋሬጣ ሆኖባቸው እንደቆየ አይሸሽግም። አሁን ግን ያ ታሪክ ተቀይሮ ተማሪዎች በግል ወይም ቢበዛ ለሁለት ሆነው በተመቻቸው ሁኔታ ስለሚማሩ፣ የራሳቸውን የፈጠራ ሀሳብ በነፃነት ለማቅረብና የተደበቀ ችሎታቸውን በተግባር ለማሳየት ችለዋል።

ተማሪ ኃይለመለኮት “በኮምፒውተር ክፍል ውስጥ አሁን እያንዳንዱ ተማሪ የራሱን ስራ ራሱ ነው የሚሰራው፤ የሌላ ተማሪን ሀሳብ መገልበጥና ጥገኝነት የለም። ይህ ደግሞ የልጆችን የፈጠራ ተነሳሽነት በከፍተኛ ደረጃ ያበረታታል” ይላል።

የህብረት ፍሬ አንደኛና ቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አብዲሳ ኦብሳ እንደሚገልጹት፤ ትምህርት ቤቱን ለመማር-ማስተማር ምቹ ለማድረግ ከማህበረሰቡ፣ ከወላጆች፣ ከተለያዩ ድርጅቶችና ከበጎ አድራጎት ተቋማት ጋር በመቀናጀት በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል።

በተለይ በኢትዮጵያና በደቡብ ኮሪያ መካከል ከሚሰሩ አካላት ጋር በተደረገ ትብብርና በቀረበ ፕሮፖዛል፤ 30 ታብሌቶች፣ ስማርት ቦርድ፣ 30 ወንበሮች፣ 5 ጠረጴዛዎች፣ የዋይፋይ አገልግሎት እና የታብሌት ማስቀመጫ ሼልፍ ሊገኝ ችሏል። ይህ የቴክኖሎጂ ድጋፍ የመማሪያ ክፍሎች እድሳት መደረጉ ታክሎበት በትምህርት ቤቱ ውጤት ላይ ትልቅ መነቃቃትን ፈጥሯል ብለዋል፡፡

> **“በትምህርት ቤቶች ውስጥ የተፈጠረው ምቹና ሳቢ የመማሪያ አካባቢ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ውጤት ከፍ እንዲል ያደረገ ሲሆን፣ የክፍል ማለፍ ምጣኔም ከዓመት ዓመት እየተሻሻለ መጥቷል”**

እንደ ርዕሰ መምህሩ ማብራሪያ፣ በ2014 እና በ2016 ዓ.ም የነበሩ የትምህርት ክፍተቶች በእጅጉ ተቀንሰዋል። “በ2017 ዓ.ም የትምህርት ቤቱን የውጤት ትንተና ስናደርግ በተማሪዎች ውጤትና ከክፍል ማለፍያ ምጣኔ ላይ የ17 በመቶ ጭማሪ አሳይቶናል። ይህ በአጋጣሚ የመጣ ሳይሆን ተማሪዎች በአይሲቲ ታግዘው በተግባር ስለሚማሩ እና ከፍተኛ ተነሳሽነት በመፈጠሩ የመጣ ለውጥ ነው” ይላሉ ርዕሰ መምህር አብዲሳ።

በ‘ትምህርት ለትውልድ’ ንቅናቄ ማዕቀፍ ውስጥ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ የሚገኘው የደጃዝማች ወንድራድ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ካሱ ቱምሳ ተቋሙን ሳቢና ምቹ ለማድረግ የተሰሩ ስራዎችን በዝርዝር አስረድተዋል። በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተማሪዎች መናፈሻ፣ የመንገድ ዳር ከርቮች፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የመጸዳጃ ቤቶችና አዲስ የህጻናት ማቆያ (ዴይ ኬር) ተገንብተዋል። የዲጂታል ቤተ-መጻሕፍትን የማስዋብና የማደራጀት ስራዎች በትኩረት ተከናውነዋል።

ትምህርት ቤቱ ካስመዘገባቸው ትልልቅ ድሎች መካከል አንዱ የተማሪና የክፍል ጥምርታን በከፍተኛ ሁኔታ መቀነሱ ነው። ከንቅናቄው በፊት በትምህርት ቤቱ የነበረው የተማሪና ክፍል ጥምርታ 1 ለ73 የነበረ ሲሆን፣ አሁን 1 ለ42 ሆኗል። ይህ የክፍል ጥምርታ መሻሻል ሊመዘገብ የቻለው በንቅናቄው በተገነባው አዲስ ህንፃ አማካኝነት ሲሆን፣ ይህም የሀገሪቱን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መደበኛ ስታንዳርድ (1 ለ 40) በእጅጉ የተቃረበ መሆኑን ርዕሰ መምህሩ ገልጸዋል።

የትምህርት ቤቱ ቤተ-መጻሕፍት ዘመናዊ አደረጃጀት እንዲኖረው መደረጉን ተከትሎ፣ ተማሪዎች ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ በሳምንት 7 ቀን የ24 ሰዓት ሙሉ አገልግሎት እያገኙ ይገኛሉ። ይህ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ከመጨመሩም በላይ፣ መምህራን የስራ ቦታ ምቾት እንዲሰማቸው በማድረጉ ካሁን ቀደም የነበረውን ከፍተኛ የዝውውር ጥያቄ በከፍተኛ ሁኔታ ሊቀንሰው ችሏል።

የ‘ትምህርት ለትውልድ’ ንቅናቄ በትብብርና በቅንጅት ከተሰራ የትምህርት ጥራትን ዘላቂ በሆነ መልኩ ማሻሻል እንደሚቻል በተግባር ያሳየ ደማቅ ስኬት ሆኖ ተመዝግቧል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ እንደገለጹት፣ በከተማዋ እየተተገበረ ላለው “የትምህርት ለትውልድ” ንቅናቄ የቀድሞ ተማሪዎችን፣ ባለሀብቶችን፣ በጎ አድራጊዎችንና መላውን ማኅበረሰብ በማስተባበር በ2018 በጀት ዓመት ብቻ ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ ሀብት በመሰብሰብ ትምህርት ቤቶችን ማጠናከር ላይ ውሏል።

ንቅናቄው ከደረጃ በታች የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን ደረጃ በማሳደግ፣ አዳዲስ የመማሪያ ክፍሎችንና መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋት እንዲሁም የትምህርት ግብዓቶችን በማሟላትን ረገድ ጉልህ መሻሻል አስገኝቷል፡፡ በትምህርት ጥራትና በተማሪዎች ውጤት ላይም ተጨባጭ ለውጥ አስመዝግቧል። ቀደም ሲል “ደረጃ 1” እና “ደረጃ 2” በሚባሉ ዝቅተኛ ደረጃዎች የነበሩ በርካታ ትምህርት ቤቶች ወደ “ደረጃ 3” ማደግ የቻሉ ሲሆን፣ ወደ “ደረጃ 4” ለማሸጋገር የተጠናከረ ስራ እየተካሄደ ነው።

በትምህርት ቤቶች ውስጥ የተፈጠረው ምቹና ሳቢ የመማሪያ አካባቢ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ውጤት ከፍ እንዲል ያደረገ ሲሆን፣ የክፍል ማለፍ ምጣኔም ከዓመት ዓመት እየተሻሻለ መምጣቱን ምክትል ቢሮ ኃላፊው ጠቁመዋል።

በ‘ትምህርት ለትውልድ’ ንቅናቄ በሀገር አቀፍ ደረጃ 7 ሺህ 923 አዳዲስ ትምህርት ቤቶች መገንባታቸው፣ ለ31 ሺህ 252 ነባር ትምህርት ቤቶች እድሳትና ጥገና እንደተደረገላቸው ከትምህርት ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡ በንቅናቄው 5 ሺህ 957 አዳዲስ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ አንድ ሺህ 862 አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና 268 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገንብተዋል። 22 ሺህ 146 አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ ታድሰዋል።

# ከስጋት ስፍራነት ወደ መዝናኛ ማዕከልነት

- **18 ሄክታር የሚሸፍን ሰፊ የወንዝ ዳርቻ ልማት በበሻሌ ወንዝ ላይ ተከናውኗል**





ፎቶ- ከፋይል
የለሚ የወንዝ ዳርቻ የቀደመ ገፅታ



ፎቶ- ከገፀ ድር
የወንዝ ዳርቻው አሁናዊ ገፅታ

**በስንታየሁ ምትኩ**

የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ነዋሪው አቶ ፍቃዱ ዘውዴ የበሻሌ ወንዝን ድሮ ሲያውቁት በጥሻ የተሸፈነና የእርሻ ሥራ ይከናወንበት የነበረ ስፍራ እንደነበር ያስታውሳሉ፤ ወንዙም ንጹሕ ስለነበር ለመጠጥነት ያገለግል ነበር። በሂደት ግን የላይኛው ተፋሰስ በተለይም በመሪ አካባቢ የሰዎች መስፈር መጀመርና ከግንባታዎች መስፋፋት ጋር ተያይዞ፣ የመኖሪያ ቤቶችና ተቋማት የፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻን ወደ ወንዙ መልቀቅ ጀመሩ። ይህም ወንዙ ተፈጥሯዊ ይዘቱን አጥቶ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲበከል እንዳደረገው ተናግረዋል።

በዚሁ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 “እንዶዲ” እየተባለ በሚጠራ ቀጣና የሚኖሩት አቶ አዱኛ ባልቻ እንዲሁ፣ ወንዙ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ብቻ ሳይሆን የሞቱ እንስሳት ጭምር የሚጣልበት እንደነበር ይገልጻሉ። ከወንዙ የሚወጣው መጥፎ ሽታ ሰዎች በአካባቢው ለማለፍ እንኳ እንዲቸገሩ ያደርጋቸዋል። ከዋናው ድልድይ ውጪ ሌላ አማራጭ መሸጋገሪያ ባለመኖሩ ሳቢያም፣ አልፎ አልፎ በመጠጥና በተለያየ ምክንያት ሰዎች ከወንዙ እየወደቁ የሚሞቱበት አሳዛኝ ክስተት ይፈጠር ነበር። በተለይ ከምሽት በኋላ አካባቢውን አቋርጦ ማለፍ ፍጹም አስፈሪ ነበር።

የአካባቢው ነዋሪዎች አቶ ሃይማኖት በላይ እና ወጣት መስፍን ግርማ እንደሚያክሉት፣ ስፍራው በእሾሃማ ዕፅዋትና በጥሻ የተሸፈነ በመሆኑ፣ ለቀማኞችና ለዘራፊዎች ምቹ መሸሸጊያ ሆኖ ለረጅም ዓመታት ለአካባቢው ነዋሪዎች የስጋት ቀጣና ሆኖ ቆይቷል፡፡

ዛሬ በ72 ድልድይ አካባቢ ያለው የበሻሌ ወንዝ አስፈሪና ቆሻሻ ገጽታ ታሪክ ሆኗል። አቶ አዱኛ በወንዝ ዳርቻ ልማቱ የመጣውን ለውጥ በማድነቅ፣ “አሁን ወንዙ እንደገና ተፈጥሯል ማለት ይቻላል፤ በጣም ትልቅ ለውጥ ነው ያለው። አካባቢው ፀድቶ ወደ ውብ መዝናኛ ማዕከልነት ተቀይሯል። በአሁኑ ወቅት የወንዝ ዳርቻው ከጨለማ ወጥቶ በዘመናዊ መብራቶች ብርሃናማ ሆኗል። አካባቢው አረንጓዴ ሽማ ለብሶ፣ የእግረኛና የሳይክል መንገዶች አካፋዮች መሀልና ዳርቻዎች በተለያዩ ማራኪ አበቦችና ዕፅዋት ተሸልመዋል” ብለዋል።

የለሚ የወንዝ ዳርቻ ፓርክ ከተፈጥሮ ጋር በተሰናሰለ መልኩ የተገነባ፣ ነፋሻማ አየርና ድንቅ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ ያለው በመሆኑ ለነዋሪው ተመራጭ የጊዜ ማሳለፊያ ሆኗል። ማራኪ ቅርፅ ያላቸው በርካታ የእግረኛ መሸጋገሪያ ድልድዮች፣ ለዕረፍት የሚሆኑ ምቹ ማረፊያ ወንበሮች፣ የልጆች መጫወቻ ስፍራዎች፣ አነስተኛ የእግር ኳስ ሜዳ እና ዘመናዊ ካፌዎች፣ አምፊቴአትርና ሌሎችን በማካተት ተገንብቷል፡፡ የአካባቢው ነዋሪ አቶ ሃይማኖት “በእረፍት ጊዜያችን ከልጆቻችን ጋር በመምጣት የምንጫወትበትና የምንዝናናበት ዕድል በመፈጠሩ እጅግ ደስተኞች ነን” ሲሉ የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል።

ፕሮጀክቱ የአካባቢውን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ፣ ለወጣቶችም የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል። ቀደም ሲል በቀን ሥራ ይተዳደር የነበረው ወጣት መስፍን ግርማ ከእነዚህ መካከል አንዱ ነው፡፡ የልማት ሥራው ከተጀመረበት ካለፈው አንድ ዓመት ጀምሮ በፓርኩ ውስጥ ሳሮችንና አበባዎችን በመትከልና በመንከባከብ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ይገኛል። ወጣት መስፍን አካባቢው ውብና ፅዱ ሆኖ መልማቱ ብቻ ሳይሆን፣ ለእርሱም የተሻለ የሥራ ዕድል እንዲያገኝ ዕድል የፈጠረለት በመሆኑ ደስተኛ መሆኑን ለዝግጅት ክፍላችን ገልጿል፡፡

የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋዬ አያና ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ማብራሪያ፣ የአካባቢውን አስከፊ ገጽታ ሙሉ በሙሉ ለመቀየር፣ የሚፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶችን ለማስወገድና ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ በማለም 18 ሄክታር የሚሸፍን ሰፊ የወንዝ ዳርቻ ልማት በበሻሌ ወንዝ ላይ መካሄዱን አብራርተዋል፡፡

“ይህ ፕሮጀክት ማኅበረሰቡን ከነበረበት የጤናና የወንጀል ስጋት አውጥቶ፣ በንፁህና ለመዝናኛ ምቹ በሆነ አካባቢ እንዲኖር ትልቅ ዕድል ፈጥሯል” የሚሉት አቶ ተስፋዬ፤ በአጠቃላይ የለሚ የወንዝ ዳርቻ ፓርክ የወንዝ ዳርቻው ብቻ 5 ነጥብ 2 ኪሎ ሜትር ይሸፍናል።

> **“አሁን ወንዙ እንደገና ተፈጥሯል ማለት ይቻላል፤ በጣም ትልቅ ለውጥ ነው ያለው። አካባቢው ፀድቶ ወደ ውብ መዝናኛ ማዕከልነት ተቀይሯል**

በወንዙ ዳርቻ ላይ አዳዲስ ስድስት ድልድዮች የተገነቡ ሲሆን፣ ይህም ነዋሪዎች ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላው በቀላሉ እንዲንቀሳቀሱና በወረዳ አምስት እና ወረዳ አስር እንዲገናኙ አስችሏል።

የለሚ የወንዝ ዳርቻ ፓርክ አካባቢውን ለመኖሪያና ለመዝናኛነት እጅግ ተመራጭ የሚያደርጉ በርካታ ዘመናዊ አገልግሎቶችን በውስጡ አካትቶ ይዟል፡፡ ለስፖርትና ጤናማ ሕይወትን ለመምራት የሚያግዙ የእግረኛና የሳይክል መንገዶች፣ የቤት ውስጥና የቤት ውጪ ስፖርታዊ መጫወቻ ስፍራዎች፣ እንዲሁም አነስተኛ የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ (ፉትሳል)፣ አምፊቴአትር፣ ዘመናዊ ካፌዎች፣ ሰው ሠራሽ ፏፏቴዎችና ውብ ድልድዮች እንዲሁም ለዓይን ማራኪ የሆኑ ሰፊ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ የተለያዩ ዕፅዋትና አትክልቶች ያሉበት ነው፡፡

ይህ ግዙፍ የልማት ሥራ የአካባቢውን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ በርካታ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ይዞ መጥቷል። ቀደም ሲል ነዋሪዎች ምሽት ላይ መሄድ የሚፈሩት ስፍራ፣ አሁን ላይ ወደ ማታ አካባቢ ከቤተሰቦቻቸው ጋር በነፃነት የሚንቀሳቀሱበት፣ የሚዝናኑበትና ስፖርት የሚሰሩበት አስተማማኝና ማራኪ ቦታ ሆኗል።

ከዚህ በተጨማሪም፣ በፓርኩ ግንባታ ወቅት እንዲሁም በአሁኑ ወቅት የፓርኩን ዕፅዋትና አትክልቶች በመንከባከብ ሥራ ላይ ለተሰማሩ በርካታ የአካባቢው ወጣቶችና ነዋሪዎች ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን አቶ ተስፋዬ አብራርተዋል። ፕሮጀክቱ የወንዝ ዳርቻዎችን ወደ ልማትና ውበት በመቀየር ረገድ ለሌሎች አካባቢዎችም አርአያ የሆነ ትልቅ ስኬት እንደሆነ የተናገሩት አቶ ተስፋዬ፣ ፓርኩ በሕዝብ መዝናኛ ቦታዎች አስተዳደር ኮርፖሬሽን ሥር ሆኖ አገልግሎት እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ከሁለት ሳምንት በፊት የለሚ የወንዝ ዳርቻ ፓርክን መርቀው መክፈታቸው ይታወሳል። ከንቲባዋ በይፋዊ የማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት፤ ፓርኩ የእግረኛና የብስክሌት መንገዶችን፣ ድልድዮችን፣ የተለያዩ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን እንዲሁም የሕፃናት መጫወቻ፣ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ የአትክልት አጸዶች፣ ካፌዎች፣ አንፊቴአትር ቤቶች እና ልዩ ልዩ መናፈሻዎችን ጨምሮ በርካታ አገልግሎቶችን የሚሰጡ መሠረተ ልማቶች ያካተተ ነው፡፡ ይህም በከተማዋ የሚገነቡ ፕሮጀክቶች አካታችና ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል እንደ ፍላጎቱ ሊጠቀምባቸው የሚችልባቸው እንደሆኑ ያመለክታል፡፡

በተለምዶ “72 ድልድይ” እየተባለ በሚጠራውና ከጎሮ ወደ አያት፣ አራብሳና ጣፎ በሚወስደው ዋናው የመተላለፊያ መስመር ላይ የሚገኘው የበሻሌ ወንዝ፤ ዛሬ ንፁህ ሆኖ ይፈስሳል። ቀድሞ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# “ሰልጣኞቹ ‘ከስልጠና በኋላ የት ደረሱ?’ በሚል ቅኝትና ክትትል ይደረጋል”

ለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል ዳይሬክተር ሂርጳሳ ጫላ (ዶ/ር)

- ለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል በአራት ዙር 2 ሺህ 400 ሴቶችን አሰልጥኖ ወደ ስራ እንዲገቡ አድርጓል

በሄለን ጥላሁን

አንዳንድ የሕይወት መልኮች ነጋችን የጨፈገገ መስሎ እንዲሰማን፣ ተስፋም እንድንቆርጥ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ለዚህ በ“ለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል” እየገቡ እንዲሰለጥኑ እየተደረጉ ያሉ ሴቶችን ታሪክ በሁነኛ አስረጅነት መጥቀስ በቂ ነው፡፡ ለተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮችና ዘርፈ ብዙ ምስቅልቅሎች እንዳለፉና ሕይወት መራር ጽዋዋን እንድትጎነጭ እንዳደረገቻቸው ከባለታሪኮቹ አፍ የሚወጡ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

እኛም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በዚህ የሕይወት መንገድ እያለፉ ያሉ ሴቶች መስመራቸው የተቃና፣ ነጋቸውም ብሩህ ይሆን ዘንድ ምን እየሠራ እንደሆነ ማብራሪያ ይሰጡን ዘንድ ከማዕከሉ ዳይሬክተር ሂርጳሳ ጫላ (ዶ/ር) ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡ መልካም ንባብ፡፡



ፎቶ- ከፋይል

የማዕከሉ ሰልጣኞች የልብስ ስፌት ስልጠና በወሰዱበት ወቅት



ፎቶ፡- ከፋይል

ለነገዋ የሴቶች የተሃድና ክህሎት ማበልፀጊየ ማዕከል ዳይሬክተር ሄርጳሳ ጫላ (ዶ/ር)

**አዲስ ልሳን ጋዜጣ፡-** ቃለ መጠይቁን ለማድረግ ፈቃደኛ ስለሆኑ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን፡፡

**ሂርጳሳ ጫላ (ዶ/ር)፡-** እኔም እንግዳችሁ ስላደረጋችሁኝ አመሰግናለሁ።

**አዲስ ልሳን ጋዜጣ፡-** ማዕከሉ ከተመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ በተለያየ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ተያያዥ ቀውስ ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች ጥላ በመሆን ረገድ እየሠራ ስላለው ሥራ ቢያብራሩልን?

**ሂርጳሳ ጫላ (ዶ/ር)፡-** ማዕከሉ የመጣበትን ሂደት የተመለከትን እንደሆነ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ሐሳብ አመንጪነት ተመሥርቷል፡፡ የማኅበረሰባችን ግማሽ አካል የሆኑት ሴቶች በብዙ ውጣ ውረድ ማለፋቸውን ተከትሎ ትንሽ ቢደገፉ ሕይወታቸው ሊቀየር የሚችልበት ዕድል ሰፊ መሆኑን በመረዳት ከተማ አስተዳደሩ በልዩ ትኩረት ከማዕከሉ ግንባታ እስከ ተጠቃሚነት የደረሰውን ሂደት እየተከታተለ ይገኛል፡፡

እነዚህን ሴቶች መደገፍ ብሎም ካሉበት ችግር እንዲወጡ ማድረግ ያለው እርካታ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ “እንዲህ ቢሆንላቸው” ብሎ ተስፈኛ ምኞት መመኘት ብቻ በቂ አይደለም፡፡ መሬት ላይ የወረደ ሥራ መሥራት፣ ያለባቸው ችግር ምንድን ነው? መፍትሔውስ ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የከተማ አስተዳደሩ ሴቷን ካለችበት የተለያየ ማኅበራዊ ቀውስ በማውጣት ነገዋን ማስጌጥ እና ተስፋ እንድታደርግ የማስቻል ራዕይን ሰንቆ እየሠራ ይገኛል፡፡ እኔም የዚህ የተቀደሰ መርሐ ግብር አካል በመሆኔ እጅግ አስደስቶኛል፡፡ የሚታይ ለውጥ፣ የሚዳሰስ እውነታ ያለው ሥራ መሥራት የልብ ደስታን ያጎናጽፋል፡፡

በማዕከላችን እየሰጠነው ያለው አገልግሎት ችላ የማይባል ብሎም ለነገ በይደር የምናቆየው አይደለም፡፡ ይልቁንም ትናንት አስከፊ የሆነ የሕይወት ቁስል ተሸክማ ለሕመሟ መድኃኒት ለምትሻ ሴት “ደርሰንልሻል፤ ጆሮ ሰጥተንሻል፤ የሚረዳሽ አካል በብዙ ሊደግፍሽ የጸና አቋም ይዟል” በማለት እጃችንን ዘርግተን እየተቀበልን እንገኛለን፡፡

**አዲስ ልሳን ጋዜጣ፡-** ማዕከሉ በተለያዩ ዙሮች ሰልጣኞችን አሰልጥኖ አስመርቋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተገኘውን ውጤት እንዴት ያብራሩታል?

**ሂርጳሳ ጫላ (ዶ/ር)፡-** ማዕከሉ በዚህ ሁለት ዓመት ውስጥ የሰው ልጆችን ክብር በሚመጥን ቦታ ላይ እንዲደርሱ፣ ከወደቁበት እንዲነሡ፣ ከነበሩበት ማኅበራዊ ቀውስ ተላቅቀው ወደ ሥራው ዓለም እንዲገቡ የማስቻል ሥራ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ በተለያዩ ዙሮች ሰልጣኞችን በማሰልጠን ረገድ ከተማ አስተዳደሩ የሰው ተኮር ፕሮጀክትን የሚቀርጸው የሰው ልጆች ሕይወታቸውን እንዲቀይሩ ለማስቻል በማሰብ ነው። የሚደረግላቸው ድጋፍ በዋናነት የምግብ፣ የአልባሳት፣ የመኝታ፣ የንጽህና መጠበቂያ፣ የጤና፣ የስፖርት እንዲሁም የተሃድሶ እና የሙያ ሥልጠናዎችን ተቋሙ በጀት በመበጀት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

እስካሁን ድረስ በአራት ዙር ቁጥራቸው 2 ሺህ 400 የሚሆኑ ሴቶችን አሰልጥኖ ወደ ሥራ እንዲገቡ አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ አግባቦች ሲደገፉ የነበሩት ፍሬያቸው ከምን ደረሰ ብሎ ማዕከሉ በየወሩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል። በተስፋ መቁረጥ ውስጥ የነበሩት በልፋታቸው እና በላባቸው ራሳቸውን የቻሉበት፣ ከጥገኝነት የተላቀቁበት እንዲሁም ቀጥረው የሚያሠሩበት አግባብ መኖሩን አስተውያለሁ፡፡ ከነበረባቸው የተለያዩ ሥነ ልቦናዊ ጉዳት ተላቅቀው “እኔ መሥራት እችላለሁ፤ ለማኅበረሰቡ የማበረክተው አስተዋጽኦ አለ” የሚል አስተሳሰብ መፍጠር ተችሏል፡፡ በራሷ የምትተማመን ሴት ለምታፈራው ትውልድ ጭምር የኩራት ምንጭ ናት፡፡

**አዲስ ልሳን ጋዜጣ፡-** ሴቶችን ማብቃትና ከነበሩበት ማኅበራዊ ቀውስ እንዲላቀቁ ማድረግ እንደ አገር ያለውን አንድምታ እንዴት ያዩታል?

**ሂርጳሳ ጫላ (ዶ/ር)፡-** ሴቶች በተፈጥሮ የተቸሩት ጸጋ ልጆችን በማኅፀናቸው ከመያዛቸው ባሻገር የእናትነትን ርኅራኄ ጭምር ከፈጣሪ ተችረዋል፡፡ ሴቶችን ከጎዳና ላይ እንዲነሡ ማድረግ ጤናማ ልጆች እንዲወለዱ እንደማስቻል ነው። በተለይም የበሽታ ስርጭት እንዲቀንስ ከማድረግ አንጻር ጠቀሜታው የላቀ ነው። ከነበሩበት ማኅበራዊ ቀውስ እንዲላቀቁ በማስቻል ወንጀል እንዲቀንስ ማድረግ ይቻላል፡፡ ለሀገር የሚያስብና የሚሠራ ዜጋን ማፍራትን ያረጋግጣል፡፡ በየጎዳናው ላይ የበዛ ችግረኛ ሰዎችን ከማየት ይልቅ በየጎዳናው የሚሠሩትን ማየት የሀገርን ገጽታ ብሎም ክብር ከማስጠበቅ አንጻር ትርጉሙ የላቀ ነው፡፡ በሴቶች ላይ መሥራት፣ በተለያየ ማኅበራዊ ቀውስ ውስጥ ያሉትን መደገፍና መርዳት የሀገርን ዕድገትና ብልጽግና ማረጋገጥ ማለት ነው።

**አዲስ ልሳን ጋዜጣ፡-** ሥልጠናውን ካጠናቀቁ በኋላ መልሰው ወደነበሩበት ሕይወት እንዳይገቡ በማዕከሉ በኩል ምን እየተሠራ ይገኛል?

**ሂርጳሳ ጫላ (ዶ/ር)፡-** ሰልጣኞች በማዕከሉ ውስጥ ለ6 ወራት ያህል ቆይታ ያደርጋሉ፡፡ ሥልጠናቸውን ከጨረሱ በኋላም በተለያዩ መንገዶች ክትትል ይደረግላቸዋል፡፡ የማዕከሉ አመራሮች በየደረጃው ከሚገኙ መንግሥታዊ ተቋማት ጋር ቀጥታ ግንኙነት አለን። ቅንጅታዊ አሠራሮች ተዘርግተዋል፡፡ ከፍተኛ አመራሮች ባሉበት ይገመገማል። “የገጠሙ አስተዳደራዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምንድን ናቸው?” በሚል ግምገማና ግብረ መልስ ይሰጣል። ከሥነ አእምሮ እንዲሁም ከሥነ ምግባር አንጻር 26 አባላት ያለው የማዕከሉ ካውንስል ክትትል፣ ድጋፍና ምክክር ያደርጋል፤ እንዲሁም በወር አንዴ “ሴቶቹ ከሥልጠና በኋላ የት ደረሱ?” በሚል ቅኝትና ክትትል ይደረጋል፡፡

በተለያየ ማኅበራዊ ቀውስ ውስጥ የሚገኙ ሰልጣኞች ሥልጠናቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከፋይናንስ ጋር በተያያዘ ለሚገጥማቸው ችግር ማዕከሉ መፍትሔ እያስቀመጠ ይሄዳል፡፡ ከባለሀብት፣ ከግለሰቦች እንዲሁም ከተቋማት ጋር ትስስር ፈጥረው እንዲሠሩ የሚደረግበት አግባብ አለ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ ጤና ቢሮ፣ ሥራ እና ክህሎት ቢሮ፣ የመሥሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ፣ የትምህርት ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ ባለሀብቶች እና የአካባቢው ማኅበረሰብ ከእኛ ባለድርሻ አካላት መካከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡

**አዲስ ልሳን ጋዜጣ፡-** የተለያዩ ማኅበራዊ ኃላፊነቶችን ከመወጣት አንጻር የግለሰቦች ብሎም የባለሀብቶች ሚና ምን መሆን አለበት ይላሉ?

**ሂርጳሳ ጫላ (ዶ/ር)፡-** ማዕከሉ እንደ ሀገራችን ብቻ ሳይሆን እንደ አፍሪካም የመጀመሪያ ነው፡፡ ሥራው መጠነ ሰፊ መሆኑን ተከትሎ እስካሁን ድረስ በመንግሥት በጀትና ድጋፍ የቀጠለ ተግባር ነው፡፡ ታዲያ እንደነዚህ ያሉ ማኅበራዊ ኃላፊነቶች መንግሥት ብቻውን የሚወጣቸው አይደሉም። ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ባለድርሻ ሊሆን ይገባል፡፡ ሴቶችን መንከባከብ ትውልድን አርቆ እንደማስቀጠል ነው። መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጭምር በስፋት መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ “ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ነው፣ ለሃምሳ ሰው ግን ጌጡ ነው” እንደሚባለው ነው፡፡ የነገዋን ኢትዮጵያ ብሩህ በማድረግ ሂደት ውስጥ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅበታል፡፡ ሰልጣኞች የተሰጣቸውን ትምህርት በአግባቡ በመከታተልና ካሉበት የሕይወት ጫና በመውጣት ራሳቸውን የመቻል፣ ማኅበረሰቡ ደግሞ ቀና ፊት ማሳየት፣ ተቋማትና የድርጅት

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# ኪነ ጥበባዊ ሁነቶች ጥቁምታ

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የመጻሕፍት ውይይት፣ የፊልም አውደ ርዕይ እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎ ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡












ፎቶ ከገፀ ድር

በከተማችን ከተዘጋጁት ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## መጻሕፍት

በዛሬው ዕለት የመጻሕፍት ውይይት ይደረጋል፡፡ ለውይይት የተመረጠው መጽሐፍ "ሣልሳዊ ልደት" ሲሆን ደራሲው ሲሳይ ንጉሡም በመርሃ ግብሩ ላይ ይታደማሉ፡፡ ውይይቱ ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ጀምሮ ቀበና፣ ካቶሊክ፣ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ፣ ወደ ሳንፎርድ ትምህርት ቤት በሚወስደው መንገድ፣ ባማ አዲስ ሕንፃ አጠገብ፣ በ-FSS አዳራሽ ይደረጋል፡፡ ደራሲው "ሰመመን" በተሰኘው መጽሐፋቸው በስፋት ይታወቃሉ፡፡

በሌላ መረጃ "ጠይም ትውስታዎች" የተሰኘ ርዕስ ያለው አዲስ መጽሐፍ ለንባብ በቃ፡፡ የደራሲ እሱባለው አበራ ድርሰት የሆነው ይህ መጽሐፍ ባሳለፍነው ሐሙስ ወደ አንባቢያን ደርሷል፡፡

## ፊልም

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፊልም ፌስቲቫል እየተካሄደ ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀው ይኸው የፊልም ፌስቲቫል በትናንትናው ዕለት የተጀመረ ሲሆን ነገ ይጠናቀቃል፡፡ ለሦስት ተከታታይ ቀናት በተዘጋጀው ፌስቲቫል ላይ በመታደም ከ25 በላይ አዳዲስ አጫጭር ፊልሞችን መመልከት፣ በፊልም ኢንዱስትሪው ላይ ካሉ ታላላቅ ባለሙያዎች ጋር ትውውቅ መፍጠር እና ውይይት ማድረግ ይቻላል ተብሏል፡፡ ፌስቲቫሉ እየተካሄደ ያለው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም፣ ሼህ አላሙዲ አዳራሽ ሲሆን ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ መታደም ይቻላል፡፡

## የስዕል አውደ ርዕይ

"የዝምታ ወጎች" የስዕል አውደ ርዕይ ከነገ በስቲያ ይጠናቀቃል፡፡ የታሪኩ አስራት የስዕል ሥራዎች የቀረቡበት ይህ አውደ ርዕይ ከግንቦት 19 ቀን 2018 ዓ.ም. ጀምሮ በእይታ ላይ ቆይቷል፡፡ አውደ ርዕዩ እየታየ የሚገኘው ሃያት ሪጀንሲ በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል ሲሆን፣ መግቢያው ደግሞ በእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን በኩል መሆኑ ተገልጿል፡፡

## የቴአትር መርሃ ግብር

"አትጥሪኝ" የተሰኘው ቴአትር ነገ ቦሌ ፍላሚንጎ በሚገኘው የሕፃናትና ወጣቶች ቴአትር ቤት በ11፡00 ሰዓት ይመረቃል። ይህ ቴአትር በዌል አርት መልቲሚዲያ ፕሮዲውስ የተደረገና ከአዲስ አበባ ቴአትር ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ጋር በመተባበር የሚቀርብ ነው፡፡ የቴአትሩ ደራሲ ትርሲት በቀለ ስትሆን በዝግጅት ተስፋዬ ገብረማርያም፣ በትወና ደግሞ አብርሃም ቀናው፣ ሄኖክ ዘርዓብሩክ፣ ሰላማዊት አረዳ እና ሌሎችም ተሳትፈውበታል፡፡

በሌላ መረጃ በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሑድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ በብሔራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 8፡00 ሰዓት እና በ12፡00 ሰዓት "12ቱ እንግዶች"፣ እሑድ "ንጉሥ አርማህ" በ7፡30 ሰዓት እና "እምዬ ብረቷ" በ11፡30 ሰዓት ይታያሉ፡፡ በዚህ ቴአትር ቤት ለሚታዩ ቴአትሮች ተመልካቾች ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ"ሁሉ በጄ" መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በተጨማሪም "ባልቻ አባነፍሶ" እሑድ በ8፡00 ሰዓት በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ የሚታይ ሲሆን ትኬቱን በኦንላይን የክፍያ ሥርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

በሀገር ፍቅር ቴአትር ደግሞ ሐሙስ 11፡30 ሰዓት "ነገሩ አይቆምም"፣ እሑድ በ8፡00 ሰዓት "ሰዴታ" (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12፡00 ሰዓት "የመጨረሻው ፍርድ" ለቴአትር አፍቃሪያን ይታያል፡፡ በተያያዘ መረጃ በሕፃናትና ወጣቶች ቴአትር ቤት ቅዳሜ ጠዋት 4፡00 ሰዓት "አዮ ቦራ" የተሰኘው የአፋን ኦሮሞ፣ እሑድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት ደግሞ "የሰማይ ልጆች" የተሰኙ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው (3 × 7) + (6 × 4) = 45 ይሆናል፡፡ ሁለተኛው (9 × 2) + (5 × 2) = 28 ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት ሶስተኛውና የመጨረሻው (8 × 5) + (4 × 3) = **52** ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ የሚገባው ትክክለኛ ቁጥር 3 ነው፡፡




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ቱሪዝም መንገድ

**በጊዜው አማረ**

ሰዎች ከተለመደው የመኖሪያ፣ የስራ ወይም የሕይወት አካባቢያቸው ውጭ ለዕረፍት፣ ለመዝናናት፣ ለሕክምና፣ ለንግድ ወይም ለሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ወደተለያዩ ቦታዎች የሚያደርጉት ጉዞ፣ በዚያም የሚያደርጉት ቆይታ ቱሪዝም የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በአጭሩ ይገልጸዋል፡፡ ይህ ዘርፍ ተጓዦች አዳዲስ ባህሎችን፣ ታሪኮችን፣ ቅርሶችን፣ የተፈጥሮ መስህቦችንና የሰዎችን የአኗኗር ዘይቤ እንዲያውቁና እንዲያደንቁ ሰፊ ዕድል ይፈጥራል።

ይህ ዘርፍ ከማኅበራዊና ባህላዊ ፋይዳው ባሻገር፣ ቱሪዝም ለብዙ ሀገራት የኢኮኖሚ ዕድገት ዋነኛ ምሰሶ ነው። የጎብኚዎች መበራከት ለሆቴሎች፣ ለትራንስፖርት፣ ለባህል እና ለሀገር በቀል እደ-ጥበብ ውጤቶች ሰፊ ገበያ ከመፍጠሩም በላይ፣ ለዜጎች ከፍተኛ የሥራ ዕድል ይፈጥራል። እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ያሳድጋል። በአጠቃላይ ቱሪዝም የተፈጥሮና የታሪክ ቅርሶች ተጠብቀው ለትውልድ እንዲተላለፉ ከማድረግ፣ ለተጓዦች ተዝናኖትና ትምህርትን ከመፍጠር ተሻግሮ በሕዝቦች መካከል ትስስር፣ ሰላምና የጋራ መከባበርን የሚያጠናክር እና ዘርፈ-ብዙ ጥቅሞች ያሉት ዘርፍ ነው። ለመሆኑ ቱሪዝም እና ተዝናኖት ያላቸው ትስስር ምን ይመስላል? የበርካታ ጎብኚዎች ፍላጎት እየሆነ የመጣው አረንጓዴ ቱሪዝም ምንድን ነው? ኢትዮጵያስ በዘርፉ ምን እየሰራች ነው? የሚለውን በዚህ ጹሁፍ እንዳስሳለን።

## የቱሪዝምና መዝናኛ ትስስር

ቱሪዝም እና መዝናኛ የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው ለማለት ይቻላል። መዝናኛ ሰዎች ከዕለት ተዕለት የሥራ ጫና እና ውጥረት እረፍት ለማግኘት የሚያደርጉትን ማንኛውንም አእምሮንና አካልን የሚያድስ እንቅስቃሴ የሚያካትት ሲሆን፣ ቱሪዝም ደግሞ ይህንን መዝናኛ ፍለጋ ከተለመደው አካባቢ ውጭ ወደ አዲስ ቦታ መጓዝን ይጠይቃል። ስለዚህ፣ አብዛኛው የቱሪዝም ጉዞ መሠረታዊ ዓላማው መዝናናት በመሆኑ፣ መዝናኛ ለቱሪዝም መፈጠርና መስፋፋት እንደ ዋና አንቀሳቃሽ ኃይል ያገለግላል።

የሁለቱ ዘርፎች ግንኙነት በቱሪስት መዳረሻዎች ልማት ላይ በግልጽ ይታያል። አንድ የቱሪስት መስህብ ተጓዦችን መሳብ የሚችለው በውስጡ የተለያዩ የመዝናኛ አማራጮችን ማካተት ሲችል ነው። ለምሳሌ፡- እንደ ብሔራዊ ፓርኮች፣ የባሕር ዳርቻዎች፣ የባህል ክለቦች እና የሙዚቃ ፌስቲቫሎች ያሉ የመዝናኛ ማዕከላት የቱሪዝም ፍሰቱን ያጠናክራሉ። ቱሪስቶች ወደ አንድ አካባቢ ሲሄዱ የተፈጥሮና የታሪክ እሴቶችን ከመመልከት ባለፈ፣ በስፖርታዊ ጨዋታዎች፣ በባህላዊ




ፎቶ ከገፀ ድር

ኢትዮጵያ ለአረንጓዴ ቱሪዝም የሚያግዙ ስራዎችን በማከናወን ላይ ነች

ጭፈራዎችና በተለያዩ የመዝናኛ ሁነቶች ላይ መሳተፍ ይፈልጋሉ፤ ይህም የጉዟቸውን ልምድ የተሟላ ያደርገዋል። ለዚህም ነው ቱሪዝም እና ተዝናኖት የማይነጣጠሉ ናቸው የሚባለው።

አርቲስት መምህሩ ጫሞ በብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ስራዎቹ የሚታወቅ ድምጻዊ ነው፡፡ ዮ ማስቃላ፣ ደሬ ዲቻ እና አንበሳ ጋሞ በሚሉት ስራዎቹ ይበልጥ ይታወቃል፡፡ ከዚህም ባለፈ የቱሪዝም ማናጅመንት ትምህርት አጥንቷል፡፡ በቅርቡም ጫሞና ኤቨንትስን በመመስረት የተለያዩ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል።

አርቲስቱ በጉዳዩ ላይ በቅርቡ ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በሰጠው አስተያየት፣ ቱሪዝም በባህሪው የሁለትዮሽ ጥቅም የሚገኝበትና ከመዝናኛ ተነጥሎ የማይታይ ዘርፍ መሆኑን ገልጿል። በእሱ እምነት ቱሪዝም ማለት በአንድ በኩል ወደ ስፍራው የሚመጡ ጎብኚዎች በሰፊው የሚዝናኑበት፣ አእምሯቸውንና አካላቸውን የሚያድሱበት እንዲሁም ከፍተኛ ደስታን የሚያገኙበት ምቹ መድረክ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ለሀገርና ለከተማ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በከፍተኛ ሁኔታ ያሳድጋል። የቱሪስት መዳረሻዎችን የሚያዘጋጁ አካላት፣ የአካባቢው ማህበረሰብ እና ከተሞች ከጎብኚዎች ፍሰት የተሻለ ገቢ የሚያገኙበትና የንግድ እንቅስቃሴዎችን የሚያነቃቁበት ሰፊ የገበያ ዕድል እንደሚፈጥር አርቲስቱ በዝርዝር አስረድቷል።

በኢኮኖሚ ረገድም የቱሪዝም እና የመዝናኛ ትስስር ከፍተኛ አቅምን ይፈጥራል። ቱሪስቶች ለመዝናኛ አገልግሎቶች (ለቴአትር፣ ለኮንሰርት፣ ለምሽት ክበባት ወይም ለፓርክ መግቢያዎች) የሚያወጡት ወጪ በቀጥታ የአካባቢውን ማኅበረሰብ የገቢ ምንጭ ያሳድጋል። የመዝናኛ ዘርፉን ለማዘመን የሚደረጉ መዋዕለ-ንዋዮች እንደ ዘመናዊ መዝናኛ ፓርኮች እና የባህል ማዕከላት ግንባታ የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜና የገንዘብ ወጪ በመጨመር ለሀገር ውስጥ የሥራ ዕድል ፈጠራና ለኢኮኖሚ መነቃቃት ትልቅ አስተዋጽዖ ያበረክታሉ።

በዚህም መዝናኛ ለቱሪዝም ህያውነትንና ማራኪነትን ሲሰጥ፣ ቱሪዝም ደግሞ ለመዝናኛ ኢንዱስትሪው ሰፊ ዓለም አቀፋዊ ገበያና ዕድገትን ያበረክታል። በዚህ ሂደት ውስጥ አረንጓዴ ቱሪዝም የሚለው ሃሳብ ሰፊ ቦታ እየያዘ መጥቷል፡፡

## አረንጓዴ ቱሪዝም ምንድን ነው?

አረንጓዴ ቱሪዝም (Green tourism) ማለት ለአካባቢ ጥበቃ ቅድሚያ የሚሰጡ፣ የአገር ውስጥ ኢኮኖሚን የሚደግፉ እና የባህል ቅርሶችን የሚያከብሩ መዳረሻዎችን የሚገልጽ ነው፡ ፡ ይህ ፅንሰ-ሀሳብ ደኖችን መጎብኘት ወይም በጫካ አካባቢ በድንኳን ውስጥ ማደር ብቻ አይደለም። ይልቁንም አካባቢንና ደን ለመጠበቅ ከትራንስፖርት እና ከማረፊያ ቦታ ጀምሮ እስከ ምግብ አጠቃቀም እና የመዝናኛ ጉዞዎች ድረስ ያሉትን እያንዳንዱን ውሳኔዎች በጥንቃቄ እና በኃላፊነት ስሜት መወሰንን የሚመለከት ነው።

ኢኮ የተሰኘው ገጽ-ድር እ.ኤ.አ በ2025 “The Rise of Green Tourism: How Travelers Are Redefining Sustainability” በሚል ርእስ ሰፋ ያለ ጽሁፍ ለንባብ አብቅቷል። ጹሁፉ እንደሚያትተው አረንጓዴ ቱሪዝም በሰው ልጅ የመዝናናት እንዲሁም ሀገራት ከቱሪዝም ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት ባላቸው ፍላጎት እንዲሁም በተፈጥሮ መካከል ሚዛን እንዲኖር ያደርጋል፡ ፡ ጸሁፉ አክሎም በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች አረንጓዴ ቱሪዝም ተመራጭ እየሆነ የመጣው የዘመናችን የተዝናኖት ፍላጎት ነው ይላል፡፡

## ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ቱሪዝም መንገድ

ከ20 ዓመታት ለሚበልጥ ጊዜ በቱሪዝምና በአስጎብኚነት ሙያ ላይ እየሰሩ የሚገኙትና የኩታ አስጎብኝ ድርጅት መስራች የሆኑት ወይዘሮ ሶስና ሙሉጌታ፣ ወደ ዘርፉ ለመግባት ያነሳሳቸውን ዋና ምክንያት በግልጽ ያስረዳሉ። እርሳቸው አዲስ አበባን ጨምሮ በአራቱም የኢትዮጵያ አቅጣጫዎች በመዘዋወርና የሀገሪቱን እምቅ የቱሪዝም አቅም በአካል በመመልከት ሰፊ ልምድ ማካበት ችለዋል።

ይህንን ሁሉ ተፈጥሯዊና ታሪካዊ ውበት ከተመለከቱ በኋላ፣ የኢትዮጵያ የቱሪዝም ሀብት ለሀገር ውስጥ ጎብኚዎችም ሆነ ለውጭ ሀገር ቱሪስቶች በአግባቡ አለመተዋወቁ ከፍተኛ ቁጭት እንደፈጠረባቸው ይናገራሉ። በመሆኑም ይህንን ክፍተት ለመሙላትና የሀገሪቱን አስደናቂ መዳረሻዎች ለዓለም ለማስተዋወቅ ባላቸው ጥልቅ ፍላጎት ዘርፉ ላይ መሰማራታቸውን ይገልጻሉ። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ባህል አላት። ታሪካዊ ቅርስ አላት፡፡ አረንጓዴ መዳረሻዎች እየበዙ ነው፡፡ በቅርቡ የተሰሩ አረንጓዴ ፓርኮችና መዝናኛዎች የሰው ልጅ ፈጠራና የተፈጥሮ ውበት የተቀናጀባቸው ናቸው፡፡

በመሆኑም ኢትዮጵያ የተፈጥሮና የባህል ሀብቶቿን ዘላቂነት ባለው መልኩ ለማልማት የምታደርገው ጥረት በአረንጓዴ ቱሪዝም (Green Tourism) ስትራቴጂ ውስጥ በግልጽ እየታየ ነው። ሀገሪቱ ያሏትን ብርቅዬ የዱር እንስሳት፣ ብሔራዊ ፓርኮችና ጥንታዊ የቅርስ ስፍራዎች ሳይበረዙ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ የምታደርገው ጉዞ፣ አካባቢን ከመጠበቅ ባለፈ የኢኮኖሚ ምንጭ እየሆነ መጥቷል። ይህ አዲስ የቱሪዝም አስተሳሰብ በተለይም ከተፈጥሮ ጋር የተስማሙ የቱሪስት መዳረሻዎችን በመገንባትና የሥነ-ምህዳር ሚዛንን በመጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሮች ለዚህ ዘርፍ ዕድገት ትልቅ መሠረት ጥለዋል። በየዓመቱ እየተተከሉ ያሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞች የደን ሽፋኑን ከማሳደጋቸውም በላይ፣ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት አደጋ ተጋርጦባቸው የነበሩ የዱር እንስሳትና አእዋፋት ለመጠበቅ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በዋና ከተማዋና በተለያዩ ክልሎች የተገነቡት ሥነ- ምህዳርን መሠረት ያደረጉ ፓርኮችና የከተማ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ የከተማ ቱሪዝምን ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ መንገድ መምራት እንደሚቻል ማረጋገጫ ሆነዋል።

የኢትዮጵያ የአረንጓዴ ቱሪዝም ጉዞ ሌላኛው ጠንካራ ጎን ማኅበረሰብ ተኮር ቱሪዝምን (Community-Based Tourism) ማጠናከሩ ነው። የአዲስ አበባን ገጽታ የቀየረው የኮሪደር ልማት እና የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክቶች፣ አረንጓዴነትን ማዕከል ያደረጉ ዘመናዊ መዝናኛዎችንና የሕዝብ መናፈሻዎችን በመፍጠር ለከተማ ቱሪዝም አዲስ ምዕራፍ ከፍተዋል። ይህ የተፈጥሮን ውበት ከዘመናዊ አርክቴክቸር ጋር የማዋሃድ ስኬታማ ተሞክሮ፣ አሁን ላይ ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በመስፋፋት ከአዲስ አበባ ውጭ በርካታ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የስነ-ምህዳር ቱሪዝም (Eco-tourism) መዳረሻዎችና ሎጆችን ለማፍራት በቅቷል።

ከእነዚህ አስደናቂ ፕሮጀክቶች መካከል በኦሮሚያ ክልል የሚገኙት የወንጪና ደንዲ ኢኮ-ቱሪዝም መንደሮች፣ በአማራ ክልል የሚገኘው የጎርጎራ መዝናኛ መዳረሻ፣ እንዲሁም በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኘው የኮይሻ ፕሮጀክት ዋና ማሳያዎች ናቸው። እነዚህ መዳረሻዎች በተፈጥሮ እቅፍ ውስጥ የተገነቡ ዘመናዊ ማረፊያዎችን (Lodges)፣ የውሃ ላይ መዝናኛዎችን፣ የባህል ማዕከላትን እና የእግር ጉዞ መንገዶችን ያካተቱ ናቸው። እያንዳንዱ መዳረሻ የአካባቢውን የተፈጥሮ መልክዓ-ምድር ሳይጎዳ ይልቁንም ውበቱን በሚያጎላ መልኩ የተገነባ በመሆኑ የአረንጓዴ ቱሪዝም ህያው ማሳያ ሆነዋል።

በአዲስ አበባም ሆነ ከአዲስ አበባ ውጭ የተገነቡ ግዙፍ መዳረሻዎችና የአረንጓዴ መዝናኛ ስፍራዎች ለሀገሪቱ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዘላቂነት ያላቸውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎች እያስገኙ ናቸው። በአንድ በኩል፣ የውጭና

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ከዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# የጤና መድህኖቹ የጤና ፈተና

• በጨቅላ ህጻናት እንክብካቤ መስጫ ክፍል ውስጥ ከሚሰሩ ነርሶች መካከል እስከ 75 በመቶ የሚሆኑት ለወገብ ህመም የተጋለጡ መሆናቸው ተመላክቷል

በሸዋርካብሽ ቦጋለ



ፎቶ፡- ከገፀ ድር

በጨቅላ ህጻናት እንክብካቤ መስጫ ክፍል ውስጥ በሚሰሩ ነርሶች ላይ የሚከሰትን የወገብ ህመም መከላከል ላይ ያተኮረ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል

በዓለም አቀፍ ደረጃ በጨቅላ ህጻናት እንክብካቤ መስጫ ክፍል (NICU) ውስጥ የሚሰሩ ነርሶች ለከፍተኛ የወገብ ህመም ተጋላጭ ናቸው። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት እስከ 70 በመቶ የሚሆኑ በዚህ ክፍል ውስጥ የሚሰሩ ነርሶች በህመሙ ይጠቃሉ። ይህ ህመም የሚመነጨው ጨቅላ ህጻናትን በተደጋጋሚ በማንሳት፣ በማገላበጥ፣ በማቀፍ እና ዝቅ ባሉ የኢንኩቤተር አልጋዎች ላይ ለረጅም ሰዓታት ጎንበስ ብሎ በመስራት ከሚመጣ የአካል ግፊት ነው። እንደ Journal of Neonatal Nursing ያሉ ዓለም አቀፍ የመረጃ ምንጮች እንደሚጠቁሙት፣ ይህ ድምፅ አልባ ቀውስ የነርሶችን የጤና ሁኔታ ከመጉዳቱም በላይ ለስራ መቅረትና ከስራ መልቀቅ ዋነኛ ምክንያት እየሆነ ይገኛል።

ለዚህ ችግር መባባስ ዋነኛው ክፍተት በሆስፒታሎች ውስጥ ያሉ የስራ አካባቢዎች ለነርሶች የአካል ብቃት ምቹ አለመሆናቸው እና ተገቢው ስልጠና አለመስጠቱ ነው። ይህንን ክፍተት ለመቅረፍ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ስራ ላይ ማዋል ወሳኝ መፍትሔ ነው። ቁመታቸው በቀላሉ ከፍ እና ዝቅ የሚሉ የኢንኩቤተር አልጋዎችንና የህጻናት መታጠቢያዎችን መጠቀም ነርሶች ጎንበስ የሚሉበትን አንግል በእጅጉ ይቀንሳል። በተጨማሪም፣ በቴክኖሎጂ የታገዙ የነርሶች ስራ መከታተያ መተግበሪያዎችን በመጠቀም የስራ ጫናን እና የሰዓት ሽግሽግን በፍትሐዊነት ማከፋፈል ይቻላል።

ቴክኖሎጂን ከማምጣት ባለፈ የባለሙያዎቹን ቀጥተኛ ተሳትፎ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መጠቀም ዘላቂ ለውጥ ያመጣል። ነርሶች ራሳቸው በስራ ቦታቸው ላይ ያሉትን ምቾት የማይሰጡ ሁኔታዎችን የሚገመግሙበትና መፍትሔ የሚያፈላልጉበት አካሄድ መዘርጋት ያስፈልጋል። በስራ መሃል የሚደረጉ የተደራጁ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን ማስተዋወቅና ነርሶች እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉበትን አሰራር መዘርጋት የችግሩን መጠን ይቀንሰዋል። ይህ ሳይንሳዊ አካሄድ የነርሶችን ደህንነት በመጠበቅ ለጨቅላ ህጻናቱ የሚሰጠውን የእንክብካቤ ጥራት ከፍ ያደርገዋል።

ዳግማዊ ምኒልክ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በ2017 ዓ.ም በአዲስ አበባ የመንግስት ሆስፒታሎች በጨቅላ ህጻናት እንክብካቤ መስጫ ክፍሎች ውስጥ በሚሰሩ ነርሶች ላይ ባካሄደው ጥናት፣ በአካባቢው ያለውን የወገብ ህመም ስርጭት ስፋትና ስር የሰደዱ መንስኤዎችን በግልፅ በማሳየት ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

በሀገራችን በጨቅላ ህጻናት እንክብካቤ መስጫ ክፍል ውስጥ የሚሰሩ ነርሶች በከፍተኛ የስራ ጫና እና የሰውነት አቀማመጥና የስራ አካባቢ ክፍተቶች ምክንያት ለወገብ ህመም የመጋለጥ እድላቸው ሰፊ እንደሆነ የዘርፉ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የተለያዩ ጥናታዊ መረጃዎችም በዚህ ክፍል ውስጥ ከሚሰሩ ነርሶች መካከል ከ60 እስከ 75 በመቶ የሚሆኑት በስራ ምክንያት ለሚመጣ የወገብ ህመም ተጋላጭ መሆናቸውን ያመላክታሉ። በአዲስ አበባ ደረጃ ያለው እውነታም ከዚህ የተለየ አለመሆኑን ከዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ያገኘነው መረጃ ያረጋግጣል።

በኮሌጁ የጨቅላ ህፃናት ትምህርት ክፍል አስተባባሪ ፍቅርተ ካሳየ በአዲስ አበባ በሚገኙ የመንግስት ሆስፒታሎች በጨቅላ ህጻናት እንክብካቤ መስጫ ክፍሎች ውስጥ በሚሰሩ ነርሶች ላይ ያለውን የወገብ ህመም ስርጭትና ተያያዥ ሁኔታዎችን በተመለከተ በ2017 ዓ.ም ጥናት አካሂደዋል። በጥናታቸውም በክፍሉ ውስጥ የሚሰሩ አብዛኛዎቹ ነርሶች ለዚህ ህመም የተጋለጡ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

ይህ የታችኛው የጀርባ ህመም ብዙውን ጊዜ በከፍተኛ የስራ ጫና እና በኤርጎኖሚክስ ክፍተቶች ምክንያት የሚመጣ ሲሆን፣ በነርሶች ላይ ከሚከሰቱት የሙያ ደህንነት የጡንቻና አጥንት መዛባቶች (Musculoskeletal Disorders) መካከል ዋነኛውና በጣም የተለመደው መሆኑን ተመራማሪዋ በጥናታቸው ጠቁመዋል።

ተመራማሪዋ በከተማዋ በሚገኙ የመንግስት ሆስፒታሎች በጨቅላ ህጻናት እንክብካቤ መስጫ ክፍሎች ውስጥ በሚሰሩ 305 ነርሶች ላይ ባደረጉት ጥናት፣ 69 ነጥብ 8 በመቶ የሚሆኑት የህመሙ ሰለባ መሆናቸውን አግኝተዋል። ይህም ችግሩ በክፍሉ ውስጥ ምን ያህል ስር የሰደደና ሰፊ ትኩረት የሚሻ መሆኑን በግልጽ ያሳያል።

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው ደም የሚቀዱ ነርሶች (AOR = 3 ነጥብ 83)፣ ምቹ ባልሆነ ወይም በተጨናነቀ የስራ አካባቢ የሚሰሩ (AOR = 2 ነጥብ 36)፣ እና በምሽት ፈረቃ የሚሰሩ ነርሶች (AOR = 3 ነጥብ 79) ያክል ለወገብ ህመም የመጋለጥ እድላቸው ከሌሎቹ በከፍተኛ ሁኔታ የላቀ መሆኑ ተረጋግጧል።

ከአጥንትና ጡንቻ ጋር የተያያዙ የጤና እክሎችን ለመቀነስና የነርሶችን ጤንነት ለማሻሻል፣ የሆስፒታል አስተዳዳሪዎች በተለይ በምሽት ፈረቃ ወቅት በቂ የሰው ኃይል መመደቡን ማረጋገጥና አካላዊ የስራ አካባቢን ምቹ ማድረግ እንዳለባቸው የጥናቱ ግኝት ምክረ-ሀሳብ ያስረዳል።

ለችግሩ መፈጠርና መባባስ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም፣ ዋነኞቹ በስራው ምክንያት ለረጅም ሰዓት መቆም፣ በተለይ ጨቅላ ህጻናትን በኢንኩቤተር (ማቀፊያ) ውስጥ በሚንከባከቡበት፣ በሚያቅፉበት እና የህክምና እቃዎችን በሚያነሱበት ወቅት የሚኖራቸው የረጅም ሰዓት የማጎንበስና ያለመመጣጠን ሁኔታዎች ናቸው።

የረጅም ሰዓት የስራ ፈረቃ፣ የሰራተኛ እጥረት እና ስለ ኤርጎኖሚክስ ደህንነት የሚሰጡ ስልጠናዎች ማነስ ለችግሩ መባባስ እንደ ትልቅ ክፍተት ይጠቀሳሉ። የተወሰኑ የጨቅላ ህጻናት እንክብካቤ መስጫ ክፍሎች ዲዛይን፣ አልጋዎችና እቃዎች ከነርሶቹ ቁመትና ምቾት ጋር አብረው የማይሄዱ መሆናቸው ደግሞ ህመሙን የከፋ ያደርገዋል።

በሆስፒታሎች ያሉ የህክምና ቁሳቁሶች ለነርሶች ምቾት ታስበው የተሰሩ አለመሆናቸው፣ ስለ ወገብ ጤና የሚሰጡ ስልጠናዎች ማነስ፣ የንድፍ (Design) ጉድለትና የጤና ስርዓቱ መዋቅራዊ ክፍተቶች ድምር ውጤት ለችግሩ መባባስ ዋነኛ ምክንያቶች መሆናቸውን ተመራማሪዋ በጥናታቸው አስፍረዋል።

ይህ ችግር በነርሶቹ ጤና ላይ ብቻ ሳይሆን በሚሰጡት የህክምና አገልግሎት ጥራት ላይ ጭምር አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ስለዚህ ይህንን ስር የሰደደ ችግር በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቅረፍ ዘመናዊ ቴክኖሎጂንና ሳይንሳዊ የስራ አመራርን አቀናጅቶ መተግበር የግድ እንደሚል ተመራማሪዋ ያሳስባሉ።

እንደ ተመራማሪዋ ማብራሪያ የጤና ባለሙያዎች ቁመት ተመሳሳይ ስላልሆነ፣ ቁመታቸው በቀላሉ የሚስተካከሉ የህጻናት አልጋዎችን፣ ጠረጴዛዎችንና የዲጂታል መከታተያዎችን መጠቀም ነርሶች በተደጋጋሚ የሚያጎነብሱበትን ሁኔታ ይቀንሳል። በተጨማሪም ነርሶች በፈረቃ ምደባና በስራ ቦታ ማሻሻያ ውሳኔዎች ላይ መሳተፍ አለባቸው።

ችግሩን ለማቃለል ከመንግስትና ከጤና ሚኒስቴር የሚጠበቀው በሆስፒታሎች ውስጥ ተግባራዊ የሚሆን የታካሚ አያያዝ እና የስራ ላይ ደህንነት መመሪያዎችን ቀርጾ በህግ ማስፈጸም ነው። እንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የህክምና ቁሶች የኤርጎኖሚክስ መስፈርትን ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

የሆስፒታልና የጨቅላ ህጻናት እንክብካቤ መስጫ ክፍሎችን የስራ ከባቢ ለነርሶች ምቹ አድርገው ማደራጀት፣ አስገዳጅ የአጭር ጊዜ እረፍቶችንና የሰውነት ማዝናኛ ሰዓታትን በፈረቃ ውስጥ ማካተት፣ እንዲሁም ስለ አካል አቀማመጥ ቀጣይነት ያለው ስልጠና መስጠትና የሙያ ደህንነት ኮሚቴ ማቋቋም አለባቸው።

በመጨረሻም ነርሶች ራሳቸው የስራ ጫና ቢኖርም እንኳ ከማጎንበስ ይልቅ ጉልበትን አጥፎ መስራትን፣ ከባድ ዕቃዎችን በጋሪ መግፋትን፣ እንዲሁም አከርካሪን የሚያጠናክሩ ስፖርቶችን መስራትና በቂ ፈሳሽ መውሰድን ማዘውተር ይኖርባቸዋል። በክፍላቸው ያሉትን ክፍተቶችም ለይተው ለአስተዳደሩ በማሳወቅ መፍትሄ ላይ በንቃት መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል።

የጥናቱን ግኝቶች በተግባር ለመፍታት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የሆስፒታሎች አስተዳደር በጋራ በመሆን የጨቅላ ህጻናት እንክብካቤ መስጫ ክፍሎችን የአሰራር መመሪያ ማሻሻል አለባቸው። በተለይም በሀገር ውስጥ አቅም ሊሰሩ የሚችሉ ቁመታቸው የሚስተካከሉ አልጋዎችን ማቅረብ፣ የነርሶችን የስራ ፈረቃ ጫና መቀነስ እና በጥናቱ ግኝቶች ላይ ተመስርቶ ቀጣይነት ያለው የጤናና ደህንነት ስልጠና መስጠት የችግሩን ስርጭት ለመቀነስ ወሳኝ እርምጃዎች ናቸው፡፡

# ልጆች ስለጤናማ አመጋገብ ምን ያህል ታውቃላችሁ?

በፋንታነሽ ተፈራ

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? በዛሬው ርዕሰ ጉዳያችን ስለ ጤናማ አመጋገብ ምንነት፣ ጤናማ አመጋገብን ብንከተል ስለምናገኛቸው ጥቅሞች እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ መረጃ እንለዋወጣለን። ለዚህ ደግሞ የአዲስ ብርሃን ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጓደኞቻችሁን ተሞክሮና የስነ ምግብ ህክምና ባለሙያ የሰጡትን ማብራሪያ በማካተት እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡




ፎቶ፡- ከገፀ ድር

የተመጣጠነ ምግብ ከሚባሉት ውስጥ ጥቂቶቹ

ሄመን ክፍሌ እባላለሁ፡፡ የ5ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ ጤናማ አመጋገብ ማለት ጤናችንን በማይጎዳ መልኩ እቅድ አውጥተን የምንመገበው ነው፡፡ ለእኔ ለጤና ተስማሚ የምላቸው ምግቦች አትክልትና ፍራፍሬ፣ ጥራጥሬ እንዲሁም ቀይ እንጀራ ናቸው፡፡ ስመገብም በመጠኑ፣ ንጽህናው በተጠበቀ መልኩ ነው፡፡ ጣፋጭ ምግቦችን አብዝቼ እንዳልመገብ እናቴ ስለምትመክረኝ በመጠኑ እጠቀማለሁ፡፡ በጣም ጠግቤ አልበላም፡፡ እየበላሁም ውሃ እና ሻይ አልጠጣም፡፡

አመጋገቤን ጥሩ ማድረጌ ጤነኛ ሆኜ ትምህርቴን እንድከታተል አድርጎኛል። የተመጣጠነ ክብደት እንዲኖረኝ ረድቶኛል።

ስንታየሁ ይርዳው እባላለሁ፡፡ የ7ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ ስለ ጤናማ አመጋገብ በሳይንስ ትምህርት ተምሬያለሁ፡፡ ጤናማ አመጋገብ ማለት ለሰውነታችን ጠቃሚ የሆኑ ኃይልና ሙቀት ሰጪ፣ ገንቢ፣ በሽታ ተከላካይ ምግቦችን በንጽህና መመገብ እንደሆነ ግንዛቤው አለኝ፡፡

እኔ ከዚህ በፊት በረዶ የመጥባትና ጣፋጭ ነገሮችን የመመገብ ልምድ ነበረኝ፡፡ በዚህም ቶንሲል እንድታመም አድርጎኛል፡፡ በዚህ እና በሌሎች ምክንያቶች የተነሳ ጣፋጭ ነገሮችን አልመገብም። ቤተሰቦቼም እኔ የምፈልገውን ሳይሆን የሚያስፈልገኝን ያደርጉልኛል፡፡ ለሌሎች ጓደኞቼም የምመክረው እንደ እኔ በቶንሲል እንዳትታመሙ በረዶ አትጠቀሙ የሚል ነው፡፡

ልጆች እንዴት ከረማችሁ? ወይዘሮ ኪብሮን ሰናይ እባላለሁ፡፡ የስነ ምግብ ህክምና ባለሙያ ነኝ፡፡ ዛሬ የምነግራችሁ ስለ ጤናማ አመጋገብ ይሆናል፡፡ ጤናማ አመጋገብ ማለት ሰውነታችን በአግባቡ እንዲሰራ ለማድረግ፣ እድገትን ለመጨመር፣ በሽታን ለመከላከል እና ሙሉ ጤንነትን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉትን አልሚ ምግቦች በተመጣጣኝ ሁኔታ መመገብ ማለት ነው።

የተመጣጠነ ምግብ የምንላቸው ኃይል ሰጪ ምግቦች (ካርቦሃይድሬት) ለምሳሌ እንደ ጥራጥሬ፣ ሰውነት ገንቢ ምግቦች (ፕሮቲን) ለምሳሌ ባቄላ፣ አተር፣ የእንስሳት ተዋጽኦ፣ ሥጋ፣ እንቁላል እና የወተት ተዋጽኦዎች፣ በሽታ ተከላካይ ምግቦች (ቪታሚንና ሚነራል) አትክልትና ፍራፍሬዎችን እንዲሁም ቅባታማ ምግቦችን የሚያካትት ነው፡፡

ልጆች እነዚህን ተመጣጣኝ ምግቦች ሁሉንም ላታገኙ ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን የቤተሰቦቻችሁ አቅም የሚፈቅደውን ከአትክልት እንደ ጎመን፣ ሰላጣ፣ ካሮት፤ ከጥራጥሬ ደግሞ አተር፣ ባቄላ፣ ሽንብራ፤ ከእንስሳት ተዋጽኦ ደግሞ ወተት፣ እርጎና አይብ ስትመገቡ ጤናማ አመጋገብ ተከተላችሁ ማለት ነው፡፡

ልጆች ጤናማ አመጋገብ ስትከተሉ ተገቢ የሆነ የሰውነት ክብደት ይኖራችኋል። ከስኳር፣ ከግፊት፣ ከልብ... በሽታዎች ይከላከልላችኋል። በተፈጥሮ በሽታን የመከላከል አቅማችሁ ይጨምራል፡፡ ብሩህ አዕምሮ ይኖራችኋል፤ የመማርና የፈጠራ ችሎታችሁንም ያዳብራል፡፡

ልጆች የታሸጉ ምግቦችን ትመገባላችሁ አይደል? አዎ፣ የታሸጉ ምግቦች በጤናችሁ ላይ ችግር የሚያመጡ ናቸው። እነዚህ ምግቦች የምግብ ቀለሞችና ምግቦቹ እንዳይበላሹ ኬሚካሎች የሚጨመሩባቸው በመሆናቸው ጤናማ ምግቦች አይደሉም። ጣፋጭ ነገሮችን ስትመገቡ ደግሞ ለአላስፈላጊ የሰውነት ውፍረት፣ ለደም ግፊትና ለስኳር በሽታ ተጋላጭ ትሆናላችሁ።ስለዚህ ልጆች የፋብሪካ ምግቦችንም ይሁን መጠጦችን ከመመገብና ከመጠጣት ይልቅ በተፈጥሮ የሚገኙና ቤት ውስጥ የምናበስላቸውን በመመገብ ጤናችሁን መጠበቅ አለባችሁ፡፡

## የከተማችን አረንጓዴ ገነት፡ የጉለሌ ዕፅዋት ማዕከል



ሰላም ልጆች! በአዲስ አበባችን የሚገኘውን የጉለሌ ዕፅዋት ማዕከልን ታውቁታላችሁ? ይህ ቦታ ለከተማችን ትልቅ ሳንባ በመሆን ንፁህ አየር የሚሰጠንና እጅግ በጣም ብዙ የሚያምሩ እፅዋት፣ በቀለማት ያሸበረቁ አበቦች እና የተለያዩ ወፎች በደስታ የሚኖሩበት አስደናቂ ስፍራ ነው። ማዕከሉ ውስጥ ስትዘዋወሩ በዕድሜ ትልልቅ የሆኑ ዛፎችንና በሀገራችን ብቻ የሚበቅሉ ብርቅዬ ዕፅዋትን ታገኛላችሁ። ወደዚህ ቦታ መጥታችሁ ስትጫወቱና ስትዝናኑ፣ ተፈጥሮን በጥልቀት እንድትረዱና እንድትወዱ ያደርጋችኋል።

በተለይ ደግሞ በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር ላይ እኛ ልጆችም የራሳችንን ችግኝ መትከልና መንከባከብ መቻል አለብን! በጉለሌ ዕፅዋት ማዕከል ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች የሚተከሉት ችግኞች ከተማችንን ይበልጥ ውብ ከማድረጋቸውም በላይ፣ የዱር እንስሳት መጠለያ እንዲያገኙና የአየር ንብረታችን ሁልጊዜ የተስተካከለ እንዲሆን ትልቅ ፋይዳ አላቸው። እናንተም በዚህ ማዕከልም ይሁን በሌሎች ቦታዎች የራሳችሁን አረንጓዴ አሻራ በማኖር ለከተማችን ፍቅርን ማበርከት ይጠበቅባችኋል!

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

እንደ አህያ ዱላ፤ እንደ ድመት ወተት፤እንደ ውሻ እሳት፤ እንደ ነበር ሥጋ የሚወድ?

**መልስ፡-** ሐ. ቆጮ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ንፍሮውን ትቶ ገበታውን በላሁት?**

ሀ . ገንፎ
ለ . ጉልባን
ሐ . ዱባ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የ“ሲስተም የለም” ሰበብን ታሪክ ያደረገው ተቋም

**“በአዲስ መሶብ ማዕከላት የኃይል እና የኢንተርኔት አቅርቦት አስተማማኝ እንዲሆን የተለያዩ አማራጮች ጥቅም ላይ ውለዋል”**

**የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ደሳለኝ ተረፈ (ኢንጅኒየር)**



ፎቶ- ከፋይል
የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ደሳለኝ ተረፈ (ኢንጅኒየር)

ፎቶ- ከገፀ ድር
ማዕከሉ በዘረጋው የአሰራር ስርዓት ተገልጋዮችን ሲያስተናግድ

**በደረጀ ታደሰ**

አቶ በላይነህ ነሲሞ ይባላሉ፡፡ ነዋሪነታቸው በአራዳ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 04 ነው፡፡ ወደ አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ተቋም መጥተው፣ የሚፈልጉትን አገልግሎት አግኝተው ሲወጡ ከቅጥር ግቢው ለተወሰኑ ደቂቃዎች አብረውን እንዲቆዩ ጠየቅናቸው፡፡ እሳቸውም ጥያቄያችንን በደስታ በመቀበላቸው ወደ ጉዳያችን ገባን፡፡

አገልግሎት ፈልጎ ወደ መንግስት ተቋማት ከሚያመራው ሕዝብ መካከል፣ ቁጥሩ ቀላል የማይባል ተገልጋይ፣ ያሰበው ሳይሳካ፣ ‘መብራት የለም፣ ሲስተም (ኔትወርክ) ተቋርጧል፣ ኃላፊ የለም …’ በሚል ሰበባ ሰበብ ከተቋማቱ እንዲመለስ የሚደረግ በመሆኑ፣ በአቶ በላይነህ ላይ ያየነው ዓይነት ደስታና ተዝናኖት አንመለከትም፡፡ የአቶ በላይነህ ገጽታ ፍካት ምክንያቱ ከምን እንደመነጨ ለመገንዘብ በአንደበታቸው ያጋሩንን የሚከተለውን ሃሳብና አስተያየት እንመልከት፤ “የመጣሁት የመንጃ ፈቃድ ለማደስ ነው፡፡ ያገኘሁት አገልግሎት በጣም ደስ የሚል ነው፡፡ በፊት መንጃ ፈቃድ ለማደስ የተለያየ ቦታ መሄድ ግድ ነበር፡፡ ቢያንስ ሜዲካል ምርመራ ውጤት ለማምጣት ጤና ጣቢያ መሄድ ያስፈልግ ነበር፡፡ በዚህ መሃል የመብራት መጥፋት፣ የኔትወርክ መቆራረጥ ያጋጥማል። አሁን ይሄ ሁኔታ በአዲስ መሶብ ቀርቷል። ሁሉም ተቋማት አንድ ቦታ ላይ ተሰባስበዋል፡፡ አንድ ወንበር ላይ በምቾት ቁጭ ብዬ፣ 15 ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ጨርሼ ወጥቻለሁ፡፡ ይህ በጣም ደስ የሚል ነው፡፡”

የፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ ላይ የተፈጠረባትን የስም ስህተት ለማስተካከል ወደ አዲስ መሶብ ጎራ ያለችው ወጣት ትዕግስት ሰለሞንም ሃሳቧን እንደሚከተለው ገልጻልናለች። “ወደ አዲስ መሶብ ከመምጣቴ በፊት ወደሌሎች ተቋማት ሄጃለሁ፡፡ በመታወቂያዬ ላይ የስም ስህተት መኖሩን ያወቅሁት ባንክ ገንዘብ ለማውጣት በሄድኩበት ወቅት ነበር፡፡ ስህተቱን የነገረኝ ባለሙያ፣ የማስተካከለው አዲሱ ገበያ አካባቢ ከሚገኘው የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ተቋም እንደሆነ መረጃ ሰጠኝ፡፡ በዚሁ መሰረት ወደተባልኩት ተቋም አመራሁ፡፡ እዚያ ብዙ ጠብቄ ባለመሳካቱ፣ አራት ኪሎ፣ ቱሪስት ሆቴል አካባቢ ወደሚገኘው ፖስታ ቤት ላኩኝ፡፡ ጊዜው የሥራ ሰዓት መውጫ እየደረሰ ስለነበር፣ በማግስቱ ወደ ፖስታ ቤት መጣሁ፤ እዚህም ሳይሳካልኝ ቀረ፡፡ በዚህ መሃል ‘የት መሄድ እንዳለብኝ’ በብስጭት የጠየኩት የተቋሙ ሠራተኛ፣ በአቅራቢያው ወዳለው አዲስ መሶብ ተቋም እንድሄድ መረጃ ሰጠኝ፡፡ ይህን በማድረግ ደስ በሚል መስተንግዶ መታወቂያዬን ማስተካከል ችያለሁ፡፡ ቀድሞ መረጃ ቢኖረኝ፣ ለድካም እና ለጊዜ ብክነት አልዳረግም ነበር፡፡ ይህም ሆኖ የአዲስ መሶብ አገልግሎት ክሶኛል፡፡”

የተበታተኑ ተቋማትን በእልፍኙ በማሰባሰብ፣ ብዛት ያለውን አገልግሎት በማስተሳሰር፣ ዘመኑን የዋጁ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን በመጠቀም፣ የተሟላ የሥራ ስነ ምግባርን የተላበሱ ሙያተኞችን በማሰማራት… በሚሰጠው አገልግሎት የዜጎችን እርካታ ከፍ ማድረግ የቻለው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት፤ ለዚህ ውጤት ለመብቃቱ ለእያንዳንዱ ተግባር የሠጠው ትኩረትና ይህንን ለመፈጸም የተሄደበት መንገድ ወሳኝነቱ የላቀ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሊዘረዘሩ ከሚችሉና በዲጂታል ቴክኖሎጂ አማካኝነት በኦንላይን ለሚቀርበው የተቋሙ አገልግሎት ውጤታማነት ቁልፍ ሚና ካላቸው መሰረታዊያን መካከል፡-- አስተማማኝ የኃይል እና የኢንተርኔት አቅርቦት በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ እንደ ተቋም ያለውን ሁኔታ እና እውነታ፣ የተቋሙን ዋና ዳይሬክተር ደሳለኝ ተረፈ (ኢንጂኒየር) አነጋግረናል፡፡

የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ተቋም ላይ የኤሌክትሪክ ኃይል እና የኢንተርኔት አቅርቦት በማይቆራረጥ መልኩ አስተማማኝ ሆኖ እንዲቀርብ፤ ስለተቋሙ ምስረታ ጥናት በሚደረግበት ወቅት ጀምሮ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ስለመሆኑ ያስታወሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በትግበራ ሂደት ላይ የተሠሩትን ሥራዎች እና ያስገኙትን ውጤት አብራርተዋል። እንደሳቸው ገለጻ፤ ዋናው መስሪያ ቤት፣ ማዕከላቱ እና የተንቀሳቃሽ መሶብ አገልግሎት በኤሌክትሪክ ኃይል እና በኢንተርኔት መቆራረጥ ምክንያት አገልግሎታቸው እንዳይስተጓጎል፣ ወሳኝ ተቋማትን በባለቤትነት ያሳተፈ፣ ብዙ አማራጮችን የያዘ ሥራ ተሠርቷል፡፡

የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን በተመለከተ በሰጡት ማብራሪያ፤ “ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የአዲስ አበባ አገልግሎት ማዕከል ጋር በመነጋገር እና በመናበብ፣ በእያንዳንዱ የአዲስ መሶብ ማዕከላት አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ካላቸው መስመሮች እንዲዘረጋ ተደርጓል፡፡ ከማዕከላቱ ጋር የሚገናኙት መስመሮች ሁለት ሁለት አማራጮች ያሏቸው ናቸው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፤ በሁሉም ማዕከላት ከፍተኛ አቅም ያለው እና በነዳጅ የሚሠራ ጀነሬተር ዝግጁ ሆኖ ይጠብቃል፡፡ በቅርቡ በነዳጅ አቅርቦት ሰንሰለት ላይ የተፈጠረውን አይነት ዓለም አቀፍ ችግር እና መሰል ሁነቶች በሚከሰቱበት ወቅት፣ ጀነሬተሮች በነዳጅ እጥረት አገልግሎታቸው እንዳይስተጓጎል፣ የአዲስ አበባ ፋይናንስ ቢሮ በልዩ ሁኔታ ነዳጅ ገዝቶ የሚያቀርብበት አሠራር ተዘርግቷል” ብለዋል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ አክለው እንዳስረዱት፤ ተቋሙ ያሉት የኤሌክትሪክ ኃይል አማራጮች የመቋረጥ ችግር ቢገጥማቸው እንኳን፣ የተቋሙ አገልግሎት ያለአንዳች እንከን ለሰዓታት ሥራው እንዲቀጥል የሚያግዙ ኃይል ማከማቻ መሣሪያዎች (Uninterruptible Power Supply-UPS) ለአገልግሎት በቅተዋል። በየማዕከላቱ ያሉ አገልግሎት ሰጪ ሠራተኞች (ሙያተኞች) የሚጠቀሙባቸው የባትሪ አቅማቸው ከፍተኛ የሆኑ የላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ ኃይል ቢቋረጥ እንኳን ሥራ እንዳይስተጓጎል ያግዛሉ፡፡

በተመሳሳይ፤ የተቋሙ የኢንተርኔት ኔትወርክ መሰረተልማት ዝርጋታ እና የአገልግሎት አቅርቦት ሂደቱ አስተማማኝ እንዲሆን ሁለት ሁለት አማራጮች ያሉት የመስመር ዝርጋታ በየማዕከላቱ መከናወኑን የጠቀሱት ደሳለኝ (ኢንጂኒየር)፤ ተግባሩ በዚህ መልኩ ተፈጻሚ እንዲሆን ኢትዮ ቴሌኮም እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

“ተቋሙ በዋና መሥሪያ ቤቱ አማካኝነት ሥራውን በይፋ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ፣ በሂደትም የማዕካላትን ቁጥር በፍጥነት እያሳደገ በተጓዘበት ርቀት ውስጥ፣ በኤሌክትሪክ ኃይል ወይም በኢንተርኔት ኔትወርክ መቆራረጥ ምክንያት የአገልግሎት አሰጣጥ መስተጓጎል አልገጠመውም” ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በግንባታ ሂደት፣ በአደጋ ወይም በሌላ ምክንያት በመስመሮቹ ላይ እክል እና የኔትወርክ መቆራረጥ ቢፈጠር፣ የኢንተርኔት ኔትወርክ አቅራቢው ተቋም አፋጣኝ ጥገና እንዲያደርግ የሚያስገድድ ስምምነት (Service-Level Agreement-SLA) መፈጸሙንም ጠቁመዋል፡፡

በተቋሙ አማካኝነት መተግበር የጀመረው፣ ለመዲናችንም ሆነ ለአገራችን የመጀመሪያ የሆነው የተንቀሳቃሽ የአዲስ መሶብ አገልግሎት ላይ፣ አስተማማኝ የኃይልና የኢንተርኔት አቅርቦት እንዲኖር ተደርጓል፡፡ አገልግሎቱን ለማቅረብ የተዘጋጀው ዘመናዊና ምቹ አውቶቡስ፣ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠራ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ከጸሐይ ጨረር ኃይል ማመንጨት የሚያስችል ቴክኖሎጂ ተገጥሞለታል፡፡ የኢንተርኔት ኔትወርክ መስመሩም ያለአንዳች ችግር በየትኛውም የከተማዋ አካባቢዎች ተንቀሳቅሶ አገልግሎት መስጠት የሚያስችለው ነው።

እንደ ከተማ አስተዳደር በከፍተኛ ትኩረት እየተገነባ እና እየተስፋፋ ያለው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ተቋም፣ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዓለም ከደረሰበት የዕድገትና የለውጥ ደረጃ ጋር የሚወዳደር የመንግስት አገልግሎት ለመስጠት ጥረቱን አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ በዚህም ዋና መሥሪያ ቤቱ በሚገኝበት የአራዳ ማዕከል፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 17፣ 6 የፌደራል፣ 2 ባንኮች በድምሩ የ25 ተቋማትን 150 አገልግሎቶች ለተገልጋይ እያቀረበ ይገኛል፡፡ በቀሪዎቹ ማዕከላት ደግሞ፤ 15 ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ 2 ባንኮች እንዲሁም 5 የፌዴራል ተቋማትን በድምሩ የ22 ተቋማትን 114 አገልግሎቶች ለከተማዋ ነዋሪ በአቅራቢያቸው አድርሷል፡፡ በዘመናዊ አውቶቡስ በታገዘው የተንቀሳቃሽ አገልግሎቱም ተደራሽነቱን አስፍቷል፡፡

በዚህ መልኩ አስደናቂ የለውጥ ጉዞ ላይ የሚገኘው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት፤ አንድ ዓመት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ፤ ከዚህ በፊት በመንግስት ተቋማት በሚሰጠው አገልግሎት የሚታዩ ችግሮችን በማቃለል፣ በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ተገልጋዮች ፈጣን፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊ፣ ወጪና ጊዜ ቆጣቢ አገልግሎት መስጠቱን የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተስተናገዱ ተገልጋዮች መሰረት የአዲስ መሶብ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተገልጋዮች እርካታ 99 ከመቶ መድረሱን ጠቁመዋል፡፡ ይህንን ውጤታማነት ማስቀጠል፣ የሕዝቡን ግብረመልስና አስተያየት በመቀበል፣ ጊዜና ወቅቱን በሚመጥን መልኩ በጥናት ላይ የተመሰረተ ማሻሻያዎችን ማድረግ እንደሚገባ፣ ለዚህ ደግሞ ተቋሙ፣ ከከተማ አስተዳደሩ፣ ከሚመለከታቸው ተቋማት እና ከማህበረሰቡ ጋር በቅርበትና በትብብር መሥራቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ተናግረዋል፡፡

ኢኮኖሚ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ለከተማ ግብርና ውጤታማነት የተቋማት ተሳትፎ እስከ ምን?

- በአዲስ አበባ ከተማ 2 ሺህ 757 ተቋማት በከተማ ግብርና ስራ ላይ በመሳተፍ ምርታማነትን የመጨመር ሚና እየተጫወቱ ነው




ፎቶ- ከገፀ ድር

የመጋላ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የከተማ ግብርና ስራ ወጤት በጥቂቱ

**በይግለጡ ጓዴ**

የከተማ ግብርና በከተማ ውስጥ ባሉ ክፍት ቦታዎች ላይ ለምግብነትና ለሌሎች ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታዎች ሊውሉ የሚችሉ ሰብሎችን፣ የአትክልትን፣ የፍራፍሬዎችን እና የእንስሳት ተዋፅኦ ምርቶችን የማልማት ሥራ ነው። ይህ ዘርፍ እንስሳትን የማርባት፣ ንብ የማነብ፣ ዓሳ የማርባት፣ የግብርና ምርት ውጤቶችን የማቀነባበር፣ ለተጠቃሚው የማቅረብ እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃን በስፋት የሚያካትት ትልቅ ተግባር ነው።

ዘርፉ ዘመናዊ አሠራርና ቴክኖሎጂን በመጠቀም በግልና በተደራጀ መንገድ ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠሪያና አስተማማኝ ገቢ ማስገኛ እየሆነ ይገኛል። የግብርና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ በከተሞች የምግብ አቅርቦት እንዲጨምር በማድረግ የቤተሰብ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ሲሆን፣ ምርትን ለገበያ በስፋት ማቅረብ የሚያስችል አቅም ፈጥሯል።

በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃም ባለፉት ጥቂት ዓመታት በከተማ ግብርና ረገድ የጊዜና የቦታ ዕይታ ለውጥ መጥቷል። በተግባር ሠርቶ በማሳየትና በማበረታታት አዲስ የከተማ ግብርና ባህልና ልማድ በህብረተሰቡ ዘንድ እየተፈጠረ ይገኛል። ዛሬ ዛሬ ጓሮን ጦም ማሳደርና የተቋማትን ክፍት መሬት ለጢሻ መተው እየተነወረ የመጣ ሲሆን፣ "ለምን መሬት ባዶ ይሆናል?" ብሎ የሚጠይቅ ከተሜም ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል።

ይህንን የከተማ ግብርና ተግባር ባህል በማድረግና አስፈላጊ የማምረቻ ግብዓቶችን በየደረጃው በማቅረብ የከተማ ግብርና ልማት በከተማዋ በከፍተኛ ሁኔታ እየተጠናከረ ይገኛል። የከተማ ግብርና በተለያዩ ድርጅቶች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በሆስፒታሎች፣ በማረሚያ ቤቶች እና በመንግሥትና የግል መሥሪያ ቤቶች ውስጥ በስፋት መተግበሩ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ወጪን ለመቀነስና አረንጓዴ አካባቢን ለመፍጠር ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

ተቋማት ያላቸውን ሰፊ ቦታ፣ የህንፃዎች ጣራ ወይም ክፍት መሬትን በመጠቀም የተለያዩ የግብርና ሥራዎችን ማከናወን እንደሚችሉ በተግባር እየታየ ነው። ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ስር የሚገኘው የመጋላ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፣ ተቋሙ እያከናወነ ከሚገኘው የመማር ማስተማር ስራ ጎን ለጎን በትምህርት ቤቱ የከተማ ግብርና ስራን በከፍተኛ ሁኔታ አጠናክሮ በመቀጠል ላይ ይገኛል።

የከተማ ግብርና እና የሌማት ትሩፋት መርሐ-ግብር ለሀገር ኢኮኖሚ እና ለቤተሰብ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። በትምህርት ቤቱ እየተተገበረ በሚገኘው በዚህ መርሀ-ግብርም ዘርፈ-ብዙ ውጤቶች በመመዝገብ ላይ ናቸው። በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ያሉ ባዶ ቦታዎችን ለከተማ ግብርና ስራ በማዋል በበጋው የመስኖ ስራ የጥቅል ጎመን ምርትን በስፋት በማምረት ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና ለአካባቢው ነዋሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረቡ ይገኛሉ።

የመጋላ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር መምህር ኃይለማሪያም ክንዴ እንደገለጹት፣ ትምህርት ቤቱ ከተቋቋመበት ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ የከተማ ግብርና ስራ በሙከራ ደረጃ ላይ የነበረ ቢሆንም፣ በተደራጀ አቅም በመምህራን፣ በተማሪዎችና በአስተዳደር ሰራተኞች በስፋት መተግበር የተጀመረው ግን ካለፈው ዓመት ወዲህ መሆኑን አብራርተዋል።

ትምህርት ቤቱ በቅጥር ግቢው ውስጥ በሚገኝ 2 ሺህ ካሬ ሜትር ባዶ ቦታ ላይ ቀይ ስር፣ ጎመን፣ ድንችና ጤፍ በማምረት የትምህርት ቤቱን ገቢ እያሳደገ ይገኛል። በዚህ ዓመት የጤፍ ምርት ከተሰበሰበ በኋላ፣ ወዲያውኑ ጥቅል ጎመን በመትከል ምርቱን ለገበያ ማሰራጨት ችለዋል። እንደ ርዕሰ መምህሩ ገለጻ፣ "መሬት ጾም ማደር የለበትም" የሚል ፅኑ አቋም በመያዝ በዓመት ሁለት ጊዜ የተለያዩ የጓሮ አትክልት እና የሰብል ምርቶችን እያመረቱ ነው።

በትምህርት ቤቱ ለጓሮ አትክልት ልማት የገጸ-ምድርና የከርሰ-ምድር ውሃን ጥቅም ላይ እያዋሉ መሆናቸውን የጠቀሱት ርዕሰ መምህሩ፣ የክፍለ ከተማውና የወረዳው የከተማ ግብርና ጽህፈት ቤቶች የሙያ፣ የግብዓት እና የምርጥ ዘር ድጋፎችን እንደሚያደርጉላቸው ተናግረዋል። በተለይም የቀይ ስር፣ የድንችና የጥቅል ጎመን ምርጥ ዘር ድጋፍ እንደሚያገኙ ጠቁመው፣ ምርቱን የገበያ ጥናት በማድረግ ለተጠቃሚው ተደራሽ ያደርጋሉ።

በዚህ ዓመት ስድስት መኪና ሙሉ ጥቅል ጎመን እና 10 ኩንታል ጤፍ አምርተው ለገበያ አቅርበዋል። አንድ መኪና ጥቅል ጎመን በ120 ሺህ ብር ሂሳብ በመሸጥ ከስድስት መኪና ጥቅል ጎመን ሽያጭ ብቻ 720 ሺህ ብር ገቢ አግኝተዋል። ይህ ጥቅል ጎመን ለአካባቢው ማህበረሰብ፣ ለትምህርት ቤቱ መምህራንና ለአስተዳደር ሰራተኞች ተደራሽ ሆኗል። ትምህርት ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ ሲያመርት ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ የሚያገኝ ሲሆን፣ ገቢው ለችግረኛ ተማሪዎች ምገባና ለትምህርት ቤት ግብዓት ማሟያ ይውላል።

ርዕሰ መምህር ኃይለማሪያም በቀጣይም ትምህርት ቤቱ የከተማ ግብርና ስራን ይበልጥ በማጠናከር፣ ከሰብልና ከጓሮ አትክልት ምርት በተጨማሪ የእንስሳት እርባታ ስራ በመጀመር የተቀናጀ የከተማ ግብርና ስራን በተግባር ለመተግበር ማቀዳቸውን ገልጸዋል። በሌላ በኩል በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የወረዳ 3 የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ መሐመድ ፈቃዱ በወረዳው 25 ተቋማት በ1 ነጥብ 25 ሄክታር መሬት ላይ በከተማ ግብርና እየተሳተፉ መሆኑን ተናግረዋል።

እነዚህም በስድስት የመንግስት እና የግል ትምህርት ቤቶች፣ በአንድ ጤና ጣቢያ፣ በአንድ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ፣ በስምንት የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በአራት የግል ድርጅቶች፣ በአምስት የኃይማኖት ተቋማት እንዲሁም በሁለት መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ውስጥ ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል። ተቋማቱ በካሮት፣ ድንች፣ ጎመን፣ ቀይስር፣ ሰላጣና ቆስጣ ልማት ላይ የተሰማሩ ሲሆን፣ የተሻለ አቅም ያላቸው ተቋማት ለሌሎች ልምድ እንዲለዋወጡ በማድረግ የአሰራር ተሞክሮን የማስፋት ስራ እየተሰራ ነው።

የከተማ ግብርና ስራ ገበያን በማረጋጋት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው የገለጹት አቶ መሐመድ፣ የመጋላ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የሰላም ፍሬ ጤና ጣቢያ ምርቶቻቸውን ለገበያ በማቅረብ ገበያ በማረጋጋት ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የክፍለ ከተማው የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት የእጽዋት ልማት ቡድን መሪ አቶ ጉደታ ሽብሩ በበኩላቸው፣ "ምንም ክፍት መሬት ጾም ማደር የለበትም" የሚለውን የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አቅጣጫ መነሻ በማድረግ ተቋማት በቅጥር ግቢያቸው በስፋት እንዲሳተፉ መደረጉን ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅት በክፍለ ከተማው ወደ 444 ነባርና አዳዲስ ተቋማት በከተማ ግብርና ላይ እየተሳተፉ ሲሆን፣ የሙያ ድጋፍ፣ የምርጥ ዘር አቅርቦትና የሱፐርቪዥን እገዛ እየተደረገላቸው ይገኛል።

በአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእጽዋት ልማት ቡድን መሪ አቶ ገቲሶ ቢጃሞ በከተማዋ በአጠቃላይ 2 ሺህ 757 ተቋማት በከተማ ግብርና ስራ ላይ ተሳታፊ መሆናቸውን ገልጸው፣ ዘርፉ የስራ እድል በመፍጠር፣ ገቢን በማስገኘትና ምርታማነትን በመጨመር ረገድ ውጤታማ እየሆነ መምጣቱንና ለዚህም የኮሚሽኑ ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የአዲስ አበባ የአየር ንብረት ጥበቃ ሲቃኝ

**በለይላ መሀመድ**

የአየር ንብረት ለውጥ በዓለም ዙሪያ ካሉ ትልልቅ ችግሮች አንዱ ሆኖ ቀጥሏል። በየጊዜው የምንመለከታቸው የምድር ሙቀት መጨመር፣ የዝናብ ስርጭት መዛባት፣ ድርቅ፣ ጎርፍ እና ሌሎች ክስተቶች መነሻቸው የአየር ንብረት ለውጥ ነው።ለአየር ንብረት ለውጥ ዋና መንስኤ ከሆኑት መካከል የሰው ልጅ ተጠቃሽ ነው። ይህን በውል በመረዳት ለመፍትሄው መትጋት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ነው፤ በከተማችን አዲስ አበባ እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ መፍትሄ የሆኑ የተለያዩ ተግባራት በስፋት እየተከናወኑ የሚገኙት።

በዚህ ጽሑፍም፤ መዲናችን አዲስ አበባ የአየር ንብረት ለውጥ ችግርን መፍትሄ ለመስጠት ምን እየሠራች ነው? ውጤቱስ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? የሚለውን ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡ ጉዳዩን በተመለከተ ማብራሪያና ሙያዊ ሃሳብ የሚያጋሩን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአየር ንብረት ለውጥና አማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ዳይሬክተር አቶ ሰይድ አብደላ ናቸው።

አቶ ሰይድ ማብራሪያቸውን የጀመሩት፤ የዘንድሮው (የ2018 ዓ.ም.) አለም የአየር ንብረት ለውጥ "ትኩረት ለአየር ንብረት ለውጥ (Climate Action") የሚል መሪ ሀሳብ መጠቀሙን በማስታወስ ነው። እነዚህን ሀሳቦች በማንገብ በየአመቱ የተካሄዱ አለምአቀፍ ጉባኤዎች ቢኖሩም፤ ከቃል ባለፈ ወደ ተግባር መግባት ላይ ክፍተቶች አሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሆኑት ያደጉ ሀገራት ለተጎጂ ሀገራት ድጋፍ አድርጉ ሲባሉ ፍቃደኛ ያለመሆን እና ፍቃደኛ የሆኑትም በቃላቸው ያለመገኘት ዋነኛው ችግር ነው ብለዋል፡፡

እንደሳቸው ገለጻ፣ የዓለም መንግስታት ጉዳዩን ቸል ቢሉትም፤ የአየር ንብረት ለውጡ ግን አሁንም እንደቀጠለ ነው። ሙቀት እየጨመረ ነው፡፡ ከአመት ዓመት የሙቀት መጨመር፣ የዝናብ ወቅት መዋዠቅ፣ የዝናብ ማነስና መብዛት እየተከሰተ ነው። በሃገራችን እያጋጠመ ያለው የድርቅና የጎርፍ አደጋ የአየር ንብረት ለውጥ ውጤት ነው፡፡

## በአዲስ አበባ ለአየር ንብረት ለውጥ መንስኤዎች

በባለስልጣኑ የአየር ንብረት ለውጥና አማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ዳይሬክተሩ አቶ ሰይድ የአዲስ አበባን ሁኔታ አስመልክተው እንደገለጹት፤ ለአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ ከሚሆኑት አንደኛው በተፈጥሮ የሚለቀቀው በካይ ጋዝ ነው፡፡ ይህ በዋናነት በሰዎች እንቅስቃሴ ምክንያት ወደ አየር በሚለቀቁ ሙቀት አማቂ ጋዞች (እንንደ ካርቦንዳይ ኦክሳይድ፣ ሚቴን) የመሳሰሉት መብዛት ነው፡፡ እነዚህ ጋዞች በባህሪያቸው ከጸሀይ የሚመጣው እና መሬት ነጥሮ የሚመለሰውን የጸሀይ ሙቀት እንዳይመለስ አፍነው ያስቀሩታል። በዚህም የአካባቢው ሙቀት እንዲጨምር ያደርገዋል።

በተለይም በሰው ልጅ እንቅስቃሴ ምክንያት የሚለቀቀው ካርቦንዳይ ኦክሳይድ እንዲሁም ለተለያዩ አገልግሎቶች ጥቅም ላይ ከሚውሉ የኃይል አማራጮች (ነዳጅ፣ ከሰል፣ ደን፣ የማገዶ እንጨት) የሚወጣው ካርቦንዳይ ኦክሳይድ መጠን እንዲሁም ከተሽከርካሪ ጭስ፣ ከሚቃጠል ቆሻሻ፣ ከኢንዱስትሪ የሚወጣው መርዛማ ጋዝ ከፍተኛ ነው፡፡ ከብስባሽ ነገሮች የሚወጣው ሚቴን የተባለው አማቂ ጋዝም የችግሩ መንስኤ መሆኑን ተናግረዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ከሆኑ መንስኤዎች ከፍተኛውን ደረጃ የሚይዘው ከተሽከርካሪዎች የሚወጣው ጋዝ መሆኑን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ "ከተሽከርካሪዎች የሚወጣው ጋዝ በካርቦንዳይ ኦክሳይድ እንዲሁም ነዳጁ በደንብ ሳይቀጣጠል ሲቀር በሚመነጭ ናይትረስ ኦክሳይድ የተባለ መርዛማ ጋዝ አማካኝነት ለአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ ይሆናል፡፡ በተለይ ናይትረስ ኦክሳይድ በሰውም ሆነ በእንስሳት ሳምባ ውስጥ በመግባት የጤና ችግር ያስከትላል። ከመኪና የሚወጣው ጥቁር ጭስ በሚያርፍበት ስፍራ ላይ ጥላሸት ሲፈጥር ይታያል፡፡ እንዲህ አይነቱ ጭስ ሰዎች ቢስቡት በቀጥታ ሳምባ ወስጥ ይገባል። ከናፍጣ ሰልፈር ዳይኦክሳይድ ሊወጣ ይችላል፡፡" ብለዋል፡፡

ዳይሬክተሩ አክለው እንዳብራሩት፤ ሌላው ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሆነው በኢነርጂ ዘርፍ የሚፈጠር ነው፡፡ በቤት ውስጥ እንጨት፣ ከሰል... ሲቀጣጠል ሊሆን ይችላል፡፡ በከተማዋ ከሰል የማይጠቀም ማህበረሰብ የለም። በተመሳሳይ ከከሰል የሚወጣውን ጭስ በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል፡፡ በደንብ ካልተቀጣጠለ ሰዎችን አፍኖ የሚገድለው ካርቦን ሞኖኦክሳይድ የተባለው ጋዝ ይለቀቃል፡፡ የሚቀጣጠል ነገር ካለ በደንብ ቢቀጣጠልም እንኳን ካርቦንዳይ ኦክሳይድ መለቀቁ አይቀሬ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ቆሻሻ ሲበሰብስ ወይም ሲቃጠል የሚወጣው ሚቴን ጋዝ ለአየር ንብረት ለውጥ መፈጠር መንስኤ ነው፡፡ ከኢንዱስትሪ የሚለቀቅ አማቂ ጋዝም ሌላው በከተማ ለሚፈጠረው የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ መሆኑን አክለዋል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ችግር ከመዲናዋ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማስተሳሰር አቶ ሰኢድ የሚከተለውን ብለዋል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ በዝናብ እጥረት ሳቢያ የሚከሰት ድርቅን ያስከትላል። ከተማ ላይ የዝናብ እጥረት ካላ ወደ ግድብ የሚገባ በቂ ውሀ ስለማይኖር ለመጠጥም ሆነ ለንጽና መጠበቂያ የሚሆን የውሀ እጥረት እንዲከሰት ያደርጋል፡፡ ውሀ ለከተማው ነዋሪ በፈረቃ ለማቅረቡ አንደኛው ምክንያት ይሄው የአየር ንብረት ለውጥ ያስከተለው ተጽእኖ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአየር ንብረት መለውጥ ምክንያት የጎርፍ አደጋ ይፈጠራል። የዝናብ ስርዓት ይዋዥቃል። አንድ ጊዜ አይኖርም ካለም በሀይል ጥሎ ከፍተኛ ጎርፍ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ አዲስ አበባ የጎርፍ አደጋ ይከሰት ነበር፡፡ በዚህም በወንዝ ዳርቻ ሰፍረው በነበሩ ቤቶች ላይ ጉዳት ይደርስ ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጀመረው የወንዝ ዳርቻ ልማት ከዚህ ችግር ታድጓል፡፡ ሌላው በከተማዋ የሙቀት መጠን እየጨመረ ከሄደ የወባ በሽታ ሊፈጠር እንደሚችል ዳይሬክተሩ አብራርተዋል፡፡

## የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ምን እየተሰራ ነው?

እንደ አዲስ አበባ ከተማ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም በሁለት መንገድ እየተሰራ መሆኑን አቶ ሰኢድ አንስተዋል፡፡ እንደሳቸው ማብራሪያ ከሆነ፤ የሙቀት አማቂ ጋዞችን የመከላል፣ የመቀነስና የመግታት ስራ የመጀመሪያው የትኩረት መስክ ነው። ሁለተኛው ደግሞ፤ ከተለወጠው አየር ንብረት ጋር እንዴት አብሮ መኖር እንደሚቻል የማሰብ እና ለዚህ መፍትሄ የሚሆን ተጨባጭ ሥራ ማከናወን ነው።

ከዚህ ጋር ተያያዘ እንደ ከተማ አስተዳዳር የተለያየ ተግባራት እየተከናወኑ ነው፡፡ ለምሳሌ ከትራንስፖርት ሴክተሩ አንጻር በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ የመንገድ መሰረተ ልማትን ማሳለጥ የመሳሰሉ ተግባራት እየተሰሩ ነው፡፡ እነዚህም ሙቀት አማቂ ጋዝ እና የአየር ብክለት እንዲቀንስ የላቀ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

ከደረቅ ቆሻሻና ከሀይል አጠቃቀም አንጻር ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው፡፡ ለምሳሌ ደረቅ ቆሻሻ ዝም ብሎ ሲበሰብስ የሚለቀውን ከፍተኛ ሚቴን ጋዝ ለመቀነስ ቆሻሻን ወደ ኮምፖስት እንዲቀየር ግንዛቤ የመፍጠር ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ሚቴን ከካርቦን ዳይኦክሳይድ ጋር ሲነጻጸር በከፍተኛ ደረጃ ሙቀት የማመቅ አቅም አለው፡፡ ስለዚህ ቆሻሻን ወደ ኮምፖስት እንዲለወጥ ማድረግ በተወሰነ ደረጃ የሙቀት አማቂ ጋዝን መቀነስ ይቻላል፡፡ በሀይል አጠቃቀም ረገድ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ እንዲሻሻል የማድረግ ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃን በመጠቀም ሙቀት አማቂ ጋዝን መቀነስ ይቻላል፡፡

በአሁኑ ወቅት እንደ አዲስ አበባ ከተማ በርካታ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋምና ከተፈጠረው የአየር ንብረት ለውጥ ጋር ለመላመድ አስተዋጽ የሚያበረክቱ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በተለይም የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር፣ የኮሪደር እንዲሁም የወንዝ ዳርቻ ልማት አብነቶች ናቸው፡፡ በወንዝ ዳርቻ የተተከሉት አረንጓዴ ተክሎች የጎርፍ መሸርሸር ችግርን ከመቅረፍ ባለፈ የካርቦን ልቀትን በከፍተኛ ደረጃ መጥጠው እስከመያዝ የደረሰ ጥቅም አላቸው፡፡ በዚህ ልክ የአረንጓዴ ልማት እየተስፋፋ ሲሄድ የከተማዋን ሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስና የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል እገዛው ከፊተኛ እንደሚሆን አያጠያይቅም፡፡


ፎቶ፡- ከገፀ ድር
ከእንጦጦ እስከ ቀጨኔ መድኃኔያለም ያለው የወንዝ ዳርቻ ልማት ከፊል ገፅታ

## በተሰራው ሥራ የመጣ ለውጥና ቀጣይ ዕቅድ

የሙቀት አማቂ ጋዝ እየጨመረ ነው ወይንስ እየቀነሰ ነው የሚለውን ማወቅ የሚቻለው ኢንቬንተሪ (አዲስ አበባ ከየሴክተሩ ምን ያህል ካርቦንዳይ ኦክሳይድ እንደምትለቅ የሚደረግ ቆጠራ) ተሰርቶ በሚወጣው ሪፖርት ነው፡፡ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በየሁለት ዓመቱ ኢንቬንተሪ ይካሄዳል። ባለፈው ዓመትም ይኸው ተካሂዷል። በውጤቱም ቀደም ብሎ ከነበረው አማቂ ጋዝ ቀንሶ ይታያል። ከዚህ በተጨማሪ በ2019 ዓ.ም ኢንቬንተሪ እንደሚካሄድና የሚኖረው የአማቂ ጋዝ መጠን ሊቀንስ እንደሚችል ይገመታል፡፡ ችግሩ ግን ለምሳሌ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ቢገቡም የነዳጅ ተሽከርካሪዎች መግባታቸው አለመቅረቱ ዳይሬክተሩ አቶ ሰይድ እንደክፍተት አንስተዋል።

ዳይሬክተሩ አቶ ሰይድ አያይዘውም፤ መደበኛ ስራዎችን ከመስራት ባለፈ ሴክተሮች ለአየር ንብረት ለውጥ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ድጋፍና ክትትል እንዲሁም ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል፡፡ ከሀይል አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሶላር ኢነርጂ እንዲስፋፋ ማድረግ አንዱና ዋናው የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡ በከተማ አስተዳደር የሚገኙ ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ ክፍለ ከተሞች ሶላር ኢነርጂን እንዲሁም የትምህርት ቤት ምገባ ማእከላት ማገዶ ቆጣቢ የሆነ ትልልቅ ምድጃዎችን እንዲጠቀሙ የማስተዋወቅና ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ በእቅድ የተያዙ ናቸው፡፡ በየትምህርት ቤቶቹ የሚገኙ የምገባ ማእከላት የሚጠቀሙት እንጨት በመሆኑ ከባድ የአየር ብክለት ከማስከተሉም በተጨማሪ ለሙቀት አማቂ ጋዞች መፈጠር ምክንያት ናቸው።

የአየር ንብረት ለውጥ የዘመናችን ትልቁ ፈተና ከመሆኑ የተነሳ ለችግሩ ተገቢውን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። መንግስት፣ ተቋማት እና ግለሰቦች በጋራ በመስራት የአየር ንብረት ለውጥን ሊቀንሱ እና ተጽእኖውን ሊቋቋሙ ይችላሉ። የዛሬ ተግባራችን የነገውን የአካባቢ ደህንነት ይወስናል፤ ስለዚህ ለአየር ንብረት ለውጥ ትኩረት መስጠት ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ነው።

## የምቹ... ከገጽ 6 የዞረ

30 በመቶ ማድረስ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የቀረው እቅድ ትንሽና የሚሳካ እንደሆነ አቶ ግርማ አብራርተዋል፡፡

አቶ ግርማ አክለውም፣ በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በመዲናዋ ብቻ ከ6 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ዕቅድ ተይዞ ወደ ስራ ተገብቷል። ለተከላ የተዘጋጁት የችግኝ ዓይነቶችም የከተማዋን ዘመናዊ ፍላጎት ያማከሉና በጥናት የተመረጡ ናቸው። በዚህም መሰረት ዘንድሮ የሚተከሉት ችግኞች ለከተማ ውበት፣ ለጥላ እና የፍራፍሬ ተክሎች ተብለው የተዘጋጁ ናቸው። ይህ ዓይነቱ አሰራር ከተማዋን ውብና አረንጓዴ ከማድረግ ባለፈ፣ ነዋሪዎች ጥላና ንጹህ አየር እንዲያገኙ እንዲሁም ከጓሮቻቸውና ከተከሏቸው ዛፎች ለምግብነት የሚውሉ የፍራፍሬ ምርቶችን እንዲሰበስቡ የሚያስችል ሁለገብ ጥቅምን ያገናዘበ ስትራቴጂ ነው።

በመሆኑም ተቋማት ግቢያቸውን በአረንጓዴ እንዲሸፍኑ፣ ነዋሪው በግቢው እንዲተክል እያበረታታን ነው ያሉት ቢሮ ኃላፊው ሀገር በቀልና የፍራፍሬ ችግኞች ዋነኛ ትኩረታችን ናቸው ብለዋል፡፡ የፍራፍሬ ዛፎች በወንዝ ዳርቻዎች ይተከላሉ፤ ይህም ውበትንም፣ ምግብንም፣ ጥላንም በአንድ ለማግኘት ያስችላል ብለዋል፡፡

ይህ የተያዘው ከፍተኛ ግብ እንዲሳካ የመዲናዋ ነዋሪዎች፣ ወጣቶችና የተለያዩ ተቋማት ልክ እንደ ቀደሙት ዓመታት ሁሉ ዘንድሮም በከፍተኛ ተነሳሽነትና በንቃት እንደሚሳተፉ ተገልጿል። ሕዝባዊ ተሳትፎው መርሃ ግብሩ ውጤታማ እንዲሆን ዋነኛው መሰረትም ነው፡፡

አቶ ግርማ አክለውም በአዲስ አበባ ባለፉት ሰባት ዓመታት ህብረተሰቡ ያደረገው ተሳትፎ አስደናቂ ነበር። ዘንድሮም ሚሊዮኖች በችግኝ ተከላ ስራው ላይ እንደሚሳተፉ ጠቁመዋል፡፡

ይሁንና ችግኝ መትከል ብቻውን በቂ ባለመሆኑ፣ ከተተከሉ በኋላ ባሉት ወራት የሚደረገው ጥበቃ፣ ውሃ የማጠጣትና የመንከባከብ ልዩ ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ ነው። ይህም በመዲናዋ የአረንጓዴ አሻራን የመጽደቅ ምጣኔ ይበልጥ ከፍ ለማድረግና የተረጋገጠ ውጤት ለማስመዝገብ ትልቅ እገዛ ያደርጋል።

አዲስ አበባ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ላይ የምታደርገው ይህ ንቁ ተሳትፎ ለመጪው ትውልድ የምትመች፣ የአየር ብክለት የቀነሰባትና የአረንጓዴ ልማት ተምሳሌት የሆነች መዲናን ለመፍጠር ለተያዘው አገራዊ ራዕይ መሳካት የጎላ ድርሻ አለው። ከተማዋ በየዓመቱ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞችን የመትከል አገራዊ ግብ ላይ የራሷን አሻራ በማሳረፍ፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የምታደርገውን ጥረት አጠናክራ ቀጥላለች።

## ከስጋት... ከገጽ 8 የዞረ

ከነበረበት የብክለት ገጽታው ተላቅቆ፣ አሁን የወንዙ ዳርቻ የተለያየ ቀለም ባላቸው አበቦችና ለምለም ሳሮች አጊጧል።

ለነዋሪዎች ምቾት ተስማሚ የሆኑ ፅዱና ሰፋፊ የእግረኛና የሳይክል መንገዶች፣ እንዲሁም ማረፊያ ወንበሮች ተሰናድተውለታል። በአካባቢው የሚነፍሰው ነፋሻማ አየርና የቦታው ድንቅ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ስፍራውን በግል አሊያም ከጓደኛና ከቤተሰብ ጋር ውብ ጊዜ ለማሳለፍ ተመራጭና ምቹ እንደሆነ በቅኝታችን መረዳት ችለናል።

የዓለም ባንክ የከተሞች ስውር ሀብት ወይም "The Hidden Wealth of Cities: Creating, Financing and Managing Public Spaces" በሚል ርዕስ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2020 ባወጣው ሰነድ ላይ እንደተመላከተው፤ በከተሞች ውስጥ ሕዝብ በጋራ የሚገለገልባቸው ቦታዎች (Public Spaces) በሕንፃዎችና በተቋማት መካከል የሚገኙና ለሕዝብ ክፍት የሆኑ አካባቢዎች ናቸው። እነዚህም መንገዶችን፣ የእግረኛ መሄጃዎችን፣ ክፍትና አረንጓዴ ቦታዎችን (ፓርኮችን፣ አደባባዮችን፣ የውሃ አካላትንና የወንዝ ዳርቻዎችን) እንዲሁም የሕዝብ መገልገያ ተቋማትን (እንደ ቤተ መጻሕፍት፣ የማኅበረሰብ ማዕከላትና ገበያዎች) ያካትታሉ።

እነዚህ ስፍራዎች ማኅበራዊ መስተጋብርን በማጠናከር፣ ጤናማ ማኅበረሰብን በመፍጠር፣ የሥራ ዕድልን በማስፋፋትና የአካባቢ ጥበቃን በማገዝ ለአንድ ከተማ ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በተለይም ፓርኮችና አረንጓዴ ስፍራዎች ለማኅበራዊ ግንኙነትና ለመዝናኛ አስፈላጊ ከመሆናቸው ባለፈ ለእግር ጉዞ፣ ለአካላዊ እንቅስቃሴና ለሌሎች ሞተር አልባ የመጓጓዣ ዓይነቶች ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ።

በተቃራኒው፣ ምቹ የእግረኛ መንገዶች መጥፋትና የመዝናኛ ቦታዎች አለመኖር የሚያስከትለው ጉዳት የጎላ ነው። ሰነዱ የዓለም ጤና ድርጅት የ2016 (እ.ኤ.አ) ጥናት ዋቢ አድርጎ እንዳመላከተው፣ ከአካላዊ እንቅስቃሴ ማነስ ጋር ተያይዞ የሚመጣው የሰዎች ቁጥር መጨመር በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚከሰቱት የሞት አደጋዎች 3 ነጥብ 3 በመቶ ድርሻ ይይዛል።

በከተሞች ውስጥ ያሉ የጋራ መጠቀሚያ ቦታዎችን አረንጓዴ ማልበስና ማስዋብ የሙቀት መጠንን በመቀነስ የነዋሪዎችን ጤናና ደህንነት ያሻሽላል። እንደ ቤተ መጻሕፍት፣ የማኅበረሰብና የስፖርት ማዕከላት ያሉ መሠረተ ልማቶች ደግሞ ከሚሰጡት አገልግሎት ባሻገር ነዋሪው በአካባቢው ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማውና ማኅበራዊ ትስስር እንዲገነባ ይረዳሉ። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፣ ጥራት ባላቸው የጋራ መገልገያዎች አቅራቢያ የሚኖሩ ሰዎች ለሌሎች ያላቸው እምነት ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ፣ የማግለል ስሜት አይሰማቸውም፤ በመንግሥት ላይ ያላቸውም እምነት የላቀ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየጋራ መኖሪያ ቤቶችና በመንገድ አካፋዮች ላይ እያከናወነ ካለው የአረንጓዴ ስፍራዎች ልማት በተጨማሪ፣ በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች የሚገኙ የወንዝ ዳርቻዎችን ከብክለት የጸዱ፣ አረንጓዴና ለኑሮ ምቹ የማድረግ ሰፊ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። በበሻሌ ወንዝ ላይ የተገነባውን የለሚ ወንዝ ዳርቻ ፓርክን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች የተከናወኑ የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎች፤ ወንዞች ከብክለትና ከወንጀል መሸሸጊያነት እንዲወጡ አድርገዋል። በምትኩ እነዚህ ስፍራዎች የውበት፣ የመዝናኛ፣ የጤና መጠበቂያ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራና የገቢ ምንጭ ማዕከል እየሆኑ ይገኛሉ። በዚህም የተነሳ የነዋሪዎች ማኅበራዊና ሥነ-ልቦናዊ ሕይወት እየታደሰ፣ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውም በተግባር እየተረጋገጠ ነው።

## "ሰልጣኞቹ.. ከገጽ 9 የዞረ

ባለቤቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ ሚናቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

አዲስ ልሳን ጋዜጣ፡- በቀጣይ ጥቂት ዓመታት ውስጥ ማዕከሉን የት ደርሶ ለማየት ይመኛሉ?

ሂርጳሳ ጫላ (ዶ/ር)፡- የከተማ አስተዳደሩ በተግባር የተፈተነ ሥራ እየሠራ ይገኛል። በ2030 እ.ኤ.አ ማዕከሉን የሴቶች አቅም ግንባታ ዋና ማዕከል የማድረግ ራዕይ ይዟል፡፡ በዋናነት የሴቶች አቅም ግንባታ ላይ የሚሠራ፣ ወቅቱን የዋጀ የቴክኖሎጂና የሳይንስ የምርምር ማዕከል (Center of Excellence) እንዲሆን የማስቻል ሥራ ይሠራል፡፡ ለዚህም ደግሞ የጀመርናቸውን ሥራዎች አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል።

አዲስ ልሳን ጋዜጣ፡- ስለሰጡን ማብራሪያ እናመሰግናለን፡፡

ሂርጳሳ ጫላ (ዶ/ር)፡- እኔም ለተሰጠኝ ዕድል አመሰግናለሁ፡፡

## ኢትዮጵያ... ከገጽ 11 የዞረ

የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ቀደም ሲል ከነበሩት የተለመዱ የታሪክ መስህቦች በተጨማሪ አዳዲስና አስደናቂ የተፈጥሮ መዝናኛ አማራጮችን እንዲያገኙ አድርጓቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ፕሮጀክቶቹ በተገነቡባቸው ገጠራማ አካባቢዎች ለሚኖሩ ማኅበረሰቦች ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የመሠረተ-ልማት አውታሮችን በማስፋፋትና የአካባቢ ጥበቃ ግንዛቤን በማሳደግ የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ እየቀየሩት ይገኛሉ።

አርቲስት መምህሩ ጫሞም ኢትዮጵያ እጅግ በርካታና ማራኪ የሆኑ የኪነ ጥበብና የቱሪዝም ሀብቶች ባለቤት መሆኗን አንስቷል። ይህ የተፈጥሮ፣ የታሪክና የባህል በረከት ደግሞ ከተለያዩ የዓለም ማዕዘናት በርካታ ጎብኚዎችን አቀናጅቶ ለመሳብና የሀገሪቱን ገጽታ ለመገንባት እጅግ ምቹና ተመራጭ አጋጣሚ መሆኑን ገልጿል።

ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ቱሪዝም መንገድ የምታደርገው ጉዞ የሀገሪቱን ገጽታ ከመገንባትና የውጭ ምንዛሬ ከመሳብ ባሻገር፣ ለዓለም አቀፉ የአየር ንብረት ጥበቃ የምታበረክተውን አስተዋጽዖ ያሳያል። ይሄንን ዘላቂ የጉዞ ባህል በሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ዘንድ እንዲሰርጽ ሰፊ ግንዛቤ መፍጠር ከተቻለ፣ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀዳሚዋ የአረንጓዴ ቱሪዝም መዳረሻ የመሆን ዕድሏ እጅግ ሰፊ ነው።

ወይዘሮ ሶስና በበኩላቸው ኢትዮጵያ ለቱሪዝም መዳረሻ የሚሆን በርካታ ሃብቶች አሏት፡፡ ሀገራችን ሁሉም ነገር አንድ ላይ የተሰጣት ነች፡፡ ከራስ ዳሽን እስከ ዳሉል በተፈጥሮ ተዘርዝረው የማያልቁ ባህላዊ ሃብቶች እና ዘመናትን ያስቆጠሩ የሃይማኖት እና ቅርስ ታሪኮች አሉን፡፡ አዲስ አበባም በርካታ አዳዲስ እና ነባር መዳረሻዎች አሏት፡፡ እነዚህን በአግባቡ ማስጎብኘት ከተቻለ ኢትዮጵያን በዘርፉ መሪ ማድረግ ይቻላል ሲሉ አንስተዋል፡፡


# ማስታወቂያ

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ ሲሳይ አበበ ፈለቀ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 12 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA00008110467 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 21 ቀበሌ 25 በአዲሱ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 146/3 በእነ ገነት ከበደ (3 ሰዎች) ስም የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ቅድመ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ይዞ እንዲቀርብ እየጠየቅን ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቂርቆስ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## አቢዳን ዴዬሪ እና ቤቨሬጅስ ማምረቻ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

### የባለአክስዮኖች የስብሰባ ጥሪ

የባለአክሲዮኖች የስብሰባ ጥሪ በመጪው እሁድ ሐምሌ 12 ቀን 2018 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት በድርጅቱ ጽ/ቤት ስለሚካሄድ የማህበሩ አባላት ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን እና ሰዓት በስብሰባው ቦታ ላይ እንዲገኙ በአክብሮት ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

**የዕለቱ መደበኛ የስብሰባ አጀንዳዎች፡-**

1. የ2018 ዓ.ም በጀት አመት ሪፖርት ማዳመጥ
2. የ2018 ዓ.ም የውጪ ኦዲት ሪፖርት ማዳመጥ እና ትርፍ እና ኪሳራ ላይ መወያየት
3. ለድርጅቱ አዲስ አባል ስለመቀበል

**ማሳሰቢያ**

1. ማንኛውም ባለአክስዮኖች ለስብሰባ ሲመጣ ማንነቱን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ዋናውን እና ኮፒ ይዞ መገኘት አለበት፡፡
2. በስብሰባው መገኘት የማይችል አባል በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ አገልግሎት ቀርቦ ውክልና በመስጠት ተወካይ የውክልና ማስረጃውን ኦርጅናል እና 2 ኮፒ እና የታደሰ መታወቂያ በመያዝ በስብሰባው ላይ መሳተፍ ይችላል ፡፡

**አቢዳን ዴዬሪ ኤንድ ቢቨሬጅስ ማኑፋክቸሪንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000060802524 ሴሪ ቁጥር- R 031831 የሆነው በአቶ መርእድ ማሞ መድፉ ስም በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በ ለገሰ ባሊ አረዶ ስም የተመዘገበ ነባር ይዞታ ካርታ ቁጥር KK.07/84/837/86/7/00 የጠፋባቸው መሆኑን በ09/10/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 የይዞታ መለያ ቁጥር፡- AA000060807902 ሴሪ ቁጥር- C 011257 የቤት ቁጥር M-304 በወ/ሮ ቆንጅት ከተማ ገብረማሪያም ስም በተቋማችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቻዋለው የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ፣ ከወጣበት ቀን እስከ 90 ቀን ድረስ በጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ /ሰርተፍኬት/ እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ መኪያ ሁሴን ስም የተመዘገበ ነባር ይዞታ ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/316/14860/00 ሴሪ ቁጥር 029517 የጠፋባቸው መሆኑን በ08/10/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በእነ መላኩ ባህነ ጋርጋዶ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩ/8/2/8/30/143064/00 የሴሪ ቁጥር 1669673 የቤቱ ስፋት በሰነድ 64.74 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና በእነ መላኩ ባህነ ጋርጋዶ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩ/8/2/8/30/143064/00 የሴሪ ቁጥር 1669673 የቤቱ ስፋት በሰነድ 64.74 ሜ.ካ የሆነው ካርታ የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ አስማ ተማም ሀሰን ስም የተመዘገበ ይዞታ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የካርታ ቁጥር 38964 ሴሪ ቁጥር 01553 የሆነ ይዞታ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 01/10/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ አስማ ተማም ሀሰን ስም የተመዘገበ ይዞታ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የካርታ ቁጥር 38963 ሴሪ ቁጥር 8421 የሆነ ይዞታ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 01/10/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር AMB/14/19 በሰኢድ ዋሃብረቢ ጁሀር ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ተነፃፃሪ የጋራ መኖሪያ ቤት ባለቤትነት ካርታ ቁጥሩ AA000020300012040319 የተሰጠበት ቀን 21/05/2013 ዓ/ም የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 27/10/2016 ዓ/ም ይህንኑ የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ በ90 ቀን ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች ብዙወርቅ ግዛው ወ/ዮሀንስ በቀን 02/10/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 14 አባዶ ውስጥ የካ12/17361/08 የሴሪ ቁጥር 108680 የቤት ቁጥር B-108/02 የቤቱ ስፋት በሰነድ 70.75 ሜ.ካ የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነው ኮንዶሚኒየም ቤት ኦርጅናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ምትክ እንዳገኝ ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኃላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወርቂቱ ሁንዴ ጫላ ስም የተመዘገበ ይዞታ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የካርታ ቁጥር ወ6/ውዝ01/50/611/125/15/00 ሴሪ ቁጥር 0261796 የሆነ ይዞታ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 09/10/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ብሌን ነጋ እና ታረቀኝ አድማሱ የእነ ትዕግስት ይርሳልኝ አጥናፌ ተወካዮች በቀን 26/9/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በይርሳልኝ አጥናፌ ስም የተመዘገበ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ውስጥ የካርታ ቁጥር ቦሌ10/42/7/5/9082/10021/01 የሴሪ ቁጥር 0120471 የቦታው ስፋት በሰነድ 93 ሜ.ካ የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነው ይዞታ ኦርጅናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ምትክ እንዳገኝ ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኃላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በ ደብረወርቅ ኦላና ኤባ ስም በልደታ ክ/ከ ወረዳ 08 የቤ.ቁ 018/511 ሴሪ ቁጥር 048145 ካርታ ቁጥር ል.08/111/6539/00 ካርታ የተሰጠበት ቀን 26/06/2005 የሆነ ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት ምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመቸ ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥር እና ሴሪ ቁጥር እና በባለጉዳዩ ስም የተመዘገቡትን ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ኦርጂናል ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀፅ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በዘርትሁን መርጋ ልካሳ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦ/አራ/11/76/1/3/11338/00 የሴሪ ቁጥር 1435057 የተሰጠበት ቀን 05/03/2009 የቤቱ ስፋት በሰነድ 54.29 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ማህደራቸው ያሳያል፡፡

ይሁንና በዘርትሁን መርጋ ልካሳ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦ/አራ/11/76/1/3/11338/00 የሴሪ ቁጥር 1435057 የተሰጠበት ቀን 05/03/2009 የቤቱ ስፋት በሰነድ 54.29 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ከእጃቸው የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያለን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የቅጥር ማስታወቂያ

## አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ  አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል።

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔት | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የቴሌቪዥን ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 1 | የቴሌቪዥን ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ረዳት አዘጋጅ | XI | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 6/4 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.148 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |
| 2 | የቴሌቪዥን ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ከፍተኛ ሪፖርተር | X | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 5/3 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.152 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |
| 3 | ከፍተኛ የዶክመንተሪ አዘጋጅ | XIII | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 8/6 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.156 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |
| 4 | የዶክመንተሪ አዘጋጅ | XII | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 7/5 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.159 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |
| 5 | ጀማሪ የቴሌቪዥን ዜና ሪፖርተር | VII | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 0 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ | አ/18.121 እስከ አ/18.126 | 5 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |
| **ለህትመትና ዲጂታል ሚዲያ ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 6 | የህትመት ግራፊክስ ባለሙያ | - | በማንኛውም የትምህርት ዝግጅትና ደረጃ ሆኖ በህትመት ግራፊክስ ላይ ልዩ ችሎታ እና ክህሎት ያላዉ/ላት | | የተግባር መመዘኛ መስፈርቶች (Technical & Practical Skills)<br>. የሶፍትዌር አጠቃቀም ብቃት (Software Proficiency):<br>. ለግራፊክስ ዲዛይን: Adobe Photoshop, Illustrator, እና InDesign ላይ ከፍተኛ ችሎታ ያለው/ላት። | - | 1 | በታለንት ግዢ | በተቋሙ አሰራር እና ስምምነት | አዲስ አበባ |
| 7 | ግራፊክ ዲዛይነር እና አኒሜተር ባለሙያ (Graphic Designer & Animator) | - | በማንኛውም የትምህርት ዝግጅትና ደረጃ ሆኖ በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች (TikTok, YouTube Shorts, Instagram Reels, Facebook) የሚመጥኑ የቪዲዮ ቅርጾችን (Formats/ Aspect Ratios) እና የዲዛይን ስታይሎችን ጠንቅቆ መረዳት የሚችል/ የምትችል። | - | የሶፍትዌር አጠቃቀም ብቃት (Software Proficiency):<br>o ለቪዲዮ ኤዲቲንግ: Adobe Premiere Pro, Final Cut Pro, ወይም DaVinci Resolve እንዲሁም EDUIS ላይ ከፍተኛ ክህሎት ያለው።<br>o ለግራፊክስ ዲዛይን: Adobe Photoshop, Illustrator, እና InDesign ላይ ከፍተኛ ችሎታ ያለው/ላት።<br>o ለሞሽን ግራፊክስ (Motion Graphics): Adobe After Effects አጠቃቀም ላይ የተመሰከረለት (ተመራጭ)።<br>• የፖርትፎሊዮ/ሾውሪል ግምገማ (Portfolio/Show reel Evaluation):<br>o ባለፉት ጊዜያት የሰራቸውን ምርጥ ስራዎች የሚያሳይ የቪዲዮ ማጠቃለያ (Show reel) እና የዲዛይን ስራዎች ስብስብ ማቅረብ መቻል።<br>o በስራዎቹ ላይ የታየው የዲዛይን ጥራት፣ የቀለም ቅንጅት (Color Grading)፣ የድምፅ አሰራር (Audio Mixing) እና የትራንዚሽን (Transitions) አጠቃቀም ደረጃ። | | 5 | በታለንት ግዢ | በተቋሙ አሰራር እና ስምምነት | አዲስ አበባ |
| **የቋንቋዎች ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 8 | አረብኛ ቋንቋ ከፍተኛ ሪፖርተር | X | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 3/1 ዓመት | በማንኛዉም የማህበራዊ ሳይንስ  የት/ት መስክ ሆኖ የአረብኛ ቋንቋ መስማት፤ መናገር፤ መፃፍና  ማንበብ የሚችል | አ/18.815 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት   ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. የምዝገባው ቀን ሰኔ 15 ቀን 2018 ዓ.ም እስከ ሰኔ 27 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ
5. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
6. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስት ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111551848

**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

# የአለም ዋንጫ፡- አይረሴ ትዝታዎቻችን



ፎቶ፡- ከገፀ ድር
የ96 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋው የዓለም ዋንጫ ውድድር በልዩ ልዩ ትዝታዎች ታጅቦ ጉዞውን ቀጥሏል

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የዓለም ዋንጫ በእግር ኳስ ቤተሰቡ ዘንድ በከፍተኛ ጉጉት የሚጠበቅ የምድራችን ቁንጮ ስፖርታዊ ውድድር ነው፡፡ የዓለም ዋንጫው ተፎካካሪ አገራት የፖለቲካና መሰል ልዩነቶቻቸውን ወደጎን ትተው በሰላሙ መድረክ ትንቅንቅ የሚፈጥሩበት ታላቅ ስፖርታዊ ውድድር ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ ፊፋ እና የዓለም አቀፍ የሚዲያ ተንታኞች ያወጡት አሃዛዊ መረጃ እንደሚሳየው የዘንድሮውን የዓለም ዋንጫ በዓለም ዙሪያ 6 ቢሊዮን ህዝብ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ይከታተሉታል። ይህም ከአጠቃላይ የዓለም ህዝብ ቁጥር ወደ 73 በመቶ ገደማ ህዝብ ውድድሩን ይከታተለዋል እንደማለት ነው።

በዓለም የእግር ኳስ አፍቃሪያን ዘንድ በጉጉት የሚጠበቀውና ቁጥሩ የበዛ ተከታታይ ያለው ይህ ስፖርታዊ ሁነት ከተመልካች ጋር የሚፈጥረው ቁርኝትና ጥሎት የሚያልፈው ትዝታ ቀላል አይሆንም፡፡ የቀድሞው የአርሰናል እግር ኳስ ክለብ አሰልጣኝ እና የፊፋ የዓለም እግር ኳስ ልማት ኃላፊ አርሰን ቬንገር ውድድሩ በሰዎች የዕድሜ ታሪክ ላይ ስለሚተክለው የማይደበዝዝ ትዝታ ሲናገሩ፣ "ሰዎች ህይወታቸውን በዓመታት አይቆጥሩትም፤ በዓለም ዋንጫዎች እንጂ። 'ያ የዓለም ዋንጫ ሲደረግ እዚህ ቦታ ነበርኩ፤ ያኔ ገና ተማሪ ነበርኩ፤ ያኔ ልጄ የተወለደችበት ዓመት ነበር'፤ እያሉ የህይወታቸውን ታሪክ ከውድድሩ ትዝታ ጋር ያቆራኙታል። የዓለም ዋንጫ የሰው ልጅ የትዝታ ማህደር ነው።" ማለታቸው የሚታወስ ነው፡፡

ይህ ውድድር ከኢትዮጵያውያን ስፖርት ቤተሰብ ጋር ያለው ቁርኝትም የጠበቀ ስለመሆኑ ብዙ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ አሁን ላይ መላው ዓለም ዐይኑን ወደ አሜሪካ፣ ካናዳ እና ሜክሲኮ ባዞረበት ወቅት፣ የእግር ኳስ ስፖርት አፍቃሪያንና የዓለም ዋንጫ ያላቸውን የጠበቀ ታሪካዊ ቁርኝት ወደኋላ መለስ ብለን ለመቃኘት ወደድን።

የ96 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋው የዓለም ዋንጫ ውድድር ከኢትዮጵያውን እግር ኳስ ቤተሰብ ጋር ያለው ቁርኝት ዓመታትን የዘለቀ ነው፡፡ ቴሌቪዥን ብርቅ በሆነበት እና የጣሪያ ላይ አንቴና የሀብታም ቤት መለያ በሆነበት በዚያ ዘመን፤ የዓለም ዋንጫን ለማየት የማይጓጓ አልነበረም ማለት ይቻላል። እንዲህ አይነት ቤቶችን ደጅ መጥናት ግድ ይል ነበር። በቀለም አልባ ቴሌቪዥን ሳይቀር የእነማራዶናን፣ ዚኮን፣ ፕላቲኒን እግር ኳሳዊ ክህሎት በቀጥታ ስርጭት የተከታተሉና የኳስ ጥበባቸውን የቀሰሙም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም፡፡

አርጀንቲናዊው የእግር ኳስ ጥበበኛ ዲያጎ ማራዶና በዓለም ዙሪያ ዝነኛ በሆነበትና በሜክሲኮ የተካሄደው 13ኛው የዓለም ዋንጫ ሳይቀር በአዲስ አበባ የእግር ኳስ አድናቂዎች ዘንድ ልክ እንደ ቅርብ ጊዜ ትዝታ ይተረካል፡፡ የሜክሲኮው የዓለም ዋንጫ የተካሄደው ከዛሬ 40 ዓመት በፊት በመሆኑ ውድድሩን በቀጥታ የመመልከት ዕድል የነበራቸው ጥቂቶች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ውድድሩ ካለፈ ከዓመታት በኋላም ቢሆን በተለይ የአርጀንቲናዊውን ዲያጎ ማራዶና እግር ኳሳዊ ጥበብ ለማየት መታደላቸውን ያስረዳሉ፡፡ የማራዶና አድናቂው ቴዎድሮስ ኃይሉ በወቅቱ የነበረውን ትውስታ ሲያስረዱ፣ የልብስና የጫማ ውጤቶች በሙሉ በማራዶና እየተሰየሙ ከተማውን አጥለቅልቀውት እንደነበር እና ፋሽን ነው የተባለ ቱታ፣ ፒጃማ፣ ስኒከር ጫማ፣ ሸሚዝ፣ ጂንስ ሱሪ… የሁሉም መጠሪያ "ማራዶና" ሆነው እንደነበር አጫውተውናል፡፡ በተጨማሪም በውድድሩ ላይ የተካፈሉት የእያንዳንዱን ተጫዋቾች ፎቶ ግራፍ የያዘ ማስቲካ መጥቶ እንደነበር ነግረውናል፡፡

አያይዘውም፣ የዓለም ዋንጫ ውድድሮች እንደ አንድ የህይወታቸው የታሪክ ምዕራፍ አድርገው እንደሚወስዱትና ጨዋታዎቹ በብዙ የአከባቢው ወጣቶች ላይ ተጽዕኖ እንደነበራቸው ይገልጻሉ። በተለይም አንዳንድ የአካባቢው ወጣቶች ፕሮፌሽናል የእግር ኳስ ተጫዋቾች እስከመሆን የደረሱት የዓለም ዋንጫው ተጽዕኖ አርፎባቸው ሳይሆን እንደማይቀርም ያስረዳሉ ቴዎድሮስ፡፡ አንዳንድ የስፖርት ቤተሰቦች ከዓመታት በፊት በተከናወኑ የዓለም ዋንጫ ውድድሮች ላይ የተጫወቱትን እነ ቡርቻጋ፣ ቫንባስተን፣ ሩድ ጉሌት፣ ካሬካ፣ ጋሪ ሊነከር፣ ጆን ባርነስ፣ ሎታር ማትያስ፣ ሩዲ ቮለርን ዛሬም ድረስ በወቅቱ ያሳዩት የነበረውን ስፖርታዊ ትዕይንት አንድም ሳይሸራረፉ ለማስረዳት አይቸገሩም፡፡

የቀድሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋች ኃይሌ ካሴ፣ አሊ ረዲና ለበርካታ እውቅ ስፖርተኞች የትውልድ ቦታ በሆነው ኳስ ሜዳ፣ ፈረንሳይ፣ መሳለሚያ፣ አውቶብስ ተራና መሰል አከባቢዎች ከእግር ኳስ ጋር ልዩ ቁርኝት አላቸው፤ በተለይ ደግሞ ከዓለም ዋንጫ ጋር፡፡ ለኳስ ሜዳ ልጆች በዓለም ዋንጫ የወይዘሮ አቻሜ 14 ኢንች ቴሌቪዥን እና የአቶ አራጌ ግሮሰሪ ውለታ እንዲሁ በቀላሉ የሚረሳ አይደለም፡፡ እንዲህ እንዳሁን ቴሌቪዥን በየቤቱ በሽበሽ ባልነበረበት በዚያን ወቅት እንደነ ወይዘሮ አቻሜና ጥቂት ቤቶች ካልሆነ በስተቀር ቴሌቪዥን ብርቅ ነበር፡፡

በወቅቱ ታዲያ እነዚህ ጥቂት ቤቶች 'በእግር ኳስ ፍቅር ላበዱ' የአካባቢው ወጣቶች የዓለም ዋንጫ የሚባል የውድድር ዓይነት መኖሩን ከማስተዋወቅ ጀምሮ አስደናቂ የውድድሩ ትዕይንቶችን እንዲመለከቱ ዕድል ፈጥረዋል፡፡ እ.ኤ.አ ከየ1990 የጣሊያው የዓለም ዋንጫ እና የ1994ቱ የአሜሪካው የዓለም ዋንጫ ውድድሮች አንስቶ ባለፉት ዓመታት የተከናወኑት ውድድሮች ለእንደነ ተፈራ ኃይሉ ላሉ እና ለአካባቢው ወጣቶች ልክ አንደ ቅርብ ጊዜ ትዝታ በአዕምሯቸው ታትመዋል፡፡ በውድድሮቹ የተቆጠሩ ጎሎች፣ ጨዋታው፣ ተጫዋቹና ቡድኖቹ እንደዚሁም እንደነ ኮሊና ያሉ ምርጥ ዳኞች ዛሬም ድረስ በእነ ተፈራ ልብ ውስጥ ቀርተዋል፡፡

እንደ አስተያየት ሰጪዎቻችን ከሆነም ለምን እንደሆነ በማያውቁት ምክንያት በቅርበት በተከናወኑ የዓለም ዋንጫዎች ላይ ካዩዋቸው ክስተቶች ይልቅ በወቅቱ በእነዚያ ትንንሽ መጠን ባላቸው ቴሌቪዥኖች የተመለከቷቸው የዓለም ዋንጫ ውድድሮች በዐይነ ህሊናቸው ተቀርፀው እንደቀሩ ያስረዳሉ። በወቅቱም የአከባቢው ወጣቶች የቅጽል ስሞቻቸውን ቤቤቶ፣ ባጆ፣ ማራዶና ብለው እስከመሰየም ደርሰው እንደነበርም ጨምረው ገልጸዋል፡፡ በርካታ ወጣቶችም የጣሊያናዊውን የእግር ኳስ ኮከብ ሮቤርቶ ባጂዮ የፀጉር ቁርጥ አይነት ወይም 'ስታይል' ያዘወትሩ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡

የዓለም ዋንጫ በእግር ኳስ ኤክስፐርቶች በጣም አሰልቺ የተባለለት በጣሊያ የተካሄደው 14ኛውንም የዓለም ዋንጫ በማስታወስ በፍጻሜው ጨዋታ ዳኛው ብዙ ቢጫና ቀይ ካርዶችን ማሳየታቸውንና አጨቃጫቂ "የፍጹም ቅጣት ምት" ሰጥተው የጨዋታውን ስሜት አበላሽተውት እንደነበር አጫውተውን አስገርመውናል፡፡ ምን ያህል ውድድሩን በትኩረት ይከታተሉ እንደነበር ሌላ ማስረጃ ስናስከትል ጨዋታው በጣሊያን ሀገር የተካሄደ በመሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ስርጭቱን ለማስተላለፍ ስፖንሰር የሆነው የጣሊያ ነዳጅ አቅራቢ ኩባኒያ የሆነው "አጂፕ" እንደነበር ነግረውናል፡፡

በዓለም ዋንጫው እጅግ ከፍተኛ ደስታ የፈጠረላቸው የካሜሩን ብሔራዊ ቡድን እንደነበርና አርጀንቲናን፣ ሩማኒያንና ኮሎምቢያን ያሸነፈባቸው ጨዋታዎች ከአዕምሯቸው እንደማይጠፋ ብዙዎች ይናገራሉ፡፡ ሮጀር ሚላ፣ አማም ቢይክ፣ ማካናኪ እና በረኛው ቶማስ ንኮኖ በተጨማሪም የሩማኒያው ጆርጅ ሃጂ፣ የአርጀንቲናዎቹ ዲየጎ ማራዶና እና ክላውዶ ካኒንጃ፣ የካሜሩኖቹ ሮጀር ሚላ እና ማካናኒ፣ የብራዚሎቹ ካሬካ፣ አሊማው እና ሙለር የዓለም ዋንጫ ትዝታዎች ናቸው፡፡

ጣሊያናዊያኑ ቫቶሬ ሺላቺ እና ሮቤርቶ ባጂዮ፣ የቼኮዝሎቫኪያው ቶማስ ስኩራቪ፣ የስፔኑ ሚሼል፣ የእንግሊዞቹ ጋሪ ሊንከር እና ፖል ጋስኮኝ፣ የእንግሊዙ በረኛ ፒተር ሼልተን፣ የጀርመኖቹ ሎታር ማትያስ እና ሩዲ ቮለር በየዘመናቸው የወቅቱ ኮከብ ተጫዋቾች እንደነበሩ ያስታውሳሉ፡፡

በጥቅሉ በዓለም ዋንጫው የየአገራቱ የተለያዩ ባህላዊ ጭፈራዎች፣ አልባሳትና አስደናቂ ውድድሮች ጋር ታጅበው ለኢትዮጵያውያን የትዝታ መዝገብ ላይ ተከትበዋል፡፡ ብራዚላውያኑን እነ ሮማሪዮና ቤቤቶ፣ ጣሊያናዊውን ሮቤርቶ ባጂዮን ጨምሮ በወቅቱ ታላላቅ ተጫዋቾችን ያስተዋወቀው የ1994 የዓለም ዋንጫ ወዲህም የውድድሩ ተመልካቾች እየጨመሩ ስለመምጣታቸው የኳስ ሜዳ ልጆች አጫውተውናል፡፡ በአካባቢውም የብራዚልና የአርጀንቲና ብሔራዊ ብድን ደጋፊዎች እንደሚበዙና ብሔራዊ ቡድኖቹ ካሸነፉ አከባቢው በደስታ ሽንፈት ከገጠማቸው ደግሞ የሀዘን ድባብ እንደሚያጠላ ያስታውሳሉ፡፡

ታዋቂው የእንግሊዝ ስፖርት ተንታኝ ማርቲን ታይለር የሚለውም ይህንኑ ነው፡፡ የዓለም ዋንጫው በተመልካች አእምሮ ውስጥ ስለሚስለው ዘላለማዊ ምስል ሲገልጽ፣ "ዳኛው የመጨረሻውን ፊሽካ ሲነፉ ጨዋታው ያበቃል፤ ተጫዋቾቹም ሜዳውን ለቀው ይወጣሉ። ነገር ግን ያ ክስተት በተመልካቹ ልብ ውስጥ የሚተክለው ስሜት ለዘላለም አይሞትም። ከአስርት ዓመታት በኋላም እንኳ ያቺን የአሸናፊነት ጎል ወይም ያቺን የለቅሶ ቅጽበት ስታስታውሳት፣ ልክ ትናንት እንደተከሰተ ሆኖ በውስጥህ ይቀሰቀሳል።" ብሏል፡፡